የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች



ከኢንተርናሽናል ኮርስፖንዳንስ ኢንስትቲዩት ጋር በመተባበር በሮበርት ኤል ብራንት ተዘጋጅቶ በሥነ መለኮት በቤቴ አማካኝነት ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተመለሰ ስለ ጸጋ ስጦታዎች የመማሪያ መጽሐፍ

Spiritual Gifts

የመጀመሪያ እትም
ያሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

1994 - አዲስ አበባ
ሥነ መለኮት በቤቱ

ማውጫ ገጽ

መግቢያ 5

ክፍል አንድ፡- የጸጋ ስጦታዎች

1. እግዚአብሔር ለአንተ ስጦታዎች አለው 9
2. እግዚአብሔር ስለ ስጦታዎቹ እንድታውቅ ይፈልጋል 21

ክፍል ሁለት፡- የአገልግሎት ስጦታዎች

3. ሐዋርያትና ነብያት 33
4. ወንጌላውያንና መጋብያን - እስተማሪዎች 49
5. ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች - 1 67
6. ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች - 2 79

ክፍል ሦስት፡- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

7. የጥበብ ቃል፣ የእውቀት ቃል፣ እምነት 93
8. የፈውስ ስጦታዎች፣ ተዓምራትን ማድረግና ትንቢት 109
9. መናፍስትን መለየት፣ ልዩ ልሳን፣ ልዩ ልሳንን የመተርጉም ስጦታ 129

የሙከራ ፈተናዎች መልስ 146

መግቢያ

"ስለ መንፈሳዊ ነገርም፥ ወንድሞች ሆይ፣ ታውቁ ዘንድ አወዳለሁ" (1ቆሮ 12፡1)። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለክርስቶስ አካል እጅግ አስፈላጊ በመሆናቸው እግዚአብሔር ለልጆቹ ስለስጣቸው ስለ እነዚህ ስጦታዎች መማር እጅግ ደስ ያሰኛል። ያለ እነዚህ ስጦታዎች ቤተ ክርስቲያን ሕልውና አግኝታ ወደ ፊት መራመድ አትችልም።

አማኞች እንደመሆናችን መጠን ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በተቻለ መጠን መማርና ማወቅ ይገባናል። በዚህ አንጻር ያለንን እውቀት በጨመርን መጠን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎቹም በሕይወታችንና በአገልግሎታችን ሰፋ ያለ ስፍራ ይኖራቸዋል። እኛም ለአማኙ ማህበረሰብ ታላቅ በረከት መሆን ከመቻላችንም በላይ በወንጌል ስርጭት ተግባርም ይበልጥ ውጤታማ እንሆናለን።

በዚህ ኮርስ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሦስት ክፍል ተመድበው ቀርበዋል። እነዚህንም ምድቦች 1) የአገልገሎት ስጦታዎች 2) ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች 3) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በማለት እንጠራቸዋለን።

የመጀመሪያው ምድብ፥ ማለትም "የአገልግሎት ስጦታዎች" በሚለው ውስጥ ክርስቶስ ቤተ ክርስትያንን እንዲመሩ የጠራቸውን አማኞች የሚያጠቃልል ሲሆን፣ በሁለተኛው ምድብ፥ ማለትም "በአጠቃላይ የአገልግሎት ስጦታዎች" ለአማኞች ሁሉ ስለሚሰጡ ስጦታዎች እናጠናለን። "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች" በተባለው በሦስተኛው ምድብ፥ ደግሞ የምንማረው መንፈስ ቅዱስ እንደ ወደደ ለአማኞች ስለሚሰጣቸው ዘጠኝ ስጦታዎች ይሆናል።

የትምህርቱ፥ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት ስታጠናቅቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

1. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መተላለፊያ በመሆን በኩል ያለውን አስፈላጊነት መግለጽ፣
2. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ተግባርና ዓላማ መረዳት፣
3. የመንፈስ ቅዱስን የማነጽ ተግባር ከአርኩሳን መናፍስት የጥፋት ሥራ ጋር በማነጻጸር ልዩነቱን መግለጽ፣
4. በክርስቶስ አካል ውስጥ ያሉትን የጸጋ ስጦታዎች ልዩ ባሕርያት መረዳትና አሰራራቸውንም በአድናቆት መመልከት፣
5. በጸጋ ስጦታዎችና በተፈጥሮ ችሎታ መካከል ያለውን ልዩነት መግለጽ፣

6. በአገልግሎታትህ ውስጥ ያሉትን የጸጋ ስጦታዎች ማወቅ፣ መለማመድና አጠቃቀማቸውን ማሳደግ፣

7. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለክርስትና ሕይወት አገልግሎት ያላቸውን አስፈላጊነት በመገንዘብ ታላቅ ግምት መስጠት፣

8. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አጠቃቀምን በተመለከተ የሚያንዣብቡትን ችግሮች ለይቶ ማወቅና መፍትሔ ማቅረብ መቻል።

የመጽሐፉ አጠቃቀም

"የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች" የተባለው የመማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀው በግልም ሆነ በጋራ ሆናችሁ ትምህርቱን መከታተል ትችሉ ዘንድ እንደ አስተማሪ ሆኖ መመሪያ በመስጠት እንዲያገለግል ታስቦ የቀረበ ነው። እንድ ተማሪ በሚገባ ለመማር አስተማሪ የሚሰጠውን መመሪያ በጥንቃቄ መከተል እንደሚገባው፣ ይህም መጽሐፍ የሚሰጠውን መመሪያ በጥንቃቄ መከተል እንደሚያስፈልግ አስቀድሞ መረዳት ይገባል።

እንዲሁም የሚሰጠውን የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል ማንበብ፣ የሚቀርቡትን ጥያቄዎች መመለስ፣ የትምህርቱን መመሪያዎች በመከተል በየትምህርቱ መጨረሻ የሚቀርቡትን የሙከራ ፈተናዎች በሚገባ ማጠናቀቅ ከእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሚጠበቅ ግዴታ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ትምህርቱን በሚገባ ለመከታተል የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ መኖር አስፈላጊ ነው። ለዚህም የቀድሞውና አዲሱ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ቢኖራችሁ እያስተያያችሁ ብታነቡ የበለጠ ጠቃሚና መልካም ይሆናል።

የትምህርቱ አዘገጃጀትና የአጠናኑ ስልት

እያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት የሚከተሉትን በቅደም ተከተል ይይዛል።

1. ርዕስ
2. መግቢያ
3. የክፍለ ትምህርቱ አስፋፊል
4. የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች
5. የትምህርቱ ዝርዝር
6. ለጥናቱ የሚረዱ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች
7. የሙከራ ፈተና (ክትምህርቱ በስተመጨረሻ)
8. የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስና በመጽሐፉ መጨረሻም የሙከራ ፈተናዎች መልስ ቀርበዋል።

የትምህርቱ አከፋፈልና ዓላማዎች በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ላይ አጠቃላይ ሃሳብ ይሰጣሉ፣ ጥናቱን በምታጠናበት ወቅት እጅግ አስፈላጊ በሆኑት ነጥቦች ላይ እንድታተኩር ይረዱሃል።

በትምህርቱ ዝርዝር ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ በዚህ የጥናት መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ክፍት ሥፍራዎችን በመሙላት ሊመለሱ የሚችሉ ናቸው። ሆኖም ረዘም ያሉ መልሶችን በማስታወሻ ደብተርህ መጻፍ ይገባል። መልሶችን በማስታወሻ ደብተርህ የምትጽፍ ከሆነ የጥናቱን ቁጥርና ርዕሱን መመዝገብህን እርግጠኛ ሁን።

የራስህን መልሶች ከመስጠትህ በፊት በመጽሐፉ የቀረቡትን መልሶች እትመልከት። የራስህን መልሶች የምትሰጥ ከሆነ ያጠናኸውን ጥናት በተሻለ ሁኔታ ትረዳዋለህ። የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን ከመለስህ በኋላ በክፍለ ትምህርቱ በስተመጨረሻ ከተሰጡት መልሶች ጋር አስተያይ። ከዚያ በኋላም በትክክል ያልመለስካቸውን አርማቸው። የቀረቡትን መልሶች በድንገት ተመልክተህ የሚቀጥለውን ጥያቄ መልስ ማግኘት እንዳትችል መልሶቹ የቀረቡት በቁጥር ቅደም ተከተል አይደለም። እነዚህ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። በጥናቱ የቀረቡትን ዋና ዋና ሃሳቦች እንድታስታውስ ከመርዳቱም በላይ ከትምህርቱ ያገኘሃቸውን የሕይወት መርሆዎች ተግባራዊ እንድታደርግ ይረዱሃል።

1 እግዚአብሔር ለአንተ ስጦታዎች አለት

ትምህርት

ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተገቢውን መሠረት እንዲያስጨብጡን ከታተዱት ሁለት ክፍለ ትምህርቶች ይህ የመጀመሪያው ክፍለ ትምህርት ነው። በዚህ የመጀመሪያው ክፍለ ትምህርት በክርስቶስ አካል ውስጥ እያንዳንዱ አማኝ ስለሚኖረው አስፈላጊነት እንማራለን።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሚሰጡት የክርስቶስ አካል ብልት ለሆኑት ብቻ ስለሆነ ስለዚሁ አካል ምንነትና እንዴትም እንደሚሠራ በተቻለን መጠን ማወቅ ይገባናል። ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኛችን አድርገን በተቀበልንበት ወቅት የዚህ አካል አንድ ክፍል ሆነናል። ክርስቶስን እንደግል አዳኙ የተቀበለ ማንኛውም አማኝ የዚህ አካል አስፈላጊ ክፍል ወይም ብልት ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ስጦታዎችን ይሰጣል። ስጦታዎቹ ከሰው ሰው ይለያያሉ።

ሰው እንደመሆናችን መጠን የአንድ ምድራዊ ቤተሰብ ወይም ጎሳ አባል መሆናችን የታወቀ ነው። ክርስቶስን እንደግል አዳኛችን በተቀበልንበት ወቅት ደግሞ ከዚያ ይልቅ እጅግ የከበረ ቤተሰብ ማለትም የክርስቶስ አካል ክፍል ወይም አባል ሆነናል። ይህንን ክፍለ ትምህርት እያጠናን ስንሄድ ለእግዚአብሔርና ለሌሎችም የአካል ብልቶች እያንዳንዳችን ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆንን በመገንዘብ፣ እግዚአብሔርም ለእኛ የተለየ ስጦታን ወይም ስጦታዎችን እንደሚሰጠንና እኛም በአገልግሎታችን መጠቀም እንዳለብን እንረዳለን።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- ሁላችንም የአካሉ ብልቶች ነን
- እያንዳንዱ ብልት አስፈላጊ ነው
- ራሳችንን ከሌሎች ጋር ልናወዳድር አይገባንም
- በስጦታዎቻችን ታማኝ ልንሆን ይገባል

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

- የክርስቶስ አካልን ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መዘርዘር፣

- በክርስቶስ አካል ውስጥ እያንዳንዱ ብልት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ መግለጽ፤
- አንድ አማኝ ራሱን ከሌላ አማኝ ጋር ለምን ማወዳደር እንደማይገባው ሦስት ምክንያቶችን መዘርዘር
- የአካል ብልቶች እግዚአብሔር በስጣቸው ስጦታዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው መግለጽ

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. የክፍለ ትምህርቱን ማጠናከሪያ ካነበብህ በኋላ የተሰጡትን ጥቅሶች አንድ በአንድ በመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ ተመልከት።
2. 1ቆሮ 13ን ቢቃልህ ማጥናት ጀምር። ይህንን ክፍለ ትምህርት በምታጠናቀቅበት ወቅት የመጀመሪያዎቹን ሁለት ቁጥሮች በቃልህ ልታጠናቸው ይገባል።
3. ክፍለ ትምህርቱን እንደሚገባ አጥና። እንድትሠራቸው የተጠየቅኸውን ጥያቄዎች መሥራትህን አረጋግጥ። በየጊዜውም መልሶችህ ትክክል መሆናቸውን አመሳክር።
4. በክፍለ ትምህርቱ በስተመጨረሻ የቀረቡትን የሙከራ ፈተና አጠናቅ። ከጥያቄዎቹ ለአንደኛው የሰጠኸው መልስ የተሳሳተ ከሆነ ትክክለኛውን መልስ መስጠት እስክምትችል ክፍለ ትምህርቱን ደጋግመህ አንብበው።

የትምህርቱ ዝርዝር

ሁላችንም የአካሉ ብልቶች ነን

ዓላማ 1 የክርስቶስ አካልን ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መዘርዘር።

ክርስቶስ ራስ ነው

በክርስቶስና በእርሱ በሚያምኑት መካከል ያለውን ግንኙነት መረዳት እንድንችል የሚረዳን ነገር ያስፈልገናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ግልጽ ማድረግ ይችል ዘንድ የተጠቀመው የሰውን አካል ምሳሌ በማድረግ ነበር። እርሱ ክርስቶስ የአካሉ ራስ እንደሆነ ተናገረ። "ራስ" ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን። በአካላችን ላይ "ራስ" ባይኖር ኖሮ ሁለት ነገሮች በእርግጥ እንደሚከሰቱብን የማይካድ እውነት ነው። በመጀመሪያ ራስ ባይኖረን መኖር ስለማንችል የሚያጋጥመን ሞት ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሚያጋጥመን መንቀሳቀስ የማንችልና ለምንም ነገር የማንጠቅም መሆን ነው። ስውነታችን ትርጉም ያለው እንቅስቃሴ ያደርግ ዘንድ ምሪት የሚሰጠው ራሳችን ነው። በተመሳሳይ መንገድ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ ፈቃዱን ያፈጽም ዘንድ አካሉን መምራት

ይፈልጋል። የክርስቶስ አካልም መጠሪያ ስሚ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

(1). ቆላ. 1:15-18 ካነበብህ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ሀ. በዚህ ጥቅስ ጳውሎስ የተናገረው ስለ ማን ነበር?

ለ. የክርስቶስን አካል የሚገልጸው ሌላ ቃል ምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ክርስቶስ አካሉ ለሆኑት ለቤተ ክርስቲያን ራስ መሆኑን ይናገራል። በመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ የሚከተሉትን ጥቅሶች በጥንቃቄ ብታነባቸው ይህንን እውነት ለማረጋገጥ እንድትችል ይረዳሃል። ኤፌ. 1:22-23፤ 4:15-16፤5:23፤ ቆላ 2:19።

አማኞች አካል ናቸው

አካል የሌለው ደማሞ ራስ እንደሌለው አካል ምንም ጥቅም የለውም። ራስ አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን አካልም አስፈላጊ ነው። የክርስቶስ አካል የታነፀው በኢየሱስ ስም በሚያምኑ አማኞች ነው። አንተም አማኝ እንደመሆንህ መጠን የእርሱ አካል ክፍል ወይም ብልት ነህ። ይህም ደማሞ የታወቀ እውነት ነው። ጳውሎስ በሮሜ 12:5 ላይ ስለዚሁ ሲገልጽ፣ "እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን" ይላል።

(2). 1ቆሮ 12:12-13፤ ኤፌ. 4:4፤ 5:29-30፤ ቆላ 1:24 አንብብና በሚከተሉት መግለጫዎች የጎደለውን ትክክለኛ መልስ ሙላ።

ሀ. ክርስቶስ የአካሉ ነው።
ለ. ለክርስቶስ አካል የተሰጠው ሌላው ስም ነው።
ሐ. አማኞች የክርስቶስ ናቸው።

እያንዳንዱ አማኝ የአካሉ ብልት ነው

የክርስቶስ አካል ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት። (1) ራስና (2) ብዙ ብልቶች ናቸው። ሥጋዊ አካላችን አንድ ብቻ ሳይሆን ብዙ ብልቶች አሉት። እጃችን፣ እግራችን፣ ጣቶቻችን፣ ልባችን፣ ወዘተ ሁሉም የአካላችን ልዩ ልዩ ክፍሎች ናቸው። የክርስቶስም አካል እንደዚሁ ልዩ ልዩ ክፍሎች አሉት። እያንዳንዱ አማኝ የአካሉ ክፍል ነው። ይህም ማለት በዓለም ውስጥ የሚኖሩ አማኞች እያንዳንዳቸው የአካሉ ክፍል ወይም ብልት ናቸው። ጳውሎስ እንደተናገረው፣ "አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለምና" (1ቆሮ 12:14)። ከማንኛውም ዘር፣ ቀለም፣ መልክዓ ምድር ወይም አገር የተወለዱ ሕዝቦች ሁሉ ክርስቶስን የሚያምኑ ከሆኑ የዚህ አካል ክፍል ናቸው።

(3). የክርስቶስን አካል ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ከገለፅክ በኋላ አንተ ከምትገኝበት ክፍል አንፃር ይህን (+) ምልክት አድርግበት።

ሀ. _____
ለ. _____

(4). ትክክለኛውን መልስ ክበበው። አንደ ሥጋዊ አካላችን ሁሉ የክርስቶስም አካል _____አለው።

ሀ. አንድ ብልት ለ. ብዙ ብልቶች

እያንዳንዱ ብልት አስፈላጊ ነው

ዓላማ 2 በክርስቶስ አካል ውስጥ እያንዳንዱ ብልት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ መማለጽ።

እያንዳንዱ ብልት የአካል ክፍል ነው

የእግርህ አውራ ጣት ከሰውነትህ ጋር ካልተያያዘ ምን ማድረግ ይችላል? ከአካልህ ተቆርጦ ከወደቀ ከመበስበስና አፈር ከመሆን ሌላ ምንም ሊጠቅም አይችልም። አውራ ጣትህ ከሌለ ሰውነትህ ፍጹም ሊሆን ስለማይችል የለውነትህ አስፈላጊው ክፍል መሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ነው። ብልቶች ሁሉ ተሟልተው የማይገኙበት አካል ጎደሎ ከመሆኑም በላይ ሊያደርጋቸው የሚችለው ነገሮችም የተወሰኑ ናቸው። ለምሳሌ፣ አንድ እግር ብቻ ያለው ሰው በሩጫ እሽቅድምድም መሳተፍ አይችልም። ዓይኖች የሌሉትም ሰው የቀረበለትን ጽሑፍ ማንበብ እንደማይችል ሁሉ፣ እጆች የሌሉትም ሰው ከዛፍ ላይ መውጣት አይችልም።

በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ብልት ለጌታ ኢየሱስ አስፈላጊ ነው። ጳውሎስ ስለዚሁ ሲገልጽ፣ "እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ" ይላል (1ቆሮ 12:27)። በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ብልት የአካሉ ክፋይ ነው በሚለው ሃሳብ ብናቀርበው ምናልባት ይህንኑ ሃሳብ ሰፋ አድርገን ለመመልከት እንድንችል ይረዳን ይሆናል። አውራ ጣትህ የለውነትህ አንድ ቅንጣት ወይም ክፋይ እንደሆነ ሁሉ፥ በክርስቶስ አካል ብልት የሆነውም እንደዚሁ በአካሉ ውስጥ ቅንጣት ወይም ክፋይ ነው።

(5). 1ቆሮ 12:15-26 አንብብ። እውነት ከሆነው ከእያንዳንዱ መግለጫ አንባር ያለውን ፊደል ክበበው።

ሀ. አማኞች ሁሉ የክርስቶስ አካል ክፍል ናቸው።
ለ. የክርስቶስ አካል ብልቶች ሁሉ የተለያዩ ናቸው።
ሐ. የክርስቶስ አካል ብልቶች እርስ በርሳቸው አይፈላለጉም።

እያንዳንዱ ብልት የራሱ ተግባር አለው

የእግራችን አውራ ጣቶችና ጆሮቻችን አገልግሎት ቢኖራቸውም የሚሰጡት አገልግሎት ተመሳሳይ ሳይሆን የተለያየ አገልግሎት ነው። ዓይኖቻችንና አሞሮቻችንም እንደዚሁ የሚሰጡት አገልግሎት የተለያየ ነው። የክርስቶስም አካል እንደዚሁ ሁሉም አባላት ተመሳሳይ አገልግሎት አይሰጡም። እያንዳንዱ የአካል ክፍል ግን ከሌሎቹ የተለየ የራሱ የሆነ ተግባር አለው። *ተግባርም* ስንል "የተለየ ሥራ" ማለታችን ነው። የዓይን ተግባር ማየት ሲሆን፣ የጆሮ ተግባር ደግሞ መስማት፣ የአፍ ተግባር ደግሞ መናገር ነው።

ስለ እግራችን አውራ ጣት እንደገና ብንነጋገር ምናልባት በሳሚማችን ውስጥ ተደብቆ ስለማይታይ ላናስበውና ላናስታውሰው እንችል ይሆናል። ቢሆንም የራሱ የሆነ አስፈላጊ ተግባርና ድርሻ እንዳለው ልንዘነጋው አይገባም። ከሌሎች የእግር ጣቶች ጋር በመሆን አገልግሎቱን ከማበርከቱም በላይ እግራችንን የተሟላ በማድረግ መላው አካላችን ሚዛኑን ጠብቆ እንዲቆም የሚረዳን የእግራችን ክፍል አውራ ጣት ነው። የእግራችን ክፍል አውራ ጣት ከሌለ ታላቅ ጉዳት ሊደርስብን ይችላል። የተቀሩት የአካላችን ክፍሎች በሙሉ የዚህ አውራ ጣታችን ተጠቃሚ ናቸው። እሱ ባይኖር ኖሮ በቀላሉ የምንደናቀፍ እንሆናለን። እንደሚገባ መሮጥ አለመቻል ብቻ ሳይሆን እስከ ማንከስም እንደርሳለን።

የክርስቶስ አካል ብልቶችም በተመሳሳይ መንገድ የእኛው አካል ብልቶች አይነት ናቸው። እያንዳንዱ ብልት የራሱ የሆነ ተግባር አለው፣ በዚህም ምክንያት "ራስ" ለሆነው ክፍልና ለሌሎችም የአካል ክፍሎች አስፈላጊ ነው።

(6). ሮሜ 12:6-8 እና 1ቆሮ 12:18-25 አንብብ። እውነት ከሆነ "እ" ሐሰት ከሆነ ደግሞ 'ሐ' ብለህ ጻፍ።

_____ሀ. የክርስቶስ አካል ብልቶች ሁሉ አንድ ዓይነት ተግባር አላቸው።
_____ለ. ተግባር ማለት አካል ነው።
_____ሐ. እያንዳንዱ ብልት በክርስቶስ አካል ውስጥ የራሱ ተግባር ስላለው ያሉት ብልቶች ሁሉ አስፈላጊ ናቸው።

ራሳችንን ከሌሎች ጋር ልናወዳድር አይገባንም

ዓላማ 3 አንድ አማኝ ራሱን ከሌላ አማኝ ጋር ለምን ማወዳደር እንደማይገባው ሁለት ምክንያቶችን መማለጽ።

ውድድር እግዚአብሔርን ያሳዝናል

የሰውነታችንን ክፍሎች አንዱን ከሌላው ልዩ አድርጎ እንደፈጠረው ሁሉ አኛንም አንዳችን ከሌላው ልዩ አድርጎ አግዚአብሔር ፈጥሮናል። የአግሬ አውራ ጣት በአፍንጫዬ ቦታ ለምን አልሆነም ብለህ ብታጉረመርም አግዚአብሔር ደስ የሚለው ይመስልሃልን? አግዚአብሔር በዚህ ደስ አይለውም። አግዚአብሔር እያንዳንዱን የሰውነታችንን ክፍል እንደፈጠረና የታቀደለትንም ዓላማ ይፈጽም ዘንድ በስፍራው እንዳስቀመጠው እድርገን መቀበል አለብን።

ራሳችንን ከሌሎች የክርስቶስ አካል ክፍሎች ጋር በምናወዳድርበትና እንደነርሱ ባለመሆናችንም በምናጉረመርምበት ጊዜ አግዚአብሔርን እናሳዝናለን። እያንዳንዳችን የሆነውን አንድነሆን ያደረገን፣ ለመላው አካል መታነጽና ለራሱም ክብር ባለንበት ስፍራ ያስቀመጠን አግዚአብሔር እንደሆነ አውቀን ባስቀመጠን ስፍራ ሆነን አገልግሎታችንን በታማኝነት ማበርከቱ ለእያንዳንዳችን የተሰጠ ኃላፊነት ነው።

ስጦታችን ወይም ስጦታዎቻችን ከሌላው ሰው ስጦታ ጋር ተመሳሳይ ባለመሆናቸው ሃዘን ከተሰማን በአግዚአብሔር ላይ ፈራጆች እንደሆንን ከማስመሰሉም በላይ፣ "አግዚአብሔር ሆይ! ያንን ስጦታ ለኔ ያልሰጠኸኝ ለምንድን ነው?" እንደማለት ይቆጠራል። አንተ ራስህ ለሦስት ዓደኞችህ በኑሮ ውስጥ ካላቸው ዝንባሌ ወይም ተሰጥኦ ጋር ተስማሚ የሆኑ ስጦታዎችን ብትሰጣቸውና ከእነርሱ አንዱ ለሌላው የሰጠኸውን ስጦታ ስላልሰጠኸው ቢያጉረመርምብህ ምን ይሰማሃል? በጣም እንደምታዝን የታወቀ ነው፣ ታዝናለህም።

(7). 1ቆሮ 12:15-18 አንብብ። ራሳችንን ከሌሎች ጋር ማወዳደር እንደ ሌለብን ከዚህ ጥቅስ እንረዳለን። ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መካከል ራሳችንን ከሌሎች ጋር ለምን ማወዳደር እንደማይገባን ከሚገልጸው መግለጫ አንጻር ያለውን ፊደል ክበበው።

ሀ. ራሳችንን ከሌሎች ማወዳደር እግዚአብሔርን ያሳዝናል።
ለ. ራሳችንን ከሌሎች ጋር ማወዳደር የክርስቶስ አካል ክፍል እንድንሆን ያደርገናል።
ሐ. ራሳችንን ከሌሎች ጋር ማወዳደር እኛ ለአካሉ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆንን እንዳልተገነዘብን ይገልጻል።

ውድድር ተስፋ ያስቆርጣል

ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ሰዎች ጋር ራሳችንን ልንመድብ ወይም ልናነጻጽር እንደናርም፣ እነርሱ ራሳቸውን በራሳቸው ሲመዝኑና ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር ሲያነጻጽሩ አስተዋዮች አይደሉም (2ቆሮ. 10:12 አ.መ.ት)።

ራሳችንን ከሌሎች ጋር የምናወዳድር ከሆነ ሁለት ነገሮች ይከሰታሉ። ከነዚህም የመጀመሪያው፣ ስጦታችን እንደ ሌላው ሰው ስጦታ ስላልሆነ ተስፋ መቁረጥ ደረጃ ላይ እንደርሳለን። እኛ ያለን ስጦታ እንደ ሌላው ሰው ስጦታ ሁሉ አስፈላጊ ላይመስለን ይችላል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የኛ ስጦታ ከሌላው ሰው ስጦታ የተሻለ ነው ብለን የምንገምት ከሆነ ወደ ኩራትና ትዕቢት ሊመራን ስለሚችል ሌላውን ተስፋ ከማስቆረጣችንም በላይ ስጦታችን ዓላማውን ይስታል።

እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን አስፈላጊ የሆኑ ስጦታዎች እንደሰጠን ማወቁ ጠቃሚ ነው። የሚሰቴን "ሚማ አድርጌ ብሄድ በጣም ያሳፍራል፣ ምጽት አደለማኝም። በእርግጥ "ሚማዎቹ ለእኔ ተስማሚ ሊሆኑ አይችሉም። ሚስቴም ብትሆን የእኔን ለማድረግ ብትሞክር አይስማማትም። የእርሷ "ሚማ ለእርሷ ብቻ እንደሚስማሙ ሆነው የተሠሩ ናቸው። እንደዚሁም እግዚአብሔር ለአንተ የሰጠህ ስጦታ ለአንተ ትክክለኛ ስጦታ ነው። ለሌሎች ለአካሉ ብልቶች የሰጣቸው ስጦታዎችም ለእነርሱ ትክክለኛ ስጦታዎች ናቸው። ታዲያ እኛ የተሰጠንን ስጦታዎች ለሌሎች ከተሰጣቸው ስጦታዎች ጋር ማነጻፀሩ ወይም ማወዳደሩ ምን ይጠቅማል?

እዚህ ላይ አንድ በተጨማሪ አስፈላጊ የሆነ ነገር አለ። "...ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፣ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን" በማለት ጳውሎስ በሮሜ 12:5 ላይ ይናገራል። ሁላችንም በዚያው አንድ አካል ውስጥ ስላለን ስጦታዎቻችንን የምናወዳድርበት ምንም ምክንያት አይኖረንም። እያንዳንዳችን የሌሎች ስጦታዎች ተጠቃሚ ነን። እግራችንን ከአፋችን ጋር ለማወዳደር ለምን እንሞክራለን? አያመሳስሉም፣ ደግሞም ተመሳሳይ ተግባር የላቸውም። ተመሳሳይ ተግባር ባይኖራቸውም ሁለቱም አስፈላጊዎችና ለአንድ ዓላማ አስተዋፅኦ የሚደርጉ ናቸው። እግራችን ምግባችን ወደሚገኝበት ይመስደናል። አፋችን ደግሞ ምግቡን ይመገባል። በዚህም ተጠቃሚ የሚሆነው መላው አካላችን ነው። በክርስቶስ አካል ውስጥ በሚገኙ ብልቶችም የሚካሄደው አገልግሎት ይህንኑ የመሰለ ነው።

(8). 1ቆሮ 12:21-27 አንብብ። የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች የተሟሉ ለማድረግ የሚያስችለውን ቃል ወይም ቃላት በባዶ ሥፍራዎች ላይ ሙላ።

ሀ. ራሳችንን ከሌሎች ጋር በምናወዳድርበት ጊዜ _____እና_____ ተስፋ ልናስቀርጥ እንችላለን።
ለ. ለእኛ አስፈላጊ የሆኑትን ስጦታዎች የሚሰጠን _____ ነው።
ሐ. ሁላችንም የአንደ _____ አስፈላጊ ብልቶች በመሆናችን ራሳችንን ከሌሎች ጋር ማወዳደር አይገባንም።

በስጦታዎቻችን ታማኝ ልንሆን ይገባል

ዓላማ 4 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ምንጭ ለመግለጽ።

ዓላማ 5 የእግዚአብሔርን ስጦታዎች እንዴት መጠቀም እንደሚገባ ለመግለጽ።

ስጦታዎቻችንን ለደቱን ልናውቃቸው ይገባል

የነርስቶስ አካል ብልቶች እንደመሆናችን መጠን ልናከናውነው የሚገባን መንፈሳዊ አገልግሎት አለ። እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሲያዘጋጀን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ስጦታዎችን ለጥቶን ይሆናል። አያንዳንዱ ብልት ቢያንስ ቢያንስ አንድ ስጦታ አለው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ስጦታዎች በተጠቀሱባቸው ስፍራዎች ሁሉ ስጦታዎች በአካሉ ለሚገኙ ብልቶች እንደተሰጡ ተገልጿል ማለት ይቻላል።

እነዚህ ስጦታዎች የተሰጡን በወላጆቻችን ወይም በአስተማሪዎቻችን አያደለም። ማንም ሰው ስጦታዎችን የመስጠት ኃይል የለውም። እንዲሁ በተፈጥሮአችን ያገኘናቸው ችሎታዎችም አይደሉም።

ችሎታዎች ሰዎች ሲወለዱ ጀምሮ አብረዋቸው ያደጉ ናቸው። ሰዎች የተለያዩ ችሎታዎች አሉአቸው። አንዳንዶች እነዚህን ችሎታዎች ስጦታዎች ብለው ይጠሩአቸዋል። ሆኖም ከአጋ ስጦታዎች ጋር ተመሳሳይ አያደለም። ብዙ አማኝ ያልሆኑ ሰዎች ችሎታዎች አሉአቸው። ለምሳሌ ያህል አንድ አማኝ ያልሆነ ሰው የሙዚቃ ችሎታ ይኖረዋል። አለበለዚያ ደግሞ በአደባባይ ንግግር የማድረግ ችሎታ ይኖረዋል። ሆኖም እነዚህ የአጋ ስጦታዎች አይደሉም።

የአጋ ስጦታ ከአንድ ምንጭ ብቻ ይገኛል። የሚገኘውም ከእግዚአብሔር ብቻ ነው። ያዕቆብ ስለዚሁ ሲገልጽ፣ "በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መሰወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ" (ያዕ 1:17) ይላል።

(9). ሮሜ 12:6፤ 1ኛ ቆሮ 12:7፣11፤ 1ጴጥ 4፤10 አንብብ። ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መካከል እውነተኛ በሆነው አንባር ያለውን ፊደል ክበብው።

ሀ. ከእግዚአብሔር ልጆች ጥቂቶቹ ብቻ የአጋ ስጦታ አላቸው።
ለ. የአጋ ስጦታዎች የሚሰጡን ከእግዚአብሔር ነው።
ሐ. የአጋ ስጦታዎችና ሰብዓዊ ችሎታዎች አንድ ዓይነት ናቸው።
መ. አስተማሪዎቻችን የዐጋ ስጦታዎችን ሊሰጡን ይችላሉ።

በስጦታዎቻችን ልናገለግል ይገባል

እግዚአብሔር በሚሰጠን ስጦታዎች ሁሉ ዘንድ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል አንድ ቀላል መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ይሰጠናል። መመሪያውም፣ "በከንቱ ተቀበላችሁ፥ በከንቱ ስጡ" የሚል ነው (ማቴ 10:8)። ይህንን መመሪያ ከአጋ ስጦታዎች ጋር ስናነጻጽረው የአካሉ ብልቶች የተቀበሉአቸውን ስጦታዎች ማዋል ያለባቸው ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ስጦታዎቹ ለተሰጡባቸው ዓላማ ብቻ ሊሆን ይገባል ማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜ አማኞች በስጦታዎቻቸው ሳይጠቀሙባቸው ይቀራሉ። አንዳንድ ጊዜም ለራሳቸው ፈቃድና ፍቅር በንደለው ሁኔታ ሊጠቀሙባቸው ይሞክራሉ። ሆኖም በእንደዚህ ዓይነት አሠራር የስጦታዎቹ ዓላማ ሊከናወንና ግብ ሊመታ አይችልም።

ስለሆነም፦

1. እያንዳንዱን ስጦታ ሊታቀደበት ዓላማ መጠቀም፣
2. የስጦታው አጠቃቀም በፍቅር የተገዛ እንዲሆን ማድረግ የእያንዳንዱ አማኝ ተግባር ሊሆን ይገባል።

ጴጥሮስ ስለዚሁ ሲገልጽ፣ "...ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የአጋን ስጦታ እንደተቀበላችሁ መጠን በዚያው ሄጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ" ይላል (1ጴጥ 4:10)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እንድ ሰው ተግባር በሚገልጽበት ጊዜ "መጋቢነት" በሚለው ቃል ይጠቀማል። መጋቢነት ለሌሎች ጉዳይ ትኩረት መስጠትና መከታተል ማለት ነው። እንደ አማኞች የመጋቢነት መንፈሳዊ ስጦታ ተሰጥቶናል። ይህም ማለት በተሰጠን የአጋ ስጦታ ላይ ልናተኩርና ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት ልንጠቀምበት ይገባል ማለት ነው። ለመጋቢዎች ደግሞ የተሰጠ ማሳጽ መመሪያ አለ፣ መመሪያውም፣ "..... በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈለጋል" የሚል ነው (1ቆሮ 4:2)። የአጋ ስጦታዎችን በታማኝነትና በትክክለኛው መንገድ መጠቀም ለሰፈው ነብርን ለነርስቶስ አካልም በረከትን ያስገኛል።

ፍቅር የአጋ ስጦታዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም የሚያስችል ቁልፍ ነገር ነው። ፍቅር እስከተለያቸው ጊዜ ድረስ የአጋ ስጦታዎች ዓላማቸውን ግብ መምታት አይችሉም። ወደ ገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ጳውሎስ እንደተናገረው "በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ..... አይጠቅምምና" (ገላ 5:6)።

(10). እውነት ከሆነው መግለጫ አንፃር ያለውን ፊደል ክበበው።

ሀ. የጸጋ ስጦታዎችን ሌሎችን ለማነፅ ልንጠቀምባቸው ይገባል።
ለ. መጋቢነት ማለት ለራሳችን ጉዳይ ትኩረት መስጠት ነው።
ሐ. የተሰጡንን የጸጋ ስጦታዎች በታማኝነት በምንጠቀምበት ጊዜ እግዚአብሔርን እናከብራለን።
መ. የጸጋ ስጦታዎች ከፍቅር ይልቅ አስፈላጊዎች ናቸው።

(11). እግዚአብሔር የሰጠንን የጸጋ ስጦታ በሚገባ ለመጠቀም ቁልፉ

ሀ. የጸጋ ስጦታ እንዳለህ ሌሎች እንዲያውቁ ማድረግ ነው።
ለ. የራስህን ስጦታ ከጓደኞችህ ስጦታ ጋር ማወዳደር ነው።
ሐ. የጸጋ ስጦታዎችን አጠቃቀም ፍቅር እንዲገዛው ማድረግ ነው።
መ. አንድ ነገር እስከሚሆን ድረስ መጠባበቅ ነው።

በዚህ ወቅት ከ1ኛ ቆሮ 13 ላይ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ቁጥሮች በቃልህ ማጥናት ይገባሃል። ይህንንም ትምህርት መከታተል እየቀጠልክ ስትሄድ የጸጋ ስጦታዎች ፍቅር ሊገዛቸው እንደሚያስፈልግ የሚናገረውን ይህንኑ ምዕራፍ በቃልህ ማጥናትህን ቀጥል።

የሙከራ ፈተና

ይህንን ክፍለ ትምህርት ከከለስህ በኋላ የሙከራ ፈተናውን ውሰድ። ከዚያም መልሶችህን በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት አርም። በትክክል ያልመለስካቸው ጥያቄዎች ካሉ እስተካክል።

እውነት ወይም ውሸት። እውነት ከሆነው መግለጫ አንፃር ባለው ክፍት ቦታ "እ" ሐሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" ብለህ ጻፍ።

1. የክርስቶስ አካል ሁለት ዋና ክፍሎች ራስና እጆች ናቸው።
2. የክርስቶስ አካል ብዙ ብልቶች አሉት።
3. አንዳንድ የአካል ብልቶች ስለማያስፈልጉ አስፈላጊ አይደሉም።
4. በክርስቶስ አካል የሚገኙ ልዩ ልዩ ብልቶች የተለያዩ ተግባሮች አሏቸው።
5. እርስ በርሳችን በምንወዳደርበት ጊዜ ክርስቶስ ደስ ይለዋል።
6. ራሳችንን በክርስቶስ አካል ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ብልቶች ጋር በምናወዳ ድርበት ጊዜ ተስፋ ልናስቆርጣቸው እንችላለን።
7. ሰብአዊ ችሎታዎች የጸጋ ስጦታዎች አደሉም።
8. የጸጋ ስጦታዎች ከኛ ጋር አብረውን የተወለዱ ናቸው።
9. እግዚአብሔር የጸጋ ስጦታዎች የሚሰጠን ለኛ ደስታ ብቻ ሲል አይደለም።
10. መጋቢነት፣ ስጦታዎችን በታማኝነት መጠቀምን ይጠይቃል።
11. የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ዓላማቸውን እንደሚገባ የሚፈጽሙት በፍቅር ስንጠቀምባቸው ነው።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. ሀ. ስለ ክርስቶስ ለ. አማኞች ወይም ቤተ ክርስቲያን

7. ሀ እና ሐ

2. ሀ. ራስ ለ. ቤተ ክርስቲያን ሐ. አካል

8. ሀ. እኛን፣ ሌሎችንም ለ. እግዚአብሔር ሐ. አካል

3. ሀ. ራስ ለ. ብልቶች (+)

9. ሀ. ሐሰት ለ. እውነት ሐ. ሐሰት መ. ሐሰት

4. ለ

10. ሀ. እውነት ሐ. እውነት
ለ. ሐሰት መ. ሐሰት

5. ሀ. እውነት ለ. እውነት ሐ. ሐሰት

11. ሐ

6. ሀ. ሐሰት ለ. ሐሰት ሐ. እውነት

2 እግዚአብሔር ስለ ስጦታዎቹ እንድታውቅ ይፈልጋል

ትምህርት

በመጀመሪያው ክፍለ ትምህርት እግዚአብሔር ለአማኞች ሁሉ ስጦታዎች እንዳሉት ተምረናል። እያንዳንዱ አማኝ ስጦታዎቹን በመጠቀም በኩል እግዚአብሔር ታማኝነትን እንደሚጠብቅበትና እያንዳንዱም ስጦታ የሚያረካ አገልግሎት ይሰጥ ዘንድ አማኙ በፍቅር የተሞላ መሆን እንዳለበትም ተገንዝበናል።

ይህ ክፍለ ትምህርት ስለ ስጦታዎች ግንዛቤ እንዲኖረን ይረዳናል። ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ማወቅ ለአማኙ አስፈላጊ መሆኑን እንረዳለን። ስለ ብዙ ዓይነት የጸጋ ስጦታዎችና መላው የአማኞች ሕብረት ስለሚኖራቸው ሚና ግንዛቤ እንድናገኝ ያደርገናል።

በዚህ ክፍለ ትምህርት ደስ የሚያሰኘው ነገር እግዚአብሔር ለአንተ የሰጠህን የጸጋ ስጦታ እንድታውቅ መርዳቱ ነው። የጸጋ ስጦታህን ማወቅህ፥ እንድታዳብረውና ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት መዘጋጀት እንድትጀምር ይረዳሃል።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የማወቅ አስፈላጊነት
- የስጦታዎች አመዳደብ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት በምታጠናቅቅበት ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

- ከጸጋ ስጦታዎች ጋር ባለው ዝምድና የእውቀትን አስፈላጊነት መግለጽ
- የጸጋ ስጦታዎችን በየዓይነታቸው መመደብ

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

ክፍለ ትምህርቱን ካነበብክ በኋላ የተለየ አስፈላጊነት እንዳላቸው የሚሰመሩትን ቃላት ወይም ሐረጎች አስምርባቸው።

2. 1ቆሮ 13ን በቃልህ ማጥናትህን ቀጥል። የዚህን ምዕራፍ ቁጥር አንድና ሁለትን ድምፅህን ከፍ አድርገህ በቃልህ ከልለው። ከዚያም በኋላ ቁ. 3 እና 4ን በቃልህ አጥና።

3. በተለየ የማስታወሻ ደብተር ሦስቱን የጸጋ ስጦታዎች አመዳደብ የሚያሳዩ ዝርዝር አውጣና በክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ላይ በተገለፀው ዓይነት ከየምድቡ ጋር የሚዛመዱትን የጸጋ ስጦታዎች መላ።

4. የክፍለ ትምህርቱን እያንዳንዱን ደረጃ በመከተልና የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን በመሥራት ያደርግኸውን እርምጃ ገምግም።

5. በክፍለ ትምህርቱ በስተመጨረሻ ያለውን የመከራ ፈተና ስራ። የሰጠሃቸውንም መልሶች ትክክለኛነት አረጋግጥ። ትክክለኛውን መልስ ማወቅህን እርግጠኛ ለመሆን በስህተት የመለስካቸውን መልሶች ወደ ክፍለ ትምህርቱ በመመለስ ከልሳቸው።

የትምህርቱ ዝርዝር

የማመቅ አስፈላጊነት

ዓላማ 1 ስለ ጸጋ ስጦታዎች ማወቅ ለአማኙ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ በአንድ በአጭሩ ለመግለጽ።

እውቀት እምነትን ያስገኛል

እምነት በጸጋ ስጦታዎችና ባጠቃቀማቸው መካከለኛ ክፍል ላይ የሚገኝ ነው። የጸጋ ስጦታዎች መሆናቸው ወይም ከመንፈስ ቅዱስ መስጠታቸው የእምነትን አስፈላጊነት ያሳያል። እምነት አማኞች ያደርገናል። እምነት በተሰጡን ስጦታዎች አማካኝነት እንደ አማኞች ጠቃሚዎች መሆናችንን ያረጋግጣል።

እውቀት ---> እምነት ---> የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

ሰዎች እምነትን የሚያገኙት እንዴት ነው? መልሱ ቀላልና እርግጠኛም ነው። እምነት የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ውጤት ነው። ስለሆነም በአንዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እውቀት አማካኝነት እምነት እውን ይሆናል። በሮሜ 10:14 ላይ ጳውሎስ ይህንኑ ጉዳይ ሲገልጽ "እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል?" በማለት ይናገራል። የወንጌልን መልዕክት በመስማት የመጣንን እውቀት እንቀበላለን። አንድ ጊዜ እውቀትን ከተቀበልን እምነት በሕይወታችን ይፈጠራል።

በኤፌሶን ስለ ነበሩ ደቀ መዛሙርት ብንመለከት ጳውሎስ እነዚህን ደቀ መዛሙርት ባገኛቸው ጊዜ፣ "ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" በማለት ጠየቃቸው። እነርሱም፣ እነኳ "አልተቀበልንም፣ መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም" ብለው መለሱለት (የሐዋ. 19:2)። ሰምተው ስለማያውቁ አያውቁም ነበር። ባለማወቃቸው ምክንያት ደግሞ ሊያምኑ አልቻሉም።

ከዚያ በኋላ ጳውሎስ ሊያስተምራቸው ጀመረ። በእርሱም ትምህርት አማካኝነት እውቀትን አገኙ። አንድ ጊዜ እውቀትን ካገኙ እምነት በልባቸው ይወለዳል። ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለመቀበልና ምንነታቸውን ለመለየት እንዲሁም ውጤታማ በሆነ መንገድ በስጦታዎቹ ለማገልገል የመጀመሪያው እርምጃ ሊሆን የሚገባው ስለ ስጦታዎቹ ማወቅ መሆኑን እንረዳለን። ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እስካላወቅን ድረስ በግል ሕይወታችንና በአገልግሎታችን እግዚአብሔር እንዲኖረን የሚጠበቀውን ሚና ሊጫወቱ አይችሉም።

(1). 1ቆሮ 12:1፤ 14:36፤ የሐዋ 19:1-7 እና ሮሜ 12:6 አንብብ። ከዚያም ከናንተ በሆነው ስፋራ ትክክለኛውን ቃል በማስገባት የሚከተሉትን መግለጫዎች አጠናቅ።

ሀ. በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና በአጠቃቀማቸው መካከለኛ ስፋራ ላይ የሚገኘው _____ ነው።
ለ. እምነት ለፈጠር የሚችለው _____ ነው።
ሐ. ከዚህ ጥናት ማግኘት የምንፈልገው እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር ስለ _____ ማወቅ ነው።

እውቀት እምነትን ይቆጣጠራል

እውቀት እምነትን ማስገኘት ብቻ ሳይሆን አሠራሩንም ይቆጣጠራል። ይቆጣጠራል ስንልም፣ አጠቃቀሙን አቅጣጫ ያስይዘዋል፣ ደግሞም ድንበር ያበጅለታል ማለታችን ነው። በዚህም ምክንያት እውቀት በተቻለ መጠን ሙሉና እውነተኛ መሆኑ አስፈላጊ ነው። ያለ እውቀት የሆነ እምነት፣ ሙሉና እውነት ባልሆነ መሠረት ላይ እንዲቆም ያደርገዋል።

መሠረት፣ ማለት አንድ ነገር የቆመበት ወይም የታነጸበት ማለት ነው። ትክክለኛ መሠረት የሌለው እምነት ደግሞ በከፊል መሠረት ላይ እንደታነጸ ቤት ነው። ስምሳሌ፣ ብዙ አማኞች የልሳን ስጦታ ለአሁኑ ዘመን የተሰጠ አይደለም የሚል ትምህርት ተምረዋል። ይህንንም እውነት ያልሆነ ትምህርት ስለ ተማሩ ይህንን ስጦታ ለመቀበል ያላቸው እምነት ደካማ ነው።

ሰዎቹ የሚመስላቸው ነገር እንደ እግዚአብሔር ቃል ባይሆንም እንኳን ሊያምኑ የሚችሉት የሚያውቁትን ያህል ነው። እምነታቸው ከእውቀታቸው

በላይ ሊሻገር አይችልም። የእውቀታቸው መሠረት ካልታረመ በስተቀር እነዚህን መሳይ አማኞች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የልሳን ስጦታ ለእነርሱ እንዳልሆነ እያመኑ ይኖራሉ። በዚህም ምክንያት ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሙሉና እውነተኛ እውቀት ማግኘታችን በጣም አስፈላጊ ነው።

(2). ዮሐ 8:30-32 አንብብ። ከሚከተሉት መግለጫዎች ውስጥ እውነት በሆኑት አንጻር ያሰውን ፊደል ክበብ።

ሀ. እውቀት እምነትን ይቆጣጠራል።
ለ. ትክክለኛ እውቀት አስፈላጊ አይደለም።
ሐ. እምነት ከምናውቀው እውቀት በላይ ያሻግረናል።

እውቀት ልምምድን ይወስናል

እውቀት እምነትን የሚያስገኝና የሚቆጣጠረው በመሆኑ እኛን ወደ ልምምድ ሊመራን ይገባል። በአእምሮአችን ውስጥ ሊቀመጥ የሚገባ አንድ ቅደም ተከተል አለ። 1. እውቀት 2. እምነት 3. ልምምድ

ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ካላወቅን እንዲሁ በእምነት ልንቀበላቸው አንችልም። በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እስካላወቅን ደግሞ እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠበቅብን የልምምዳችን አካል ወይም ክፍል አይሆኑም።

እውቀት -------> እምነት -------> ልምምድ

በሐዋ ምዕራፍ 19 ላይ የተገለጸውን የጳውሎስን ልምምድ ከልስ። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው እነዚያ የኤፌሶን ሰዎች ስለ መንፈስ ቅዱስ ባለማወቃቸው ምክንያት ሊያምኑበት አልቻሉም። አሁን ደግሞ እንደምንመለከተው እውቀት ስለጎደላቸውና እምነትም በማጣታቸው እግዚአብሔር እንዲኖራቸው ያቀደላቸውን ልምምድ ሳይለማመዱ ቀርተዋል።

ጳውሎስ ስለ መንፈስ ቅዱስ እንዳላወቁ በተረዳ ጊዜ ሊያስተምራቸው ጀመረ። ማለትም እውቀት እንዲኖራቸው ረዳቸው። የዘያን ጊዜ ሊያምኑበት ያልቻሉትን መናገሩን ካወቁ በኋላ ሊያምኑበት ችለዋል። ባገኙት አዲስ እውቀት ላይ እምነታቸውን ሥራ ላይ ሲያውሉ ፍጹም አዲስ ልምምድ ውስጥ ገቡ። የአዲሱ ልምምዳቸው ጅማሬ ጳውሎስ ካስተማራቸውና ካገኙት አዲስ እውቀት ጋር በቀጥታ ሊያያዝ ይችላል።

ይህ እንግዲህ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ማወቅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንድንገነዘብ ያረዳናል። ያለንን እንደሚገባ አስካላወቅን ድረስ ልምምዳችንም ውስን ይሆናል።

ከዚሁ ጋር አያይዘን ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈላቸውን ብንመለከት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንደነበሩአቸው ይገልጻል። "..... በነገር ሁሉ፣ በቃልም ሁሉ፣ በእውቀትም ሁሉ በእርሱ ባለጠጎች እንድትሆኑ ተደርጋችኋልና። እንደዚህ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ስትጠባበቁ አንድ የጸጋ ስጦታ እንኳ አይጎድልባችሁም" (1ቆሮ ተሰ 1:5-7)። የቆሮንቶስ ሰዎች ስለ እነዚህ የጸጋ ስጦታዎች ያውቁ /እንደነበረና ብዙዎቹም ስጦታዎቹ ላይኖራቸው እንደማይቀር ይገመታል። የሚያስፈልጋቸው ስጦታዎቹን እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው ማወቅ ነበር። "ስለ መንፈሳዊ ነገርም፣ ወንድሞች ሆይ፣ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ" (1ቆሮ 12:1)።

ስለነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ያለውን እውነት ማወቅ ፍሬያማ በሆነ መንገድ እንድንጠቀምባቸው ይረዳናል። ስለ እነርሱ በተቻለ መንገድ መማር ያለብን በዚህ ምክንያት ነው።

(3). ትክክለኛውን ቃል ወይም ቃላት በመጨመር የሚከተሉትን መግለጫዎች አጠናቅቅ።

ሀ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለመቀበል መከተል የሚገባን ትክክለኛው ቅደም ተከተል እውቀት፣ _____ እና _____ ናቸው።
ለ. እምነትን የሚያስገኘውና የሚቆጣጠረው _____ ነው።
ሐ. ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ያለውን እውነት ማወቅ ይበልጥ ፍሬያማ ወደ ሆነ _____ ይመራናል።

የስጦታዎች አመዳደብ

ዓላማ 2 በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ የሚገኙትን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለመዘርዘር።

ዓላማ 3 በአገልግሎት ስጦታዎች፣ በሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎችና በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል ልዩነቱን መግለጽ።

የአገልግሎት ስጦታዎች

መጽሐፍ ቅዱስ በእያንዳንዱ የጸጋ ስጦታዎች ምድብ ውስጥ ስለሚገኙት ስጦታዎች የተሟላ ዝርዝር አያሰጠንም። አንዳንድ ጊዜ ምድቦችን በእንድነት የሚቀላቅላቸው ይመስላል። ይህም አደራረግ የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ እርስ በርሳቸው የተዛመዱ ናቸው የሚል ይመስላል። ቢሆንም ለዚህ ጥናታችን ዓላማ የጸጋ ስጦታዎችን በሦስት ክፍል መክፈሉ ይረዳናል። እያንዳንዱም ምድብ የራሱ ዝርዝር ይኖረዋል። በአንድ ምድብ ውስጥ የሚገኙት ስጦታዎች ስለሚመሩራሱ በሌላ ምድብ ውስጥ ከሚገኙት አንዳንድ ስጦታዎች ጋር ፍጹም የሚመሳሰሉ ይመስላሉ። ስጦታዎች ሁሉ የሚሰጡት በእግዚአብሔር ስለሆነና ለአንድ የጋራ ዓላማም ማለትም

ለእግዚአብሔር ክብር አማኞች ሁሉ የሚገኙበትን አካል ለማነጽ ስለሚውሩ ይህ ሊያስጨንቀን አይገባም።

የመጀመሪያው ምድብ አማኞች በሚገኙበት አካል ውስጥ ከሚኖረን ከፍተኛ የኃላፊነት አገልግሎቶች ጋር የተያያዙትን ስጦታዎች የሚጨምር ነው። ጳውሎስ ይህንን ዝርዝር በኤፌሶን መልዕክቱ ውስጥ አቅርቦልናል። "ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን ስለዚህ... ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ" ይላል። "..... እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ ሌሎቹም ነቢያት፣ ሌሎችም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ...." (ኤፌ. 4:7-8፤11)። በአገልግሎት ስጦታዎች ምድብ ስር ሊሰፍር የሚገባው ዝርዝር እንደሚከተለው ነው።

1. ሐዋርያት 2. ነቢያት 3. ወንጌላውያን 4. እረኞች 5. አስተማሪዎች

እንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን፣ እረኞችና አስተማሪዎች ተጣምረው አንድ የአገልግሎት ስጦታ እንደሆኑና በአንድነት አስተማሪ - እረኞች ተብለው እንደሚጠሩ ይናገራሉ። ይህንን በሚከተለው ክፍል ትምህርት ሰፋ አድርገን እንመለከተዋለን። በሚቀጥለው ክፍል ትምህርት በተጨማሪ ስለ እያንዳንዱ ስጦታ አጠቃቀም በደንብ መማር እንጀምራለን።

ሆኖም ስለ እነዚህ የአገልግሎት ስጦታዎች አጠቃላይ ዓላማ አሁን መመልከት የሚረዳን ይሆናል። ይህንንም አጠቃላይ ዓላማ ጳውሎስ በኤፌሶን 4:12 ላይ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል። "..... ቅዱሳን አገልግሎትን ስለመሥራትና ስክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ"

(4) 1ኛቆሮ 12:27-30 አንብብ። እውነተኛ ከሆነው ከእያንዳንዱ መግለጫ አንባር ያለውን ሬዲል ክበቡ።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ በእያንዳንዱ ስጦታ ምድብ ስር ያሉትን ትክክለኛ የስጦታዎች ዝርዝር በሙሉ ያቀርባል።
ለ. የጸጋ ስጦታዎች እርስ በርሳቸው ተወራራሽ ይመስላሉ።
ሐ. በአንዱ የጸጋ ስጦታ ምድብ ውስጥ የሚገኙት የስጦታዎች ዝርዝር በሌላው ምድብ ውስጥ ካለው ዝርዝር ጋር ሊመሳሰሉ ይችላሉ።
መ. የጸጋ ስጦታዎች በሙሉ የሚሰጡት ከእግዚአብሔር አይደለም።
ሠ. የአገልግሎት ስጦታዎች የሚባሉት በልዩ ልሳን መናገር፣ እምነትና ተዓምራትን ማድረግ ናቸው።
ረ. እረኞችና አስተማሪዎች፣ አስተማሪ- እረኞች ተብለው ዝርዝር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።

ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች

ከሦስቱ የጸጋ ስጦታ ምድቦች ውስጥ ከዚህ ቀጥለን የምንመለከተው ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች የተባሉትን ይሆናል። በዚህ ምድብ ውስጥ የሚካተቱት ስጦታዎች የትኞቹ እንደሆኑ ከመለየታችን በፊት ሦስቱን የጸጋ ስጦታ ምድቦች ለመከለስ ያህል እንደገና መለስ ብለን እንመልከታቸው።

1. የአገልግሎት ስጦታዎች
2. ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች
3. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች በሚለው ምድብ ስር ያሉት ስጦታዎች በሙሉ በሮሜ መልዕክት ምዕራፍ 12 ወይም በ1ኛ ቆሮ ምዕራፍ 12 ላይ የተጠቀሱት ናቸው። እነዚህ ስጦታዎች እንደ አገልግሎት ስጦታዎች ወይም እንደ አንዳንድ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በቀላሉ ተለይተው ላይታወቁ ይችላሉ። ሆኖም ይህ ሁኔታ ስጦታዎቹ አስፈላጊ እንዳልሆኑ አያስገነዝበንም። ስጦታዎቹ በየበኩላቸው በክርስቶስ አካል ውስጥ አንድ የተለየ ተግባርን ያከናውናሉ። ለምሳሌ እስኪ ስለ ልብህ አስብ። መጠኑ ትንሽ ነው፣ አይታይም ደግሞም አይናገርም። ታዲያ እንዲህ መሆኑ አስፈላጊ ያለመሆኑን ይገልጻል? ይህ ሊሆን አይችልም። ልብህ ከሌለ እጆችህ፣ እግሮችህ፣ ራስህ የቀሩትም የአካላትህ ክፍሎች በየበኩላቸው ተግባራቸውን በሚገባ ሊያከናውኑ አይችሉም።

ከአካላችን በጣም ታናሽ የሆነው ክፍል እንኳን አገልግሎት ስላለው ለመላው አካል መታነፅ አስተዋፅኦ ያደርጋል። ትንሽ የሆነው ይህ የአካል ክፍል ሊታይ ወይም ላይታይ ይችላል። ሆኖም አስፈላጊ ነው የሚያሰኘው አካል ውስጥ ተገኝቶ እንዲያከናውን የሚጠበቅበትን ዓላማ ያከናውናል። የአካሉ ክፍል ከጎደለ ያ አካል ጤናማ አይሆንም፣ ደግሞም ተግባሩን ማከናወን አይችልም። ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች፣ መላው አማኞች አካል ከሆኑበት ጋር ሲነጻጸር ስለ ታናሹ የአካል ክፍል የተነገረው ምሳሌ እውነት ነው።

ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች የምንላቸው በዚህ ምድብ ውስጥ የሚጠቃለሉት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

1. አገልግሎት
2. ማስተማር
3. መምከር
4. መለገስ
5. መግዛት(ማስተዳደር)
6. ምሕረት ማድረግ
7. እርዳታ

(5). ሮሜ 12:6-13፣ 1ቆሮ 12:22-25 አንብብ። በሚከተሉት መግለጫ ሀረፍተ ነገሮች ውስጥ የጎደለውን መላ።

ሀ. ሦስቱ የስጦታዎች ምድብ _____ እና _____ ናቸው።
ለ. አንድን ስጦታ አስፈላጊ የሚያደርገው የተሰጠበትን _____ ማገልገሉ ነው።
ሐ. ከሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች ሦስቱ _____ እና _____ ናቸው።

(6). ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች በሚል ምድብ ስር የዘረዘርናቸው የአገልግሎት ስጦታዎች አስፈላጊ የሆኑበት ምክንያት፦

ሀ. በቀላሉ ስለምንረዳቸው ነው።
ለ. የተፈለጉበትን ዓላማ ስለሚያገለግሉ ነው።
ሐ. አስፈላጊ የአገልግሎት ስጦታዎች መሆናቸው በቀላሉ ስለሚታወቅ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

የአጋ ስጦታዎችን ሁሉ የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው። ሌሎች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የተባለውን የስጦታ ምድብ ስንመሰክት ደግሞ ስጦታዎቹ የተሰየ ልዕለ ተፈጥሮአዊ አሠራር እንዳላቸው እንረዳለን። "ልዕለ ተፈጥሮአዊ" የሚለው ቃል የሁለት ቃል ቅንጅት ነው። 1. "ልዕለ" ማለት "ከላይ የሆነ" ማለት ነው 2. "ተፈጥሮአዊ" ማለት ደግሞ "የተለመደውን ስብዓዊ ወይም ልማዳዊ አሠራር የተከተለ" ማለት ነው። "ልዕለ ተፈጥሮአዊ" የሚለው ቃል ከሰው ባሕርይ በላይ የሆነውን የእግዚአብሔርን አሠራር ያመሰክታል። ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች "ልዕለ ተፈጥሮአዊ" ናቸው ስንል ምንጫቸውና የንያላቸውም መገኛ እግዚአብሔር ነው ማለታችን ነው።

ለምሳሌ, ያህል ስለ ልሳን ስጦታ ብናስብ ከልምምድ ወይም ከማንዛቤ ባገኘነው መረጃ መሠረት አንድ ሰው ቋንቋ የመማር ችሎታ አለው እንላለን። ነገር ግን ይህን መሳይ ችሎታ ያለው ሰው ያልተማረውን ቋንቋ ይናገራል ብለን አንጠብቅም። ሆኖም በልዩ ልሳን የመናገር ችሎታ ከተሰጠው ተምሮት የማያውቀውን ቋንቋ መናገር ይችላል። በዚህም ምክንያት ይህ ሰው ልዕለ - ተፈጥሮአዊ ስጦታ አለው እንላለን። ከእግዚአብሔር ዘንድ በተገኘ ልዩ ችሎታና ኃይል አማካኝነት በልዩ ልሳን መናገር ይችላል።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሙሉ ልዕለ - ተፈጥሮአዊ ናቸው። ይህም ማለት በስብአዊ መንገድ ሊከናወኑ አይችሉም ማለት ነው። ችሎታዎች ሁሉ የሚገኙት ከእግዚአብሔር በመሆኑ ስብአዊ ችሎታ የሚባል ነገር የለም። ሆኖም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሚባሉት ከምናውቃቸው ከማንኛውም ስጦታዎች የተለዩ ስጦታዎች ናቸው።

በዚህ ምድብ ውስጥ የሚጠቃለሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. የጥበብ ቃል
2. የእውቀት ቃል
3. እምነት
4. የፈውስ ስጦታዎች
5. ተዓምራት ማድረግ
6. ትንቢት
7. መናፍስትን መለየት
8. በልዩ ልሳን መናገር
9. ልዩ ልሳን መተርጎም

(7). በ1ቆሮ 12 መሠረት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ የሚለጡት ነው።

ሀ. በአማኞች
ለ. በእግዚአብሔር
ሐ. በአስተማሪዎች
መ. በሐዋርያት

(8). በጥናታችን እንደተመለከትነው "ልዕለ-ተፈጥሮአዊ" ማለት _____ነው።

ሀ. ሰብአዊ ችሎታ
ለ. የምንማረውና በልማድ የምናገኘው
ሐ. ከተለመደው ከተፈጥሮአዊ አሠራር በላይ የሆነ

(9). በሰዎች ዘንድ ባልታወቀ ስማያዊ ቋንቋ መናገር የሚገኘው _____ነው።

ሀ. ለአንድ የተለየ ዓላማ ከእግዚአብሔር በሚሰጥ ስጦታ አማካኝነት
ለ. ከራሳችን ሰብአዊ ችሎታዎች
ሐ. አንድን የተፈጥሮ ሕግ ከማጥናት

(10). እውነት ከሆኑት መግለጫዎች አንጻር ያሉትን ፊደሎች ክበብ

ሀ. የአገልግሎት ስጦታዎችና ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሰየት ያሉ ናቸው።
ለ. ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች አስፈላጊ አይደሉም።
ሐ. አማኞች አካል በሆኑባት ቤተ ክርስቲያን የሚያከናውኑት ተግባር ስላለ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሙሉ ለእኛ አስፈላጊ ናቸው።

(11). ከዚህ በታች በርከት ያሉ የአጋ ስጦታዎች ተዘርዝረዋል። ከተዘረዘሩት የአጋ ስጦታዎች አንጻር ባለው ባዶ ስፍራ ስጦታው የአገልግሎት ስጦታ ከሆነ "አስ"፥ ስጦታው ሌላ የአገልግሎት ስጦታ ከሆነ፥ "ሌአስ" ስጦታው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ከሆነ "መቅስ" የሚሉትን ቃሎች በባዶ ቦታው ላይ ጻፍ።

___ሀ. ትንቢት
___ለ. እረኞች
___ሐ. ልሳን
___መ. ልግስና
___ሠ. እምነት
___ረ. አርዳታ
___ሰ. ሐዋርያት
___ሸ. የፈውስ ስጦታ
___ቀ. አስተማሪዎች
___በ. መምከር

የመከራ ፈተና

አጭር መልሶች። ለሚከተሉት መግለጫዎች የጎደሉትን ቃላቶች በቀረበው ባዶ ስፍራ በመሙላት አጠናቃቸው።

1. የአጋ ስጦታዎችን በሚመለከት ጥንቃቄ እንድታደርግ በዚህ ክፍለ ትምህርት የተለጡት ሦስቱ መመሪያዎች ምንና ምን ናቸው?

ሀ. _____
ለ. _____
ሐ. _____

2. ከአጋ ስጦታዎች አጠቃቀም ጋር በተያያዘ እውቀት ጎ ሚያደርጋቸውን ሦስት ነገሮች ጻፍ።

ሀ. _____
ለ. _____
ሐ. _____

3. መጽሐፍ ቅዱስህን እየተመለከትህ አምስቱን የአገልግሎት ስጦታዎች ዘርዝር፣ የሚገኙበትንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጥቀስ።

ሀ. _____ መ. _____
ለ. _____ ሠ. _____
ሐ. _____ ጥቅስ. _____

4. አራት ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎችን ዘርዝር።

ሀ. _____ ሐ. _____
ለ. _____ መ. _____

5. መጽሐፍ ቅዱስን ሳትመለከት ዘጠኙን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ዘርዝር።

ሀ. _____ ረ. _____
ለ. _____ ሰ. _____
ሐ. _____ ሸ. _____
መ. _____ ቀ. _____
ሠ. _____

6. በቃል ባጠናኸው መሠረት 1ቆሮ 13:1-2 ጻፍ።

_____ _____
_____

ምርጫ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ የሆነ አንድ መልስ ብቻ አለ። ከትክክለኛው መልስ አንዳር ያለውን ፊደል ክበብ።

7. ስለ አጋ ስጦታዎች ትክክለኛ የሆነ እውቀት ማግኘት አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም፤

ሀ. እነርሱን በሚመለከት ለምንጠየቀው ጥያቄ መልስ ይኖረናል።
ለ. እምነታችንን ጥሩ መሠረት ያስይዘዋል።
ሐ. ስጦታዎችን በዝርዝር እንድንጠራ ይረዳናል።

8. እምነት የሚገኘው በ_____ ነው።

ሀ. ፍቅር ለ. እውቀት ሐ. ችሎታዎች

9. የኤፌሶን አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ሳይጠመቁ የቀሩት

ሀ. መጠመቅ ባለመፈለጋቸው ነው።
ለ. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለእነርሱ ተገቢ ስላልነበረ ነው።
ሐ. ስለ ጥምቀቱ ሳያውቁ በመቅረታቸው ነው።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

1. ሀ. እምነት ለ. በቃሉ ላይ ባለን እውቀት
ሐ. መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

6. ለ

2. ሀ. እውነት ለ. ሐሰት ሐ. ሐሰት

7. ለ

3. ሀ. እምነት፣ ልምምድ ለ. እውቀት ሐ. ልምምድ

8. ሐ

4. ሀ. ሐሰት መ. ሐሰት
ለ. እውነት ሠ. ሐሰት
ሐ. እውነት ረ. እውነት

9. ሀ

5. ሀ. የአገልግሎት ስጦታዎች፣ ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎችና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

ለ. ዓላማ

ሐ. መምከር፣ መጣዛት(ማስተዳደር)፣ ልግስና፣ ምሕረት ማድረግ፣ ማፍቀርና እርዳታ (ከነዚህ ሦስቱ መልሶች ተቀባይነት አላቸው)

10. ሀ. እውነት ለ. ሐሰት ሐ. እውነት

11. ሀ. መቅሰ
ለ. አስ
ሐ. መቅስ
መ. ሌአስ
ሠ. መቅስ
ረ. ሌአስ
ሰ. አስ
ሸ. መቅስ
ቀ. አስ
በ. ሌአስ

3 ሐዋርያትና ነቢያት

ትምህርት

ባለፉት ሁለት ክፍሰ ትምህርቶች ስለ አጋ ስጦታዎች ግንዛቤ ማግኘት የሚያስችሰንን መሠረት ስንገነባ ቆይተናል። ከስጦታዎች ጋር በተያያዘ ሁኔታ የእውቀትና የእምነትን አስፈላጊነትም ተመልክተናል። ከዚህም በተጨማሪ እውቀታችንና እምነታችን በልምምዳችን ላይ ወሳኝ እንደሆኑና ልምምዳችንንም እንደሚቆጣጠሩ ተገንዝበናል። ይህንን ግንዛቤ ካገኘንና ከስጦታዎች አመዳደብ ጋር በመጠኑ ከተዋወቅን ስለ መጀመያው ምድብ ማለትም "ስለ አገልግሎት ስጦታዎች" ጥናታችንን ለመቀጠል ዝግጁ ያደርገናል።

በዚህ ክፍሰ ትምህርት የሚሰጠውን ትምህርት ማጥናት ስንቀጥል የእነዚህን ስጦታዎች የአገልግሎት ክልልና ተግባር አንድ በአንድ በሚዛባ እንመለከታለን። እንዲሁም እያንዳንዱ ስጦታ አማኞች ሁሉ አባል የሆኑበትን አካል በመገንባት በኩል ታላቅ ሚና እንዴት እንደሚጫወት እንማራለን።

አንተም እንደክርስቲያን ልዩ ልዩ የሆኑትን የአገልግሎት ስጦታዎች ለይተህ የማወቅ ችሎታ እያገኘህ ትሄዳለህ። ከዚህም በላይ መንፈሳዊ አውቀትህ ባደገና በዳበረ መጠን የእግዚአብሔር እጅ በግል ሕይወትህ ሲንቀሳቀስ ይሰማሃል፥ በዚህን ጊዜ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ወደኋላ አትበል።

የክፍለ ትምህርት፥ አከፋፈል

- አንዳንዶች ሐዋርያት እንዲሆኑ ሰጠ
- አንዳንዶችን ነቢያት እንዲሆኑ ሰጠ

የክፍለ ትምህርት፥ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

- የአገልግሎት ስጦታዎችን መግለጽ መቻል
- የእያንዳንዱን የአገልግሎት ስጦታ ተግባር መረዳት
- የአገልግሎት ስጦታዎች ሲያድጉ እንደሚችሉ መገንዘብ

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ይህንን ክፍለ ትምህርት ማጥናት ከመጀመርህ በፊት ኤፌ 4፤1-16ን ሦስት ጊዜ በጥንቃቄ ደጋግመህ አንብበው።

2. በማስታወሻ ደብተርህ በኤፌ 4:11 ላይ ያለውን ቃል ከገለበጥክ በኋላ አምስቱን የአገልግሎት ስጦታዎች አስምርባቸው።

3. የሚያጋጥሙህን የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች ስራ።

4. በክፍለ ትምህርቱ በስተመጨረሻ የሚገኘውን የሙከራ ፈተና መልስ። በትክክል ያልመለስከው ጥያቄ ቢኖር እያንዳንዱን ጥያቄ በትክክል ለመመለስ እስክትችል ወደሚቀጥለው ክፍለ ትምህርት አትሸጋገር። እርዳታ የሚያስፈልግህ ከሆነ ክፍለ ትምህርቱን መለስ ብለህ ተመልከት።

የትምህርቱ ዝርዝር

እንዳንዶች ሐዋርያት
እንዲሆኑ ሰጠ

ዓላማ 1 የጸጋ ስጦታዎች ሰጪ የሆነውን ማወቅና የሐዋርያነትን ተግባር መግለጽ።

የሰጪውን ማንነት ለይቶ ማወቅ

ሰጪው ------> ስጦታው ---------> ተቀባዩ

የስጦታ መሰጠት የሁለት ወገኖችን መኖር ያሳያል። 1). የሰጪውንና 2) የተቀባዩን መኖር ያመለክታል።

የስጦታ አስፈላጊነት በሰጪው ማንነትና በስጦታው ምንነት ላይ የተመሠረት ነው። ዱዊይት ዲ. አይዘንሃወር የአሜሪካ መንግሥት ፕሬዚዳንት በነበሩበት ዘመን፣ የእንግሊዝ ንግሥት አገራቸውን ሊጎበኙ ሲመጡ ፕሬዚዳንቱ ለንግሥቲቱ በእጅ ጥበብ የተዘጋጀ እጅግ በጣም ውብ የሆነ የአበባ ማስቀመጫ አበረከቱላት። ፕሬዚዳንቱ ያንን የአበባ ማስቀመጫ ለማሰራት ዘኒውዮርክ ግዛት ለሚገኘው የመስታወት ሥራዎች ፋብሪካ ከፍተኛ ዋጋ ከፍለዋል። ንግሥቲቱ ከነበሩአቸው ብርቅ ዕቃዎች ይህ የአበባ ማስቀመጫ አንዱ በመሆኑ ታላቅ ግምት እንደሚሰጠው እርግጠኛ መሆን እንችላለን። ይህ የሚሆንበት ሁለት ምክንያቶች ይኖራሉ።

1. ስጦታው የተሰጠው በተከበሩ (አስፈላጊ በሆኑ) ሰው ሲሆን፣
2. ስጦታው ደግሞ ውብና ከፍ ያለ ዋጋ ያለው ነበር።

ከላይ ከተጠቀሰው ምሳሌ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ምክንያት የሐዋርያነት ስጦታም አስፈላጊ ነው። በመጀመሪያ ስጦታውን ከስጠው ማንነት የተነሣ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከስጦታው ምንነት የተነሣ ስጦታው አስፈላጊ ነው። ይህን ሁለተኛውን ምክንያት ወደኋላ ላይ እንመለስበታለን። አሁን "እንዳንዶች ሐዋርያት እንዲሆኑ ሰጠ" ብሎ የተገለፀው ማን እንደሆነ አስቀድመን እንመልከት።

በኤፌ 4:11 ላይ ስለ ሰጪው ሲናገር፣ "እርሱ" በማለት ይጀምራል። እዚህ ላይ "እርሱ" ተብሎ የተጠቀሰው ማን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው። በዚሁ ምዕራፍ ቁ.8 ላይ የሰፈረው ቃል ከመዝ 68:18 የተወሰደ መሆኑን ይገልጽልናል። በቁ.7 ላይ ደግሞ ከሚከተለው ግልጽ የሆነ መግለጫ ላይ የሚያደርሰን ቃል፣ "..... እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን" ይላል። ከዚህም በመነሣት ክርስቶስ የአገልግሎት ስጦታዎች ሰጪ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን። ምዕራፉን ጠለቅ ብለን ማጥናት ስንቀጥል ስለ ክርስቶስ የስጦታዎች ሰጪነት በይበልጥ ለመረዳት እንችላለን።

(1). ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት እውነተኛ መግለጫዎች አንፃር ያለውን ፊደል ክበብ።

ሀ. ስጦታ የአንድን ወገን ብቻ መኖር ያመለክታል።
ለ. የአንድ ስጦታን አስፈላጊነት የምንገነዘበው በሰጪው ማንነትና በስጦታው ምንነት ነው።
ሐ. በሮሜ 12 የአገልግሎት ስጦታዎችን ማን እንደሰጠ እንማራለን።
መ. ክርስቶስ "እንዳንዶች ሐዋርያት እንዲሆኑ ሰጠ"

የስጦታው ተቀባይ ተገልጿል

ቀደም ሲል ይህን ክፍለ ትምህርት ስንጀምር እንደተማርነው ማንኛውም ስጦታ የሁለት ወገኖችን መኖር ያመለክታል። የሰጪውንና የተቀባዩን መኖር ያመለክታል። ክርስቶስ የአገልግሎት ስጦታዎች ሰጪ እንደሆነ ቀደም ብለን ተመልክተናል። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የምንመለከተው ተቀባዩ ማን እንደሆነ ነው። ለዚህ ሁኔታ መልሱ ሁለት አንፃር ያለው ነው። "ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ" የሚለውን ከኤፌ 4:8 ላይ ብቻ ተመልክተን የምንወስን ከሆነ "የአገልግሎት ስጦታዎች የተሰጡት ለወንዶች ብቻ ነው" የሚል ውሳኔ ላይ እንደርሳለን። የሆነው ሆኖ አጠቃላዩን እውነት ለማግኘት ከአንድ ነጠላ ጥቅስ በላይ መመልከት ይኖርብናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምር ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ለማግኘት እንችል ዘንድ ይህ ዘወትር ልናስታውሰው የሚገባ መመሪያ ነው። በዚህ ጥቅስ ላይ እንደተመለከትነው አንድ ነጠላ ጥቅስ የእውነቱን አንድ አንጸር ብቻ ሊሰጠን ይችላል። መሉ ምንባቡን ማለትም ኤፌሶን 4:1-16ን ስናነብ ጳውሎስ በልቡ ያሰበው ስለመላው ቤተ ክርስቲያን ወይም ስለመላው አካል እንደሆነ እንረዳለን። ይህ እንግዲህ የአገልግሎት ስጦታዎች የተሰጡት በአካሉ ውስጥ ለሚገኙ ግለሰቦችና ለመላው አካል እንደሆነ እንድንገነዘብ ያረዳናል።



ለግለሰቡ ጥሪውና ሐዋርያ እንዲሆን የሚያስችለው የተለየ ችሎታ ወይም ጸጋ ይሰጠዋል። አገልግሎቱ የሚጠይቀውን ያሟላ ዘንድ ራሱ ሐዋርያው የተሰጠው ለአካሉ ነው። ኤፌ. 2:10ና 3:5 አንብብ።

(2). የአንድን ጥቅስ ትክክለኛ ትርጉም ለማግኘት በጣም ጥሩ የሆነው አጠናን መንገድ

ሀ. ጥቅሱን ብቻ ማጥናት ነው።
ለ ባጠቃላይ ምንባቡን ማጥናት ነው።
ሐ. ቢያንስ ሁለት ቁጥሮችን ማጥናት ነው።

(3). ሐዋርያት

ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ መጻሕፍት ናቸው።
ለ በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚገኙ የተለዩ ሰዎች ናቸው።
ሐ. በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ናቸው።

(4). የሐዋርያነት የአገልግሎት ስጦታ

ሀ. ግለሰቡ ራሱን እንዲያንጸባርቅ የተሰጠ ነው።
ለ. የመጀመሪያዎቹ 12ቱ ብቻ እንዲኖሯቸው የታቀደ ነው።
ሐ. ለግለሰብ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ የተሰጠ ነው።

ተግባሩ ሲብራራ

ሐዋርያነት በመባል የሚታወቀው የአገልግሎት ስጦታ በክርስቶስ አካል ውስጥ ካሉት እጅግ በጣም አስፈላጊ አገልግሎቶች አንዱ ነው። አገልግሎት ስንል የኃላፊነት ስፍራ ወይም ተግባር ማለታችን ነው። ይህ ስጦታ

በዝርዝር ውስጥ በመጀመሪያው ላይ የተጠቀሰው ምናልባት ከቤተ ክርስቲያን አመሠራረትና የበላይ ጠባቂነት ጋር በመያያዝ ሊሆን ይችላል።

ሁለት ዓይነት ሐዋርያት እንዳሉ ነው የምንረዳው። በመጀመሪያ በዚህ መጠሪያ የሚታወቁ እጅግ ልዩ የሆኑ የአማኞች ወገን ነበሩ። እነዚህም ወገኖች አሥራ ሁለት ብቻ ነበሩ። ከእነርሱ አንዱ የነበረው ይሁዳ ጌታውን በካደበት ጊዜና የሐዋርያነት ስፍራውን በአጣበት ጊዜ በሌላ ሰው ተተክቶአል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚሁ ሲገልጽ፣ "ዕጣም ተጣጣሉላቸው፥ ዕጣ ውም ለማትያስ ወደቀና ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቆጠረ" ይላል (የሐዋ 1:26)።

ለዚህኛው የመጀመሪያ የሐዋርያነት አገልግሎት ስፍራ ብቁ ለመሆን እያንዳንዱ ሰው ሊያሟላቸው የሚገቡ ሁኔታዎች ነበሩ። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን የጻፈው ሉቃስ በሐዋ 1:21-22 ይህንኑ ሁኔታ ሲገልጽ፣ "...ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ ከእኛ ዘንድ እስካረገበት ቀን ድረስ፥ ጌታ ኢየሱስ በእኛ መካከል በገባበትና በወጣበት ዘመን ሁሉ ከእኛ ጋር አብረው ከነበሩት ለዎች ከነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ይገባል" ይላል። ይሁን እንጂ ይህ ቅድመ ሁኔታ እንዲሟላ ጌታ ጠይቆ እንደሆነ እርግጠኞች አይደለንም። ይህ አሥራ አንዱ ሐዋርያት የተሰማሙበት ሃሳብ ሊሆን ይችላል።

እዚህ ላይ እንግዲህ የሚያጋጥመን ከበድ ያለ ጥያቄ፡- ጳውሎስ እንደ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ነበርን? የሚል ነው። በእርግጥ አንዳንድ ጥያቄዎች ለመመለስ ቀላል አይደሉም። የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች እንደመሆናችን መጠን አንዳንዶቹ ጥያቄዎቻችን መንግሥተ ሰማያት እስካልደረስን እንደማይመለሱ ልናውቅ ይገባናል። ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ መልሶችን ከመፈለግ ሊገታን አይገባም። መልሶችን ለማግኘት የምናደርገው ጥረት አእምሮአችንን ንቁ ከማድረጉም በላይ ለጌታም በተሻለ ሁኔታ አገልግሎት የምንሰጥ እንድንሆን ይረዳናል።

ቀደም ብለን ወደ አነሳነው የሐዋርያው ጳውሎስ ጉዳይ እንመለስና ራሱ ከሰጠው ምስክርነት ተነሥተን ብንመለከት፣ ጳውሎስ ራሱን ከነዚያ ሐዋርያት አንዱ አድርጎ ይቆጥር እንደነበር ለመረዳት እንችላለን። ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ እንደነበረ ጳውሎስ በግልጽ ከተናገረባቸው ጥቅሶች መካከል ጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥሎ እንመልከት።

1. "እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋለኞች እንዳደረገን ይመስለኛልና" (1ቆሮ 4:9)። እዚህ ላይ ጳውሎስ "እኛን ሐዋርያቱን" በማለት ራሱን ከሐዋርያቱ እንደ አንዱ አድርጎ እንደቆጠረ ግልጽ ነው።

2. "እንደ ሌሎቹ ሐዋርያትና..... መብት የለንምን?" (1ቆሮ 9:5)። በዚህ ላይ "እንደ ሌሎቹ" በማለት ከነዚያ ሐዋርያት አንዱ እንደ ነበረ ያመለክታል።

3. "እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና ..... ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፣....." (1ቆሮ 15:9)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ቁልፍ የሆነው ቃል "የማንስ" የሚለው ስለሆነ ይህም ከእነርሱ አንዱ እንደ ነበረ *ያመለክታል*። ከእነርሱ አንዱ ባይሆን ኖሮ ከእነርሱ አነስተኛውም መሆን ባልቻለ ነበር።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በዚያ ተሰብስበው በነበረው ቤት የነበሩት የጸሎት ቡድን ማትያስን በመሾማቸው ስህተት ፈጽመዋል በማለት ያስባሉ። የይሁዳን ስፍራ ይወስድ ዘንድ የጌታ ምርጫ የነበረው ጳውሎስ ነበር ብለው ያምናሉ። ስለዚህ ጉዳይ እኛም በእርግጠኝነት መናገር አንችልም። በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም አሥራ ሁለተኛው መሠረት ላይ የማን ስም ተጽፎ እንደሚገኝ ለማወቅ እዚያ እስክንደርስ መቆየት ሳያኖርብን አይቀርም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚሁ ሲገልጽ፣ "ለከተማይቱም ቅጥር አሥራ ሁለት መሠረቶች ነበሩአት፣ በእነርሱም ውስጥ የአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስሞች ተጽፈው ነበር" ይላል (ራዕይ 21:14)። የሚጸፈው የማትያስ ይሆን? ወይስ የጳውሎስ?፥ የሚጸፈው የማንኛው ስም እንደሚሆን የምናውቀው እዚያ ስንደርስ ነው።

አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በክርስቶስ አካል ውስጥ ማንም ሌላ አባል ሊኖረው የማይችለው ተግባር ነበራቸው። *በዚህ ዓለም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ድርሻ ነበራቸው። ከዚያም በስተቀር አብዛኛዎቹ በአዲስ ኪዳን የሚገኙትን መጻሕፍት ጽፈዋል።*

አሥራ ሁለቱ እንደ ሐዋርያት በጣም ልዩ ተግባር ቢኖራቸውም ሐዋርያነት የተባለ ሌላ የአገልግሎት ስጦታም አለ። ሁለቱም በመጠኑ ቢመሳሰሉም አንድ እንደሆኑ አድርገን ልናስብ አይገባንም። በክርስቶስ አካል ውስጥ የአሥራ ሁለቱ ስፍራ በጣም የተለየ ነበር። የእነርሱ ዓይነት አገልግሎት በፍጹም የሚያገኝ ዓይነት አልነበረም። "ሐዋርያነት" የተባለው የአገልግሎት ስጦታ ግን በቤተ ክርስቲያን ወይም በክርስቶስ አካል ግንባታ ዘመን ሁሉ የሚሰጥ ስጦታ እንዲሆን የታቀደ ነበር።

ልዩ ተግባርን ያከናውኑ በነበሩ ክርስቶስ ሐዋርያትን እነሱ ለሆኑት ቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል። አንድ ጭብጥ ጭቃ እንድን የሸክላ ዕቃ ዓይነት ለመሆን በራሱ ሊወሰን እንደማይችል ሁሉ ሰዎችም ሐዋርያ ለመሆን በራሳቸው መወሰን አይችሉም። እውነተኛ ሐዋርያት የሆኑት ሐዋርያ መሆናቸውን እንኳ ሳያውቁትና ራሳቸውን በዚያ ደረጃ ሳያመለክቱት ይችላሉ። የሚያደርጉት ነገር ሌሎች ሰዎች በሐዋርያነት እንዲያውቋቸው ያደርጋቸዋል። ራሳቸውን ሐዋርያት ብለው የሚጠሩ ወይም ሐዋርያት ተብለው በሰዎች የተሾመ ከቶውኑም ሐዋርያት ሳይሆኑ ይችላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ "ሐዋርያት ነን የሚሉትን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሀቸው አውቃለሁ" ይላል (ራዕይ 2:2)። በተጨማሪ 2ቆሮ 11:13 ተመልከት።

ሐዋርያት የሚለው ቃል ትርጉም ሐዋርያት እነማን እንደሆኑና ተግባራቸውም በእርግጥ ምን ምን እንደሆነ እንድንረዳ ያደርገናል። "ሐዋርያ" የሚለው ቃል "የተላከ" ወይም "መልዕክተኛ" አድርጎ ማሰማራት ማለት ነው። ማቴዎስም ሆነ ማርቆስ እያንዳንዳቸው "ሐዋርያ" የሚለውን ቃል አንዳንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅመውበታል (ማቴ 10:2፤ ማር 6:30)። ጥቅሶቹ በተጠቀሱበት በእያንዳንዱ ስፍራ የሚያመለክተው አንድ የተለየ ተግባርን ነው። ይኸውም የመልዕክተኛነትን ሥራ ነው። ከዚህ አንጻር አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትና የሐዋርያነት ስጦታ ሁለቱም ይመሳሰላሉ።

ስለሆነም ሐዋርያ ወንጌልን ወደ አዳዲስ ስፍራዎች ለማድረስ በጌታ የተላከ መልዕክተኛ ነው። ተግባሩም ለክርስቶስ አዲስ የአካሉ ክፍል ለሚሆኑት መሠረት መጣል ነው። የክርስቶስን አካል ማነጽና የአካሉንም መንፈሳዊ እቅም መቆጣጠር በተግባሩ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚሁ ሲናገር፣ "ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ" ይላል (ኤፌ 4:12)።

ለምሳሌ ያህል ኬን ጌትስ የተባሉ አንድ ሚሲዮናዊ በሰሜን ምዕራብ ወደሚገኘው የካናዳ ክልል ሄደው ነበር። ወደዚያ ከመሄዳቸው በፊት ግን እንዳንድ ሰዎች ያንን እርምጃ እንዳይወስዱ ተስፋ ሊያስቆርጡአቸው ሞከሩ። መምህሮቻቸው ከነበሩት አንዳንዶቹ በፍጹም ሰባኪ ሊሆኑ እንደማይችሉ ነግረዋቸው ነበር። ሐዋርያ ለመሆን የሚያበቃ ባሕርይ ይኖራቸዋል ብለው ጨርሶ አላሰቡም። ሊያገለግሉአቸው የሄዱባቸው ሕዝቦች መልካም አቀባበል አላደረጉላቸውም። እንዲያውም ሥራቸውን ትተው እንዲመለሱ ለማድረግ ሞከሩ።

ሆኖም ኬን እግዚአብሔር እንደላካቸው ያውቁ ነበር። በዚህም ምክንያት በስፍራቸው ጸንተው ቆዩ። ዛሬ ታዲያ በዚያች አገር ድንቅ የሆኑ አማኞችና ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም አሉ። በዚያ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት እንዲተከሉ ያደረጉት ኬን ጌትስ ናቸው። አማኞች በእምነታቸው እንዲያድጉና እንዲጎለምሱ ረድተዋል። በዚያም ይሠራ የነበረውን የጌታ ሥራ እንደ አባት ሆነው ተንከባክበዋል። በዚህ ሁሉ ግን ራሳቸውን እንደ ሐዋርያ ፈጽሞ ቆጥረው አያውቁም። ዳሩ ግን እርሳቸውንና የሠሩትን ሥራ የሚያውቁ በእርግጥ ሐዋርያ እንደሆኑ ይገነዘባሉ።

(5). አሥራ ሁለቱ የጥንት ሐዋርያት በዛሬ ዘመን ካሉት ሐዋርያት ልዩ የሆኑት፡-

ሀ. ራሳቸውን ሐዋርያ ስላደረጉ ነው።
ለ. በወንጌል ሥራ ላይ ስለተጠመዱ ነው።
ሐ. የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ስለጻፉ ነው።

(6). በዛሬው ዘመን የሐዋርያት ተግባር

ሀ. ተጨማሪ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን መጻፍ
ለ. ወንጌል ወደ አልደረሰባቸው አዳዲስ ስፍራዎች ማድረስና በዚያ የሚካሄደውን የእግዚአብሔር ሥራ ዕድገት መከታተል ነው።
ሐ. ጥሩ ሰባኪዎች እንዲሆኑ ተግተው ማጥናት ነው።

የአገልግሎቱ ዕድገት ሲብራራ

ሐዋርያት ሁሉ ነገር የተሳካላቸውና የተጠናቀቀላቸው ሰዎች አይደሉም። በመጀመሪያ ደረጃ የኢየሱስ ክርስቶስ የቅርብ ተከታዮች መሆናቸው የታወቀ ነው። ብርቱ የሆነ የእግዚአብሔር ጥሪ በሕይወታቸው ይሰማቸው ይሆናል፤ ሆኖም ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ የክርስቶስ ልዩ ስጦታዎች መሆናቸውን ብዙውን ጊዜ ራሳቸውም አይገነዘቡትም።

እግዚአብሔር አንድን ሰው ሐዋርያ እንዲሆን ሲመርጥ ያ ሰው እንዲያድግና ለአገልግሎቱ ዝግጁ እንዲሆን ጊዜ ያመቻችለታል። ጳውሎስ በመጀመሪያ ድነትን እንዳገኘ በሐዋርያነት የአገልግሎት ሥራ ላይ አልተ ቀመጠም። ሆኖም አንድ የተለየ አገልግሎት እንደሚሰጥ እግዚአብሔር በልቡ ውስጥ ያረጋገጠለት ሃሳብ ነበር።መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚሁ ሲገልጽ፣ "የአባቶቻችን አምላክ ፈቃዱን ታውቅ ዘንድና ጻድቁን ታይ ዘንድ የአፉንም ድምፅ ትሰማ ዘንድ አስቀድሞ መርጦሃል፤ ባየኸውና በሰማኸው በሰው ሁሉ ፊት ምስክር ትሆንለታለህና" ይላል (የሐዋ 22:14-15)።

ጳውሎስ የተለየ ዓይነት ሐዋርያ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም፣ ሆኖም ሐዋርያ ለመሆን የተዘጋጀበት መንገድ ዛሬ አንድ አማኝ ለዚሁ አገልግሎት ከሚዘጋጅበት መንገድ ጋር በአብዛኛው ሊመሳሰል የሚችል ነው። በዝግጅቱ ሂደት ውስጥ የሚካተቱ በርከት ያሉ ደረጃዎች አሉ።

1 - መከራ መቀበል

አማኞች ሁሉ ሐዋርያ ለመሆን አይችሉም። ምክንያቱም በሐዋርያነት የአገልግሎት ዝግጅት በሚያስችለው የመከራ ሕይወት ለማለፍ ስለማይፈቀዱ ነው። ሐዋርያ ከመሆን በፊት ተደም ብሎ ጳውሎስ ስለዚሁ ሁኔታ እንደተናገረው ሲገልጽ፣ "ስለ ስሜ ስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው እኔ እመለክተዋለሁና" ይላል (የሐዋ 9:16)። መከራ በተለየ ዓይነት መንገድ ሰዎችን በክርስቶስ አካል ውስጥ መሪዎች እንዲሆኑ ያዘጋጃቸዋል። በመከራ ውስጥ ያላለፉ ሰዎች በመከራ ውስጥ እንዳለፉ ሰዎች ሰዎችን ሊያገለግሉ አይችሉም።መከራ ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች ብዙ መከራ ሊቀበሉባቸው ወደሚችሉባቸው አዳዲስ ስፍራዎች የወንጌልን ቃል ይዘው ለመሄድ ዝግጁ አይደሉም። መከራ መቀበል ሰዎችን ለበለጠ መከራ ያዘጋጃቸዋል።

2 - ብርታትና ዕድገት

ለአገልግሎቱ እየተዘጋጀ በነበረበት ጊዜ ኢየሱስ እንኳን እድገት አሳይቷል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚሁ ሲገልጽ፣ "ኢየሱስ ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።" ይላል (ሉቃ 2:52)። እገልግሎቱ እደገ ስንል እገልግሎቱ ጨምሮ ነበር ማለታችን ነው። ስለሆነም ኢየሱስ በጥበብና በሞገስ አድጎ ነበር። እንግዲህ ለእርሱ ይህ እስፈላጊ ከሆነ ለሐዋርያነት ዝግጅት ምን ያህል ይበልጥ ያስፈልጋቸው ይሆን?

ጳውሎስ ብርታት በመጨመር እያደገ ይሄድ ነበር። በሐዋ 9:22 ላይ ስለዚሁ ሲገልጽ፣ "ሳውል ግን እየበረታ ሄደ" ይላል። በዚህ ጥቅስ ውስጥ "እየበረታ" የሚለው ቃል በተለይ መንፈሳዊ ብርታትን የሚያመለክት ይመስላል። በተለየ ዓይነት መንገድ የእግዚአብሔርን ብርቱ ኃይል ሳያውቅ እንደማይቀር ይገመታል። እዚህ ላይም በድጋሚ ታላቁ ሐዋርያ ጳውሎስ ያንን መሰያ ዝግጅት ካስፈለገው ሌሎች ሐዋርያት ሁሉ ዝግጅት እንደሚያስፈልጋቸው እርግጠኛ መሆን እንችላለን።

3 - መማር

መማር ለማንኛውም እገልጋይ እስፈላጊ ነው። በክርስቶስ አካል ውስጥ መሪዎች በመሆናቸው ለሐዋርያት ደግሞ በይበልጥ እስፈላጊ ይሆናል። ሰለ ጳውሎስ በድጋሚ ብንመለከት ለዚህ ጉዳይ እርሱ ጥሩ ምሳሌያችን ነው። እርሱ ሐዋርያ ከመሆኑ በፊት ለተወሰነ ወቅት ራሱን ሲያዘጋጅ በረሃ መቆየት ነበረበት (ገላ 1:16-18)። የመማሩ ወቅት እንደተጠናቀቀ ጳውሎስ የተሳካ የምስክርነት አገልግሎት ለመጀመር ዝግጁ ሆነ።

(7). ከዚህ በታች ከቀረቡት መግለጫዎች መካከል እውነት በሆነው እንጻር ያለውን ፊደል ክበቡ።

ሀ. ሰዎች ሐዋርያ ሆነው ይወለዳሉ።
ለ. ሐዋርያት የሚሆኑት በቅድሚያ ዝግጅት ሊያደርጉ ይገባቸዋል።
ሐ. ጳውሎስ ድኅነትን እንዳገኘ ወዲያው ሐዋርያ ሆነ።
መ. ሐዋርያ በመሆን ዝግጅት ውስጥ መከራን መቀበል አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

አገልጋዮችን ጎጣዎች እንዲሆኑ ሰጠ

ዓላማ 2 የነቢይ ተግባር ምን እንደሆነ መግለጽ።

የሰጪውን ማንነት ለይቶ ማወቅ

ክርስቶስ የአገልግሎት ስጦታዎች ሁሉ ሰጪ መሆኑን ቀደም ብለን ተምረናል። በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ ስጦታ አስፈላጊ እንደሆነ

ተረድተናል። ስለ ሐዋርያት ስመታ እውነት የሆነው ነገር ሁሉ ስለ ነብያትና ስለቀሩትም የአገልግሎት ስመታዎች ሁሉ እውነት ነው። እያንዳንዱ ስመታ በክርስቶስ ለአካሉ የተሰጠ ነው። ይህን መሳዩን ስመታ ለማግኘት የሚያበቃው ችሎታና ጥሪ በክርስቶስ ለተወሰኑ የአካሉ ብልቶች ይሰጣል። ክርስቶስ አካሉን የሚያንጹትን አገልጋዮችን ይሰጣል ማለት እንችላለን።

ማንኛውም ሰው ሐዋርያ ወይም ነቢይ ሊሆን ይገባዋል ማለት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዳንዶች ሐዋርያት፣ አንዳንዶች ነብያት እንዲሆኑ ሰጠ ይላል። አንዳንዶች የሚሰው ቃል ሁሉም ሐዋርያት ወይም ሁሉም ነብያት ሊሆኑ እንደማይችሉ ግልጽ ያደርገዋል። በእያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል አንዳንዶች እንዲያገልግሉ ጌታ አስቀምጦአቸዋል። ይህ ሁኔታ ጳውሎስ በ1ቆሮ 12:17 ላይ "አካል ሁሉ ዓይን ቢሆን መስማት ወዴት በተገኘ? ሁሉም መስማት ቢሆን ማሽተት ወዴት በተገኘ" በማለት የጠየቀውን ጥያቄ ያሳስበናል።

ስለ ሰጨው የሚናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስንመለከት ደግሞ በ1ቆሮ 12:28 ላይ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያት ሁለተኛም ነብያትን አድርጎአል" የሚል ቃል ተጽፎ እናነባለን።

በኤፌሶን መልዕክት ስጨው እግዚአብሔር እንደሆነ ተነግሯል። ጥቂት አሰፍ ብሎ እዚያው የኤፌሶን መልዕክት ውስጥ ስጨው ክርስቶስ እንደሆነ ተነግሯል። ታዲያ ይህንን እንዴት ልንረዳው ይገባል? እንደ እውነቱ፥ ከሆነ ይህ ምንም አስቸጋሪ አይደለም። በሥላሴ ውስጥ ካሉት ሦስት አካላት አንዱ ክርስቶስ ስለሆነ ራሱ እግዚአብሔር ነው። ሥላሴ ማለት በሦስትነት አንደነት፥ ማለትም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ማለት ነው። በዙሰተኛ ደረጃ እግዚአብሔር የሚሰጠውን ስመታ ሁሉ በክርስቶስ በኩል እንደሚሰጥ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ያዕ 1:17 እና ኤፌ 4:1:11 አንብብ።

(8) ከሚቀጥሉት መግለጫዎች እውነት በሆነው መግለጫ አንጻር "እ" ሐሰት በሆነው መግለጫ አንጻር ደግሞ "ሐ" የሚሉትን ፊደሎች ጻፍ።

___ ሀ. በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ አባል ነቢይ እንዲሆን ይጠበቅበታል።

___ ለ. ከክርስቶስ አካል ብልቶች መካከል አንዳንዶቹ ብቻ ነቢያት እንዲሆኑ ተጠርተዋል።

___ ሐ. እግዚአብሔር የአገልግሎት ስመታዎችን የሚሰጠው በክርስቶስ አማካኝነት ነው።

የስመታው ተቀባይ ተገልጿል

በአንድ በኩል ስንመለከተው ነቢይ የተባለው የዚህ አገልግሎት ስመታ ተቀባይ የክርስቶስ አካል ናት። በሌላ መንገድ ስንመለከተው ተቀባዩ ነቢይ ተብሎ የተጠራው ሰው ነው። ነቢይ የሆነው ሰው በእግዚአብሔር የተጠራና ለክርስቶስ አካል ስመታ ለመሆን የተዘጋጀ ነው።

አንድ ሰው ነብይ ለመሆን ሊያደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች ይኖሩ ይሆን? እግዚአብሔር ያለ አንዳች ምክንያት የተወሰኑ ሰዎችን ወደዚህ ከፍ ያለ የአገልግሎት ስፍራ አላመጣቸውም። ይህም የሚያስረዳን እግዚአብሔር ይህንን የማድረግ መብት እንዳለው ነው። ጳውሎስ ስለዚሁ ሲገልጽ፣ "ሥራ ሠሪውን፣ ስለ ምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን?" (ሮሜ 9:20)። ይህ ሲባል በአንድ አማኝና በሽክላ ዕቃ መካከል ልዩነት መኖሩ ገልጽ ነው። አማኝ የራሱ የሆነ ፈቃድ ስላለው የራሱን ምርጫ የመከተልና የማድረግ ችሎታ አለው።

በአማኝ ላይ በሚደርሰው ነገር በከፊልም ቢሆን የራሱ ምርጫም አለበት። የልቡም ዝንባሌ ከእግዚአብሔር ምርጫ ጋር የተያያዘ ነው። የሸክላ ዕቃ ምንም የአስተሳሰብ ዝንባሌ የለውም። ሰዎች ግን የአስተሳሰብና ምርጫን የመከተል ዝንባሌ አላቸው። የአስተሳሰብ ዝንባሌ ስንል አስተሳሰብን፣ ድርጊትን፣ ወይም ስሜትን የምንገልጽበት መንገድ ማለታችን ነው። እግዚአብሔር ፈቃዳችንን፣ አስተሳሰባችንን፣ የድርጊታችንና የስሜታችንንም አካሄድ በሚገባ ያውቃል። ነቢያትን በሚመርጥበት ወቅት እነዚህን ነገሮች ሁሉ ይመገዘናል።

ዳዊት የብሉይ ኪዳን ንጉሥ ከመሆኑም በተጨማሪ ነቢይ ነበር። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከአዲስ ኪዳን ነብያት በመጠኑ ለየት ያሉ ነበሩ። ሆኖም እግዚአብሔር ዳዊትን ሰምን የተለየ ስመታ አድርጎ ለሕዝቡ ለእስራኤል እንደሰጠው ልብ ብለን ብናስተውል ጠቃሚ የሆነ ትምህርት እናገኛለን። የዳዊትን ታሪክ ከብሉይ ኪዳን በማንበብ እንደምንረዳው ዳዊት በዕድሜው፣ በቤተሰብ በነበረው የተለየ ግምት፣ የሕይወት ልምምድ ወይም በውጫዊ አቋሙ እንዳልተመረጠ መረዳት እንችላለን። በዳዊት ዘመን ሰዎች መሪ እንዲሆን የሚመርጡት ኤልያብን ወይም የእነርሱ ታላቅ የሆነውን ነበር። በባህሉ መሠረት ከታናናሽ ይልቅ ታላላቅ ወንድሞች ለመሪነት አገልግሎት ይመረጣሉ። ዳዊት የመጨረሻው ታናሽ ቢሆንም እግዚአብሔር ከፍ ላለው የመሪነት ስፍራ መረጠው። ይህ ለምን ይሆን? በእርግጥ ሲያዩት ደስ የሚያሰኝ ልጅ ቢሆንም የተመረጠው በዚህ ምክንያት አልነበረም። የዚህ ጥያቄ መልስ የሚገኘው በሐዋ 13:22 ላይ ሲሆን፣ ቃሉም፣ "እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" የሚል ነው። እግዚአብሔር ፈቃዱንና የአስተሳሰቡን ዝንባሌ ስለ ተመለከተ ዳዊትን ንጉሥም ነቢይም እንዲሆን መረጠው።

ነቢያትና ሌሎችም የአገልግሎት ስመታዎች ተዘጋጅተው ለክርስቶስ አካል የሚለጠጉት እግዚአብሔር ውስጣዊ ባሕርያትን ስለሚመለከት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል። 1ኛ ሳሙ 16:1-13፣ የሐዋ 22:14 አንብብ።

(9). በሐዋ 13:22 መሠረት ዳዊት ለአንድ የተለየ ምክንያት ተመርጦ ነበር። ዳዊት የተመረጠበትን ትክክለኛ ምክንያት ከሚገልጸው ዓረፍተ ነገር አንጻር ያለውን ሬዲል ክበበው።

ሀ. ነቢይ ይሆን ዘንድ ሳሙኤል መርጦት ስለነበረ ነው።
ለ. ከወንድሞቹ ሁሉ ታናሽ ስለነበረ ነው።
ሐ. ሲያዩት ደስ ይል ስለነበረ ነው።
መ. እግዚአብሔር የሚፈልገው የልብ ዝንባሌ ስለነበረው ነው።
ሠ. በጎችን በማሠማራት ልምድ ስለነበረው ለሕዝብ ጥሩ መሪ ስለሚሆን ነው።

ተግባሩ ሲብራራ

ነቢይነት በመባል የሚታወቀው የአገልግሎት ስውታ ሁለት ዋና ዋና ተግባሮች አሉት።

1. መተንበይ ማለትም አንድ ሁኔታ ከመፈጸሙ በፊት መናገር እና

2. ማወጅ ማለትም "መልእክትን በቀጥታ መናገር ወይም ማስተላለፍ"

ነቢይ በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድቶ የሚናገር ነው። ይህም ማለት የእግዚአብሔር መንፈስ በወረደበት ጊዜ የእግዚአብሔርን መልዕክት ያስተላልፋል። ለሕዝቡም የእግዚአብሔርን መልዕክት የሚያብራራው እርሱ ነው። "ያብራራል" ስንልም "ትርጉሙን ይገልጻል" ማለታችን ነው። አንድ ሰው እንደ ነቢይ ተናገረ የምንለው ከመንፈስ ቅዱስ ባገኘው መረዳት መሠረት የእግዚአብሔርን መልዕክት ሲተረጉምና ሲያብራራ ነው።

ነቢይ ስለ ወደፊት የሚናገር ሲሆን፣ "ስለ ወደፊት መናገር" የሚለው ሐረግ "መተንበይ" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። የብሉይ ኪዳን ነብያት ሁኔታዎች ከመፈጸማቸው አስቀድሞ ሊሆን ያለውን ይናገሩ ነበር። ከዚያ በኋላ ከእግዚአብሔር ያገኙትን የመልዕክቱን ትርጉም ለሕዝቡ በማቅረብ ያብራሩ ነበር።

የአዲስ ኪዳን ነቢይ ተግባር ከብሉይ ኪዳን ነቢይ ጋር በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው። የአዲስ ኪዳኑም ነቢይ የእግዚአብሔርን መልዕክት ለሕዝቡ ይናገራል። ከዚያ በኋላም የመልዕክቱን ትርጉም ያስታውቃል። ሆኖም እንዳንድ ልዩነቶችም አሉ። የብሉይ ኪዳኑ ነቢይ ቃሉች ቀደም ሲል በተሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ላይገኙ ይችላሉ (ምንም እንኳን ከተሰጠው ቃል ጋር የሚቃረኑ ሆነው ባይገኙም)። በእርግጥ አልፎ አልፎ ከተጻፈው ቃል ይጠቀሱ ይሆናል። የአዲስ ኪዳን ነቢይ አብዛኛውን ጊዜ ቀድሞ በተሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ላይ በተመሠረቱ ማበረታቻዎችንና ተግሳፅን ያቀርባል። በሐዋ 15:32 ላይ የምንመለከተው የይሁዳና የሲላስ አገልግሎት ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። እንግዲህ በዚህ ዓ

ይነት ከእግዚአብሔር ዘንድ በእግዚአብሔር መንፈስ አማካኝነት በአንድ የተለየ ወቅት ለሕዝቡ ችግር መልስ የሚሆን የተለየ መልዕክት ያቀርባል።

የአዲስ ኪዳኑ ነቢይ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር የሚገልጸ የትንቢት ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚቀበልበትም ጊዜ ይኖራል። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ አጋቦስ የተባለ አንድ ሰው ነቢይ ተብሎ ተጠርቷል። "አያሌ ቀንም ተቀምጠን ሳለን ነቢይ የነበረ አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ከይሁዳ ወረደ" (የሐዋ 21:10)። ወደፊት ስለሚፈጸመው ሁኔታዎች እንደተናገረ ሁለት ጊዜ ተገልጿል። አጋቦስ "ተነሥቶ በዓለም ሁሉ ታላቅ ራብ ሊሆን እንዳለው በመንፈስ አመለከተ፤ ይህም በቀላውዴዎስ ቄሣር ዘመን ሆነ" (የሐዋ 11:28)። ስለዚሁ ነቢይ የሚናገረውን ሁለተኛውን ታሪክ በሐዋ 21:11 ላይ እናገኘዋለን።

ትንቢት የሚናገር ነቢይ መልዕክቱ ከእግዚአብሔር እንደሆነ እንዲታወቅ መልዕክቱን መፈተን ይቻላል። ትንቢቱ የማይፈጸም ከሆነ የተናገረው ከልቡ አውጥቶ ነው ማለት ነው። "ስለ ሰላም የተናገረ ነቢይ፥ የነቢዩ ቃል በሆነ ጊዜ፥ እግዚአብሔር በእውነት የሰደደው ነቢይ እንደሆነ ይታወቃል።" (ኤር 28:9)።

ትንቢት ስለሚናገሩ የአዲስ ኪዳን ነብያት ጴጥሮስ መልካም ምሳሌ ነው። እርሱ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱና ነቢይም ነበረ። እንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው በብዙ አቅጣጫ ስውታ ሊኖረው ይችላል። በሐዋ 2:1-12 ላይ እንደተገለጸው መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ወቅት የሆነውን ነገር ለመመልከት ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ነበር። እነዚያም ሰዎች ይህ ምን ማለት ነው?" ብለው ጠየቁ። በዚያን ጊዜ እንደ ነቢይ መንፈስ ቅዱስ ሲወርድበት የእግዚአብሔርን መልዕክት ተናገረ። መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰውን የትንቢት ቃል አስታወሰው። ጴጥሮስ ለሚናገረው ቃል ቅድመ ዝግጅት ለማድረግና ዕቅድ ለማውጣት ጊዜ አልነበረውም። ስለሆነም በቀጥታ እንደተናገረ የመልዕክቱን ትርጉም ወዲያው ይሰጥ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ችሎታውን ሰጠው።

እጅግ አስፈላጊ የሆነው የነቢይ ተግባር በኤፌ 4:12 ላይ እንደሚከተለው ተገልጿል። "..... ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ናጹማን ይሆኑ ዘንድ" ይላል። መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ በወረደ ጊዜ የእግዚአብሔርን መልዕክት የሚናገር ሰው ሁለቱንም ዓላማዎች እንደሚገባ ያሟላል። በቅድሚያ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ዝግጁ እንዲሆን ይረዳል። ምዕመናን የእግዚአብሔር መንፈስ አርፎበት ከሚያስተምራቸው አስተማሪ ብዙ ይማራሉ። መልዕክቱ ከሚተላለፍበት ከራሱ ከመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ያገኛል።

(10). ቀጥሎ የተጠቀሰውን ዓረፍተ ነገር የተሟላ ሊያደርገው ከሚችለው መግለጫ አንጻር ያለውን ሬዲል ክበበው። የነብይ ተግባር. . .

ሀ. በምዕመናኑ መካከል በትምክህት መመላለስ ነው።
ለ. ታላቅ መሪ እንደሆነ መታወቅ ነው።
ሐ. ለምዕመናኑ የእግዚአብሔርን መልዕክት ማስተለለፍ ነው።
መ. የእግዚአብሔርን መልዕክት ለምዕመናኑ ማስረዳት ነው።

የአገልግሎቱ ዕድገት ሲብራራ

አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔር ሰዎታዎች እንደሚገባ ሊሠሩ የሚታዩት ራሳቸውን ባዘጋጁ አገልጋዮች ውስጥ ነው። የጴጥሮስን መልዕክት በድጋሚ ብንመለከት በመንፈስ ቅዱስ በመሞላቱ ዝግጁ እንደነበር እንረዳለን። እርሱ የነበረውም የእግዚአብሔር ቃል እውቀት የዚያን ጊዜ ለተከሰተው ሁኔታ አንዱና በጣም አስፈላጊው ክፍል ነበር።

በአንድ ነቢይ ወደ አገልግሎት መምጣት የሚታዩ ሦስት አስፈላጊ የዕድገት ደረጃዎች አሉ።

1. *በየዕለቱ መጸለይ*- የማይጸልይ ነቢይ ብዙም ሳይቆይ ይደክማል። መጸለይ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ያስችላል። አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ካልተሞላ በስተቀር ነቢይ መሆን አይችልም። መጸለይ በመንፈስ ቅዱስ እየተንተባተበ እንደሆነ እንዲያውቅ ያረዳዋል።

2. *የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ*- የእግዚአብሔር ቃል እውቀቱ በጨመረ መጠን የነቢይ አገልግሎቱ ጠንካሳ የመሆን እድሉ እየጨመረ ይሄዳል። "የእውነትን ቃል በትንንት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ የተፈተንህን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ" (2ጢሞ 2:15)። የእግዚአብሔርን መልዕክት በሚናገርበት ወቅት አንድ ነቢይ አስተማሪም ይሆናል።

3. *በስዎታው ማገልገል*- የእግራችንና የእጃችን ጡንቻዎች ስንጠቀምባቸው እንደሚዳብሩ ሁሉ ከጌታም የምንቀበላቸው ስዎታዎች ስንጠቀምባቸው ይዳብራሉ። ነቢይ መናገር በሚጀምርበት ጊዜ ሊፈራ ይችላል። ይህን ስንል ታዲያ የሚናገረው በእግዚአብሔር መንፈስ አይደለም ማለታችን አይደለም። የእግዚአብሔር መንፈስ በሙላት በነፃነት እንዲጠቀምበት የበለጠ ዕድል መስጠት ያስፈልገዋል ማለታችን ነው። ስዎታ በጥቅም ላይ ሲውል ይበልጥ እየዳበረ ይሄዳል።

(11). አንድ ነቢይ ስዎታውን እንዴት ማዳበር እንደሚገባው ከሚገልጸው ዓረፍተ ነገር አንጻር ያለውን ፊደል ክበበው።

ሀ. መዘጋጀትና የእግዚአብሔርን ማረጋገጫ ማግኘት
ለ. መጸለያና በስዎታውም መገልገል መጀመር
ሐ. በተቻለው መጠን ስለ ነቢያት ማጥናት
መ. እግዚአብሔርን ደስ ስላሳኘት ነብያት ከታሉ ማንበብ

የመከራ ፈተና

1. ትክክለኛውን ቁጥር በክፍት ስፍራው በመጻፍ በቀኝ በኩል ያሉትን መግለጫዎች በግራ ካሉት ቃላት ጋር አዛምድ።

____ሀ. ማብራራት	1. በቀጥታ መናገር
____ለ. መፍቀድ	2. መላክ
____ሐ. ማወጅ	3. መምረጥ
____መ. መተንበይ	4. ስለ ወደፊቱ መናገር
____ሠ. ሐዋርያ	5. ትርጉም መስጠት

2. የመንፈሳዊ ስዎታዎች ሁሉ ስጪ _____ ነው።

3. ከእውነተኛው መግለጫ አንጻር ያለውን ፊደል ክበበው።

ሀ. ጳውሎስ ሐዋርያ የሆነው ክርስቶስን የግሉ አዳኝ አድርጎ እንደተቀበለ ነው።
ለ. ሁሉም ሰው ነቢይ ወይም ሐዋርያ እንዲሆን አልተፈጠረም።
ሐ. በአሁኑ ዘመን ሐዋርያ የሚሆኑት ሰዎች ተግባር ከቀድሞዎቹ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ምንም የተለየ አይደለም።
መ. የትኛው አማኝ የአገልግሎት ስዎታዎች መቀበል እንደሚገባው የምት ወስነው ቤተ ክርስቲያን ናት።
ሠ. ስዎታዎች በተቀበልናቸው ወቅት የዳበሩ አይደሉም፥ የሚዳብሩት በአገልግሎት ላይ ሲውሉ ነው።

4. ሁለቱ አስፈላጊ የሐዋርያት ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

5. የነቢይ ሁለት ዋና ተግባሮች ምንድን ናቸው?

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. ሀ. ሐሰት ሐ. ሐሰት
   ለ. እውነት መ. እውነት

7. ሀ. ሐሰት ሐ. ሐሰት
   ለ. እውነት መ. እውነት

2. ለ

8. ሀ. ሐ ለ. እ ሐ. እ

3. ለ

9. መ

4. ሐ

10. ሐ እና መ

5. ሐ

11. ለ

6. ለ

4 ወንጌላውያንና መጋቢ አስተማሪዎች

ትምህርት

ቀደም ባለው ክፍለ ትምህርት ከአገልግሎት ስጦታዎች ስለ ሁለቱ ማለትም ስለ ሐዋርያትና ስለ ነቢያት የቀረቡትን ትምህርቶች ተከታትለናል። ሁለት ዓይነት ሐዋርያት እንደነበሩም ተረድተናል። በቅድሚያ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የተባሉ ልዩ የሆኑ ወገኖች ከጌታ ኢየሱስ ጋር በመሆን ቤተ ክርስቲያንን በመትከል ከማገልገላቸውም በላይ ከእነርሱ አንዳንዶቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን የጻፉ መሆናቸውን ተመልክተናል።

በሁለተኛው ምድብ የሚገኙት በኤፌ 4:11 ላይ የተመዘገቡት ሲሆኑ፣ በዚህ ምድብ የተጠቀሱት ደግሞ ወደ አዳዲስ ክልሎች በመሄድ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረትና ለማሳደግ ሃላፊነት ነበራቸው። ሆኖም ከነርሱ አንዳቸውም የእግዚአብሔርን ቃል እንዲጽፉ አልተጠበቀባቸውም፣ ምክንያቱም ይህ ሥራ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተጠናቀው በተጻፉበት ወቅት በሚገባ ተጠናቅቆ ነበርና።

ነቢይ ሁለት መንታ ተግባሮችን ማለትም የማወጅና የመተንበይ አገልግሎትን እንደሚያከናውን ተምረናል። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስለቀሩት ሦስት ስጦታዎች ለመማር ዝግጅታችንን እንቀጥላለን።

ይህ ክፍለ ትምህርት ወንጌላውያንና መጋቢ - አስተማሪዎች በመባል የሚታወቁትን የአገልግሎት ስጦታዎች ያስተዋውቀናል። መጋቢ - አስተማሪዎች በመባል የሚታወቁት ሁለቱም ስጦታዎች በብዙዎች ዘንድ አንድ ዓይነት አገልግሎት እንደሆነ ስለሚታመን ስለ እነዚህ የአገልግሎት ስጦታዎች በዚህ ክፍለ ትምህርት እንማራለን።

እነዚህ የአገልግሎት ስጦታዎች ያላቸውን አገልጋዮች ጌታ ብዙ እንደ ተጠቀመባቸውና አሁንም እንደሚጠቀምባቸው ግልጽ ነው። ስለሆነም ከእነዚህ ስጦታዎች ወደ አንደኛው የእግዚአብሔር እጅ የሚመራህ ከሆነ ለዚሁ ራስህን በሚገባ አዘጋጅ።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- አንዳንዶች ወንጌላውያን እንዲሆኑ ስጠ
- አንዳንዶችን መጋቢ - አስተማሪዎች እንዲሆኑ ስጠ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

- የአገልግሎት ስጦታዎችን ምንነት በሙሉ ማወቅና የእያንዳንዱን ተግባር መግለጽ
- የአገልግሎት ስጦታዎችን ማን እንደሚሰጥና እነማን እንደሚቀበሉ መግለጽ
- የአገልግሎት ስጦታዎች ሊዳብሩ የሚችሉበትን መንገዶች መገንዘብ
- በግል ሕይወትህ ጌታ አገልግሎቱን እያሳደገ መሆን አለመሆኑን መረዳት።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ሐዋ ምዕራፍ 7 እና 8 እንደዚሁም 1ጢሞ 4:1-16 አንብብ።

2. 1ቆሮ 13 በቃልህ ማጥናት ቀጥል። ይህንን ክፍለ ትምህርት በምታጠናቅቅበት ጊዜ ከዚሁ ምዕራፍ ከቁ. 1-7 ያለውን በቃልህ አጥንተህ መጨረስ ይገባሃል።

3. ይህንን ክፍለ ትምህርት በሙሉ በዘጣታ በማንበብ ጠቃሚ ነጥቦቹን አስምርባቸው።

4. የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎቹን መልስ። መልሱን ከተሳሳትክ ትክክለኛውን መልስ እስከምትረዳ ድረስ ወደሚቀጥለው ትምህርት አትተላለፍ።

5. በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ የቀረበውን የሙከራ ፈተና አጠናቅ። የሰጠሃቸውን መልሶች ከቀረቡት ትክክለኛ መልሶች ጋር በጥንቃቄ አስተያይ። በትክክል ያልመለስክቸው ጥያቄዎች ካሉ በድጋሚ ክለሳቸው።

የትምህርቱ ዝርዝር

አገልግሎት መገለጫውን አገኙ ሰጠ

ዓላማ 1 የመንፈል ሰባዚነት የተባለውን የአገልግሎት ስጦታ ለይተህ እንድታውቅና የመንፈል ሰባዚነትን ተግባር በአጭሩ በጽሑፍ መግለጽ።

የሰጪውን ማንነት ማወቅ

በአገልግሎት ስጦታዎች ላይ የተመሠረተውን የመጀመሪያውን ክፍለ ትምህርት ባጠናንበት ወቅት ከርስቶስ የእነዚህ ስጦታዎች ሰጪ መሆኑን ተምረናል። የእነዚህ ስጦታዎች ሰጪ ማን መሆኑን በሚመለከት ኤፌ 4:11 እና 1ቆሮ 12:28 መካከል ምንም ልዩነት እንደሌላቸውም ተመልክተናል። ይህንንም ስንል እግዚአብሔር በሦስትነት አንድነት ማለትም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ ክርስቶስና አብ አንድ መሆናቸውን ተረድተናል። በመለኮት አካላት ውስጥ ክርስቶስ ሁለተኛው የመለኮት አካል ነው። ስለዚህም ክርስቶስ አምላክ ነው የሚለው አነጋገር ትክክለኛ አባባል እንደሆነም ተረድተናል።

ስለ ስጦታ ሰጪው በደብልዋ ማወቅ አስፈላጊ ነው። በኤፌ ምዕራፍ 4 ውስጥ ክርስቶስ ራስ መሆኑ ተገልጿአል። በቁ. 15 ላይ "... በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ..." ይላል። ወደ አካል የሚያደርስ ማንኛውም ነገር የሚተላለፈው በራስ በኩል ነው። ይህም በራስ በኩል የሚተላላፈው የአገልግሎት ስጦታዎችን ለአካሉ መታሰቢ የሚሆኑትንና የሚያስፈልጉትን ያጨምራል። "...ከእርሱም አካል ሁሉ በጅማትና በማስሪያ ምግብን እየተቀበለ እየተጋጠመም፣ እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ያድጋል" (ቆላ 2:19)።

የእኛ የሰዎች የተፈጥሮ ራስ ሦስት አጠቃላይ ተግባሮችን ያከናውናል፦

1. ያውቃል።
2. ፍላጎቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል።
3. ይቆጣጠራል።

የአገልግሎት ስጦታዎችን በሚመለከት እነዚህ ተግባሮች በቀጥታ ከርስቶስ ከሚያከናውነው ተግባር ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

ራስ የአካልን ፍላጎት ያውቃል

እግሮቻችን የአካላችንን ፍላጎት እያውቁም፣ እጆቻችንም ሆኑ እግሮቻችን ወይም የትኛቹም የአካላችን ክፍሎች ያዘንን ማድረግ አይችሉም።

አንዳንድ ጊዜ በክርስቶስ አካል ውስጥ የአካሉ ብልቶች የተወሰኑ አባላትን ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ የወንጌል ሰባኪዎች ወይም መጋቢያንና አስተማሪዎች አድርገው የመምረጥ መብት እንዳላቸው አድርገው ይቆጥራሉ። እንደዚህ ማድረግ ማለት እግር ለእጅ ሥራው ምን እንደሆነ እንደ መንገር ማለት ነው። ራስ የሆነው ክርስቶስ ብቻ ነው የአካልን ፍላጎት የሚያውቀው። ለእነዚህ የአካሉ ፍላጎቶች የትኞቹ የአካል ብልቶች ምን አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው እርሱ መወሰን ይችላል። የአካሉ ብልቶች እርስ በርሳቸው መረዳዳት ይችሉ ይሆናል፥ ሆኖም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን መስጠት አይችሉም። የአገልግሎት ስጦታዎችን መስጠት የሚችለው ራስ የሆነው ክርስቶስ ብቻ ነው።

ራስ የአካል ፍላጎት መሟላቱን ይከታተላል

አንዳንድ ጊዜ አጥንቶቻችን ወተት ካላገኙ በቀላሉ ስለሚሰበሩ አካላችን ተጨማሪ ወተት እንደሚያስፈልገው ራሳችን ያውቃል። ከዚያም በኋላ ይህ የወተት ፍላጎታችን ይሟላ ዘንድ ወተት መቅረቡን ያረጋግጣል። ልክ እንደዚሁ ራስ የሆነው ክርስቶስ የአካሉ ፍላጎት መሟላቱን ይከታተላል።

ራስ አካልን ይቆጣጠራል

ራሳችን ስውነታችንን ይቆጣጠራል። የአካላችን ፍላጎት መሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ራስ ለእያንዳንዱ የአካል ክፍላችን የተሟላ መመሪያ ይሰጣል። የአካላችን ጤናማ ክፍል የሆነው እግራችን ለአካላችን ምን እንደሚስማማው መወሰን አይችልም። ከዚያ ይልቅ ከራሳችን መመሪያ ተቀብሎ ለአካላችን ፍላጎት አገልግሎት ይሰጣል። እንደዚሁም ክርስቶስ ስጦታውን ለአካሉ ከሰጠ በኋላ ለአጠቃቀማቸው መመሪያ ይሰጣል።

(1). ክሚከተሉት ቃላት ውስጥ ራስ የሚያከናውነውን ተግባር ከሚገልጹት አንጻር ያሉትን ፊደሎች ክበቡዋቸው።

ሀ. መታዘዝ	መ. ማወቅ
ለ. መቆጣጠር	ሠ. ማቅረብ
ሐ. ማገልገል	

የስጦታው ተቀባይ ተገልጿል

ማንኛውም ስጦታ ተቀባይ ሊኖረው እንደሚገባ የታወቀ ነው። እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባን አማኞችና መላው ምዕመናን በመቀበል ተግባር ተሳታፊ መሆን እንዳለባቸው ነው። ግለሰብ አባላት የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ በሚያገኙ ጊዜ ይህንን ስጦታ ያገኙት ለአካሉ የተሰጠ ይሆናሉ።

አሁን የእኛ ትኩረት ለወንጌል ሰባኪነት የሚመረጡት እንማን እንደሆኑ ወይም የዚህ አገልግሎት ስጦታ ተቀባዮች ማን መሆን እንደሚገባቸው

ለማወቅ ነው። እያንዳንዱ አባል የወንጌል ሰባኪ ሊሆን የሚገባበት ሁኔታ አለ። "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፣ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤ ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማር 16:15-16)። ምናልባት አንድ ሰው፦ "ታዲያ፣ ይህ እኔን አይመለከተኝም፣ ያ ትዕዛዝ የተሰጠው የተለዩ ሐዋርያዎች ለሆኑት ለመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት፥ ነው" በማለት ይናገር ይሆናል።

ለአሥራ አንዱ የተነገረውን ሌላውን የእግዚአብሔር ቃል ክፍልም ልንመለከት ይገባል። "ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴ 28:20)። ይህም ትእዛዝ የተሰጣቸው አዲሶቹን አማኞች እንዲያስተምሩአቸው ነበር። "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" የሚለውን ትዕዛዝ መቀበላቸው እውነት ነው። ነገር ግን ልብ ልንለው የሚገባን ለአዲስ አማኞች ትዕዛዙቱን ሁሉ እንዲጠብቁ እንዲያስተምሩ መታዘዛቸውንም ጭምር ነው። ስለሆነም አማኞች ሁሉ ወንጌል ሰባኪዎች መሆን እንዳለባቸው እንረዳለን። ይህን እንጂ የወንጌል ሰባኪነት አገልግሎት ስጦታ ያለው በአንዳንድ መንገዶች ከሌሎች ለየት ይላል።

እግዚአብሔር የትኞቹን የአካሉን ብልቶች እንደሚገባ በወንጌል ሰባኪነት እንደሚጠቀምባቸው ያውቃል። አገልግሎታቸውን ሲጀምሩ እንደ ወንጌል ሰባኪዎች ሆነው ላይጀምሩ ይችላሉ። ከመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ሌላ በሐዋርያት ሥራ የምናውቃቸው ሁለት የወንጌል ሰባኪዎች ፊልጶስና እስጢፋኖስ ነበሩ። ሁለቱም ሲጀምሩ ግንዘብ ያገሮች ነበሩ። "የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ አይደለም። ወንድሞች ሆይ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፥ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን። እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።" (የሐዋ 6:2-3)። " . . . እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን፣ ፊልጶስንም . . . መረጡ" (የሐዋ 6:5)።

ለዚያ አገልግሎት ሊሰጥም ተመርጠው ነበር፣ ነገር ግን ከዚያ ከተመረጠው ቡድን ወንጌል ሰባኪዎች የሆኑት እስጢፋኖስና ፊልጶስ ብቻ ነበሩ። ምናልባት ከመጀመሪያው የወንጌል ስብከት አገልግሎት በኋላ እስጢፋኖስ ቢገደልም፥ ፊልጶስ ግን ጥቂት ቆይቶ በሐዋ 21:8 ላይ የወንጌል ሰባኪ ተብሎአል። "... በወንጌላዊው ፊልጶስ ቤት ገብተን በእርሱ ዘንድ ተቀመጥን" ፊልጶስ የወንጌል ሰባኪ የሆነው በ33 ዓ.ም ነበር፣ ሆኖም እስከ 60 ዓ.ም ድረስ የወንጌል ሰባኪ ነበር። ይህም የሚያመለክተው የወንጌል ስብከት አገልግሎት የሕይወት ጥሪ እንደነበረ ነው።

እስጢፋኖስና ፊልጶስ ለዚህ ታላቅ ኃላፊነት ከተመረጡበት ምክንያቶች አንዱ ለጌታ ሥራ የነበራቸው ታማኝነት ሊሆን ይችላል። ለተሰጣቸው ኃላፊነት ታማኞች የሆኑትን እግዚአብሔር እንዴት ብድራታቸውን እንደሚከፍላቸው ለማወቅ ሉቃስ 19:11ን አንብብ። እነዚያ ሁለት አማኞች

የቤተ ክርስቲያን ራስ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል ሰባኪዎች እንዲሆኑ የተጠሩበት ሌሎች ምክንያቶችም ነበሩ። "በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ ነበሩ"። "እስጢፋኖስም ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ...." ይላል (የሐዋ 6:8)።

የወንጌል ሰባኪዎች እንዲሆኑ በቤተ ክርስቲያን ራስ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚመረጡት በብዙ ምክንያቶች ነው። ከእነዚህም ምክንያቶች ወይም መመዘኛዎች መካከል ታማኝነት፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ በጥበብ፣ በእምነት፣ በኃይል መሞላት ይገኙበታል። ምናልባት እግዚአብሔር ሌሎች መመዘኛዎችንም ይመለከት ይሆናል። ማንኛውም ሰው ሳያውቃቸው በፊት እግዚአብሔር እነማን ትክክለኛው መመዘኛ እንዳላቸው እንደሚያውቅም ማስታወስ ይገባናል። ለምሳሌ እግዚአብሔር አንድ ወጣት ራሱም ሆነ፥ ሌላ ማንም ሰው ተፈላጊዎቹ መመዘኛዎች እንዳሉት ሳያውቅ የወንጌል ሰባኪ እንዲሆን ሊመራው ይችላል። ሳሙኤልን በእስራኤል ላይ ነቢይ እንዲሆን የጠራው ገና በጣም ልጅ በነበረበት ጊዜ ነበር። (1ሳሙ 31 ተመልከት)።

እንግዲህ በዚህ አገልግሎት ተቀባይነትን የሚያገኘው እግዚአብሔር መመዘኛውን እንደሚያሟላ የሚያውቀው ወይም ለዚያ አገልግሎት የሚያበቃው አማኝ ነው።

(2). ይህ የተለየ የአገልግሎት ስጦታ ያላቸው የወንጌል ሰባኪዎች እነማን መሆን እንደሚገባቸው ውሳኔ የሚሰጠው ማነው?

ሀ. ሐዋርያት
ለ. የቤተ ክርስቲያን ራስ (ኢየሱስ)
ሐ. የክርስቶስ አካል (ቤተ ክርስቲያን)
መ. ሌላው የአካሉ ብልት

(3). ለወንጌል ሰባኪነት ከተመረጡት ልንጠብቃቸው ከሚገባን መመዘኛዎች ጥቂቶቹ የትኞቹ ናቸው? በትክክለኛው መልስ አንጻር ያለውን ፊደል ክበቡ።

ሀ. በእምነትና በኃይል የተሞላ
ለ. ረጅም ርቀት የመጓዝ ችሎታ
ሐ. በቤተ ክርስቲያን ታማኝ የሆነ
መ. በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞላ

ስጦታው የሚያከናውነው ሲብራራ

የወንጌል ሰባኪ ዋና ተግባር ምን እንደሆነ "የወንጌል ሰባኪ" ከሚለው ቃል መረዳት ይቻላል። "የወንጌል ሰባኪ" ማለት "የምሥራች የሚያበስር" ማለት ነው። በዓለም ውስጥ ብዙ ዓይነት መልካም ወሬዎች ሊኖሩ ይችላሉ። የወንጌል ሰባኪዎች የሚያውጁት መልካም ዜና ግን ወንጌልን የሚያወሳ

ነው። ጳውሎስ በ1ቆሮ 15:1-4 ላይ ወንጌል ምን እንደሆነ አጭር መግለጫ ሲሰጥ፣ ወንጌልን በሚከተሉት ሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ያጠቃልላል።

1. ቅዱሳት መጻሕፍት እንደተናገሩት ክርስቶስ ለኃጢአታችን ሞተ።
2. ተቀበረ።
3. በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሣ።

የወንጌል ሰባኪው ዋና ተግባር የወንጌልን ቃል መናገር ቢሆንም ሌሎች ተግባሮችም አሉት። የወንጌሉን ቃል መናገር አብዛኛውን የሚታቀፈው ላላመኑት ወገኖች ነው። ሆኖም ጳውሎስ በኤፌ 4:12 ላይ ስለ አገልግሎት ስጦታዎች ሲናገር ".... ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ" ይላል፥ የመዘጋጀቱን ሃላፊነት በወንጌል ሰባኪዎች ላይ ያኖረዋል። ይህንን ለማከናወን እጅግ መልካም ከሆኑት መንገዶች አንዱ ምሳሌነትን ማሳየት ነው። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ለእኛ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን አሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የወንጌል ሰባኪ ተብሎ የተጠራውን የአንድ ሰው ሕይወትና አገልግሎት ብንመረምር የወንጌል ሰባኪን ተግባር በተሻለ መንገድ ለመረዳት እንችላለን። ያም ሰው ፊልጶስ የተባለው ሲሆን፥ ስለ እርሱ የተነገሩትን በጥንቃቄ ብናጠናቸው መልካም ነው።

1. ወደ ሰማርያ ሄዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው (የሐዋ 8:5)።
2. ለሕዝቡ ተናገረ ተዓምራትንም አደረገ (የሐዋ 8:6)።
3. ከተሞው ሐሴት እንዲያደርግ ምክንያት ሆነ (የሐዋ 8፤8)።
4. ያመኑትን አጠመቃቸው (የሐዋ 8:12)።
5. ሊያገለግል የሚገባውን አቅጣጫ በሚመለከት ለጌታ ታዘዘ (የሐዋ 8:26-27)።
6. ከመንፈስ ቅዱስ የተለየ ምሪት ተቀበለ (የሐዋ 8:29)።
7. ብቻውን ለነበረ ግለሰብ ወንጌልን ነግሮታል። (የሐዋ. 30-35)።
8. የወንጌልን ቃል በብዙ ከተሞች ሰብኳል (የሐዋ. 8:40)።
9. ለቤተሰቦቹ ወንጌልን አድርሷል (የሐዋ. 21:9)።

የእስጢፋኖስን ሕይወትና አገልግሎቱን በመመልከት ስለ ወንጌል ሰባኪ አገልግሎት ጥቂት ነገሮችን በተጨማሪ መማር እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ የእስጢፋኖስን አገልግሎት የወንጌል ሰባኪነት አገልግሎት ብሎ አይጠራም። የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ አድርግ።

1. በሕዝቡም መካከል ታላቅ ድንቅንና ተዓምራትን አደረገ (የሐዋ 6:8)
2. በታላቅ ጥበብና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አገለገለ (የሐዋ 6:10)
3. በተስደደ ጊዜ መልካም ባሕርይ አሳይቷል (የሐዋ 615)
4. የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽነትና በኃይል ሰበከ (የሐዋ 7:2-53)
5. የሕይወት መሥዋዕት የጠየቀ ቢሆንም እውነቱን ያለፍርሃት ተናገረ (የሐዋ 7:51-53)

6. የገደሉትን ሰዎች ይቅርታ አደረገላቸው (የሐዋ 7:60)
7. የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ሰማዕት ሆነ።

ሰባኪዎች ሁሉ ከፊልጶስና ከእስጢፋኖስ ጋር ተመሳሳይ ልምምድ እንዲኖራቸው አያስፈልግም። ሆኖም የዚህ ስጦታ መሠረታዊ ተግባር ምን እንደሆነ ከእነርሱ ብዙ መማር እንችላለን።

በማስተዋል ልንመለከተው የሚገባን ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በ2ጢሞ 4:5 ላይ "የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ" የሚለው ነው። ይህ ስጦታ ከሌላ ስጦታ ጋር ሊቀናጅ እንደሚችል ከዚህ አንድ ምልክት እናገኛለን። ከፍ ብለን የጠቀስነውን ትዕዛዝ የተቀበለው ጢሞቴዎስ፥ መጋቢ ነበር። የመጋቢን ዋና ተግባር በሚቀጥለው ምዕራፍ ላይ እናጠናለን። ለጊዜው መጋቢ የሆነ የወንጌል ሰባኪ ሊሆን እንደሚችል መረዳቱ መልካም ነው። እነዚህ ሁለት አገልግሎቶች የጋራ የሆነ ብዙ ነገር አላቸው።

(4). እውነት ከሆነው መግለጫ አንጻር ያለውን ፊደል ክበበው።

ሀ. የወንጌል ሰባኪ ማለት "የተላከ" ማሰት ነው።
ለ. የወንጌል ስብከት አገልግሎት አብዛኛውን ጊዜ ላላመኑ ነው።
ሐ. የወንጌል ሰባኪ አንድ ተግባር ብቻ አለው።
መ. መጋቢዎች የወንጌል ሰባኪን ሥራ ለመሥራት መሞከር አሰባቸው።

የአገልግሎቱ ዕድገት ሲገለጽ

ማንኛውም የአገልግሎት ስጦታ በክርስቶስ የተሰጠ ቢሆንም እንኳ ሊያድግ ይገባዋል። አንድ ሕጻን ትክክለኛውን ቅርዕ ይዞ የወጣ የሰው ዘር ሊሆን ቢችልም ዕድገቱን ጨርሷል ማለት አይደለም። ሙሱ ሰው ከመሆኑ በፊት ብዙ የዕድገት ዘመናትን ማሳለፍ ይኖርበታል። የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ የአካሉ ራስ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ መልካምና ፍጹም ስጦታ ነው። ይሁን እንጂ የተሟላ አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት ዕድገት ይጠበቅበታል። ስጦታውን ማሳደግ የሚቻልበት አራት መንገዶች እነሆ፦

አብዝቶ መጸለይ

አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የወንጌል ሰባኪዎችም ነበሩ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጸለዩት ጸሎት ምን እንደሚል ልብ ብለህ አስተውል። "እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን" (የሐዋ 6:4)። ከዚህ በተጨማሪ የሐዋ 3:21 እና 10:9 አንብብ። ጸሎት ወንጌላዊው በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ ያስችለዋል። በመንፈስ ቅዱስም በተሞላ ጊዜ ስብከቱ ውጤት ያስገኛል።

የእግዚአብሔርን ቃል አብዝቶ ማጥናት

መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ሰይፍ ነው (ኤፌ 6:17)። መንፈስ ቅዱስ ሊሠራበት የሚችለው በእጁ ላይ ያስቀመጥነውን ነገር ነው። ቃሉን በትክክል ማወቅ እስከምንችልበት ደረጃ የቃሉን ሰይፍ በእጁ እናኖራለን። የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ የወንጌል ስብከት አገልግሎት ዋና ተግባር ነው (2ጢሞ 2:15 አንብብ)።

የጌታን ድምፅ መስማትና መታዘዝን አብዝቶ መማር

የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ምሪት ሰወንጌል ስብከት አገልግሎት እጅግ አስፈላጊ ነው (የሐዋ 8:29፤ 9:10-17 እና 16:6-11 ተመልክት)። በልምምድ አማካኝነት እንማራለን። ልምምድ የራሳችንን ሃሳብ እግዚአብሔር ሊናገረን ከሚችለው እንዴት መለየት እንደምንችል ያስተምረናል።

የወንጌል ስብከት አገልግሎት አብዝቶ ማካሄድ

የወንጌል ስብከትን የአገልግሎት ስጦታ ሰማሳደግ ወንጌልን ከመስበክ የተሻለ መንገድ የለም። ይህ እውነት ሲ.ኤም. ዋርድ በተባሉ በዘመናችን እጅግ በጣም የተዋጣላቸው ሰው አገልግሎት ሲታይ ይችላል። ሆኖም እርሳቸውም ቢሆኑ ከመጀመሪያው ጀምሮ እንደዚህ የተዋጣላቸው አገልጋይ አልነበሩም። አገልግሎታቸውን እንደጀመሩ በአንድ አገልግሎት ወቅት ሊናገሩ ያቀዱትን ነገር ፈጽመው ረስተው ነበር። በዚያ ስብሰባ ስብከት ሳይሰብኩ ተመልሰው ሄዱ። ሆኖም ይህንን በማድረጋቸው የወንጌል ሰባኪ አልነበሩም ማለት አይደለም። ያንን ማድረጋቸው በወንጌል ስብከት አገልግሎት ተጨማሪ ልምድ ማትረፍ እንዳለባቸው ያመለክታል። ከዓመት ወደ ዓመት ይህንን ተግባር ለማከናወን ራሳቸውን ሰጡ። ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በዚህ ስጦታቸው ያገለግሉ ነበር። በአሁኑ ጊዜ በመላው ዓለም እጅግ በጣም የተዋጣላቸው የወንጌል ሰባኪ እንደሆኑ ይታወቃል።

(5). የወንጌል ስብከትን የአገልግሎት ስጦታ ሰማሳደግ የሚጠይቀው

ሀ. የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት
ለ. የእግዚአብሔርን ድምፅ ማዳመጥን መማር
ሐ. የወንጌል ስብከት ማካሄድ

አንዳንዶች መጋብያን አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ

ዓላማ 2 መጋብያንና አስተማሪዎች የተባሉትን የአገልግሎት ስጦታዎች ምንነት መግለጽ።

ዓላማ 3 የአገልግሎት ስጦታዎችን ሁሉ መዘርዘር፣ የተሰጡበትን ምክንያትና ተግባራቸውን መግለጽ።

የሰጪውን ማንነት ማወቅ

እስካሁን ባጠናነው ጥናት የአገልግሎት ስጦታዎችን ስለሚሰጠው ሦስት አስፈላጊ ነጥቦችን ተመልክተናል።

1. ስጦታዎችን የሚሰጠው ክርስቶስ እንደሆነ፣
2. ስጦታዎችን የሚሰጠው ክርስቶስ ራሱ አምላክ እንደሆነ፣
3. ስጦታዎችን የሚሰጠው ክርስቶስ የአካሉ ራስ እንደሆነም ተምረናል።

አሁን የስጦታዎች ሰጪ የሆነው ክርስቶስ አካሉን የሚያድን መሆኑን ለመማር ዝግጅታችንን እንቀጥላለን። "ክርስቶስ አካሉን የሚያድን እንደሆነ" (ኤፌ 5:23)። አዳኝ ማለት "ነፃ አውጪ" ማለት ነው። በአገልግሎት ስጦታዎ ች ነፃ አውጪ በመሆን ስጦታዎችን የሚሰጠው ከአካሉ ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው? በዚህ ሦስት የተለያዩ መንገዶች እንዳሉ እንመለከታለን።

ካለማወቅ ነፃ ያወጣል

አለማወቅ የእምነት ታላቅ እንቅፋት ነው። በአስተማሪዎች ስጦታ አማካኝነት ራስ የሆነው ክርስቶስ ከዚህ ችግር ነፃ ያወጣል። በአካሉ ውስጥ እንዳያኖር የሚከላከለውን አለማወቅ አስታማሪው እውቀትን በማካፈል ያስወግደዋል።

ከራስ ወዳድነት ነፃ ያወጣል

የመጋቢ - አስተማሪዎች ስጦታ በጣም ታላቁ ተግባር የአካሉን ብልቶች ከራስ ወዳድነት ነፃ ማድረግ ነው። ይህም የሚከናወነው ሰዎችን በክርስቶስ ላይ የተመሠረተ ሕይወት እንዲኖሩ በመምራት ነው።

ከፈተናዎች ነፃ ያወጣል

"ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል" (2ጴጥ 3:9)። ፈተናዎች የሕይወት አንድ ክፍል ናቸው። የአካሉ ብልቶች የሆኑ አማኞች እንኪን ፈተናዎች አለባቸው።

በመጋቢ - አስተማሪዎች ስጦታ አማካኝነት የስጦታዎች ሰጪ የሆነው ክርስቶስ ከፈተና ነፃ ያወጣናል። ይህንን ስንል አማኞች ከፈተናቸው ሁሉ በአንድ ጊዜ ያመልጣሉ ማለት አይደለም። ይህ ማለት በመጋቢ - አስተማሪዎች ስጦታ አማካኝነት ፈተናዎችን ሊያስከትሉ ከሚችሉት ሽንፈቶች ያመልጣሉ ማለት ነው። ከፈተናቸው ማትረፍንና ፈተናቸውንም ይበልጥ የተሻለ ሕይወት ለመኖር እንደ መሸጋገሪያ መጠቀም ይማራሉ።

አካሉን የሚያድን መሆኑና የመጋቢ አስተማሪዎች ስጦታ ሰጪነት። የስጦታ ሰጪው የክርስቶስ አንዳንድ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

(6). እውነት ክሆነው መግለጫ አንጻር ያለውን ራያል ክበበው።

ሀ. የአገልግሎት ስጦታ ሰጪ የሆነው አካሉን የሚያድን ተብሎ ይጠራል።
ለ. አዳኝ ማለት "የተሰወረውን የሚያገኝ" ማለት ነው።
ሐ. የመጋቢ - አስተማሪዎች አንዱ ተግባር አማኞችን በክርስቶስ ላይ የተመሠረተ ሕይወት እንዳይኖሩላቸው ነፃ ማድረግ ነው።
መ. መጋቢ - አስተማሪዎች አማኞች ከችግራቸው እንዲማሩ ወይም እንዲያተርፉ ይረዳሉ።

የስጦታው ተቀባይ ተገልጿል

ከአገልግሎት ስጦታዎች ሁሉ የመጋቢ - አስተማሪ ስጦታ በጣም የተለመደ ነው። ይህም ማለት ከሐዋርያት፣ ከነቢያትና ከወንጌል ሰባኪዎች ይልቅ ብዙ መጋቢ አስተማሪዎች አሉ ማለት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት በአካሉ ውስጥ ይህ የአገልግሎት ስጦታ ያላቸው አገልጋዮች አስፈላጊነት ከፍ ያለ በመሆኑ ነው። መጋቢ - አስተማሪ በክርስቶስ አካል ውስጥ ብዙ አስፈላጊ ሥራዎችን ማከናወን ይችላል።

ይህንን የአገልግሎት ስጦታ የሚቀበለው ማን ነው? ስለ ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች በምናጠናበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ራስ ከአገልጋዮቹ አንዳንድ ባሕርያትን ማግኘት እንደሚሻ አስተውለናል። እነዚህም ባሕርያት ታማኝነትን፣ ጥበብን፣ እምነትንና በመንፈስ ቅዱስና በኃይል መሞላትን ያጠቃልላሉ። እነዚህ ሁሉ የመጋቢ - አስተማሪነት ስጦታ ላለው አገልጋይ አስፈላጊዎች ናቸው። ሆኖም ከእነዚህ ሁሉ በላይ አንድ ሌላ ባሕርይ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም ባሕርይ ሰዎችን የማፍቀርና ለሰዎችም የመጠንቀቅ ባሕርይ ነው። በዚህም ምክንያት ነው "እረኛ" የሚለው ቃል ከመጋቢ - አስተማሪ አገልግሎት ጋር ተያይዞ የሚጠቀሰው። እረኛ መንጋውን ይወዳል፣ መንጋውንም ይንከባከባል።

የዚህ ስጦታ ሰጪ የሆነው ክርስቶስ ራሱ ለመንጋው ታላቅ አረኛ ነው። የአረኞች አለቃም ተብሎ ይጠራል። የመጋቢ - አስተማሪን ስጦታ የሚቀበሉት በዚህ አለቃ ሥር ሆነው የሚያገለግሉ የበታች አረኞች ናቸው። ይህም ማለት የአካሉ አዳኝ እንደሆነው የአረኞች አለቃ ሁሉ እነርሱም ያንኑ የመሰለ ፍቅርና መንጋውን የመንከባከብ ባሕርይ ሊኖራቸው ይገባል።

(7). የተወሰኑ አማኞች የመጋቢ- አስተማሪነት ስጦታ ይቀበላሉ። የአካሉ አዳኝ ለአካሉ እንዲህ ዓይነት ስጦታ ሆነው እንዲሰጡ ሰዎች በሚፈልግበት ጊዜ ከነዚህ ሰዎች የሚፈልገው ባሕርይ ምንድን ነው?

(8). አረኛ ከመጋቢ - አስተማሪ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ስጦታው የሚያከናውነው ሲብራራ

ከሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መጋቢ - አስተማሪነት ስጦታ ብዙ የሚናገረው ነገር አለው። መጋቢነትና አስተማሪነት የተባሉትን እነዚህን ሁለት ስጦታዎች በጋራ የምንመለከታቸው ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ሁለቱ እንደ አንድ ስጦታ እንደሆኑ ስለሚስማሙባቸው ነው። የቃላቶቹ ትርጉም *መጋቢ ከማስተማር አገልግሎት ጋር* ማለት እንችላለን።

የመጋቢ- አስተማሪን ተግባር ማጥናት ስንጀምር ወደ ኤፌ 4:11-12 መለስ በማለት፣ "እርሱም አንዳንዶቹ .... አረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ..... ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ....." የሚለውን ቃል መመልከት ይገባናል።

የአገልግሎት ስጦታዎች ተግባር የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት ማዘጋጀት እንደሆነ ተገንዝበናል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንዳንድ መጻሕፍት ሙሉ በሙሉ በተለይ ለመጋቢያን የተጻፉ ናቸው።እነዚህ መጻሕፍት የመጋቢያን መልዕክቶች በመባል ይታወቃሉ። ለጢሞቴዎስ የተጻፉት ሁለቱ መልዕክቶችና የቲቶ መልዕክት በእነዚህ መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው። መጻሕፍቱ ተግባራቸውን በሚመለከት በቀጥታ ለመጋቢያን የተጻፉ በመሆናቸው እያንዳንዳቸውን ደጋግመህ ልታነባቸው ይገባል።

የመጋቢ - አስተማሪዎችን ተግባር ለመረዳት እንዲረዳን የበግ መንጋ አረኛን በምሳሌነት ወስደን እንመለከታለን።

እረኛው በጎቹን ይወዳል፣ ስለሚወድም ሕይወቱን ለእነርሱ መሥዋዕት ሊያደርግ ፈቃደኛ ነው።

ዮሐ 10:11-15ን አንብብ። የእረኞቹ አለቃ ለበታች እረኞች ታላቅ ምሳሌ ነው። መጋቢ- አስተማሪው በቅድሚያ መንጋውን የሚይዘድ ከሆነ ሊያደርግላቸው የሚችለው በጣም ጥቂት ነገር ነው። የዐጋ ስጦታዎች ሁሉ ፍሬያማ ተግባር እንዲያከናውኑ መሠረቱ ፍቅር ነው።

እረኛው መንጋውን ይመግባል

"የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ትወደኛለህን? ..... ግልገሎቼን አስማራ .... ጠቦቶቼን ጠብቅ" እለው (ዮሐ 21 15-16)። ጴጥሮስ የመጀመሪያ መልዕክቱን ሲሸኝግሌዎች (ሰመጋቢ) በጻፈበት ጊዜ፣ "በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ ..... በበጎ ፈቃድ ..... ጎብኙት" በማለት ተናግሯል (1ጴጥ 5:2)።

ለመንጋው ሊቀርብ የሚገባው ምግብ ግልገሎቹም ሆኑ ጠቦቶቹ ሲመዝኑት የሚችሉት ሊሆን ይገባል። ስግልገሎቹ ማለትም ለአዲሶቹ አማኞች ወተት የሆነው የእግዚአብሔር ቃል አለ (1ጴጥ 2:2፣ ዕብ 5:13 ተመልከት)። ለበሰሉት አማኞች ጠንከር ያለ ምግብ ሊኖር ይገባል (1ቆሮ 3:1-2 እና ዕብ 5:14 አንብብ)።

መጋቢ-አስተማሪ ለነበረው ለጢሞቴዎስ ጳውሎስ የሰጠውን መመሪያ እስኪ ተመልከት። "ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ" (2ጢሞ 2:2)። ጢሞቴዎስ እንዲያስተምር ጳውሎስ በተደጋጋሚ ነግሮታል። "ይህን እዘዝና አስተምር" (1ጢሞ 4:11) "እነዚህን አስተምርና ምከር" (1ጢሞ 6:2)፣ የጌታም ባርያ ሰለው ሁሉ ገር ለማስተማርም የሚበቃ ሊሆን...." (2ጢሞ 2:24)።

እረኛው ለመንጋው መሪ ነው

የበጎቹ እረኛ በጎቹን እንዲመራ ይጠበቅበታል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል" (ዮሐ 10:4) ይላል። ለእግዚአብሔር መንጋ የእረኞች አለቃ የሆነው መጋቢ - አስተማሪ ሰሆኑት እጅግ ታላቅ ምሳሌ ነው። የእረኞች አለቃ ለእርሱ ምሳሌ እንደሆነ ሁሉ መጋቢ አስተማሪውም ለመንጋው ምሳሌ ሊሆን ይገባል። "ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ግዛነሮቻችሁን በኃይል አትግዙ" (1ጴጥ 5:3)፣ "በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑት ምሳሌ ሁን" (1ጢሞ 4:12)። መልካም መሪ ከሚከተሉት ፊት በመሄድ ምሳሌ ይሆንላቸዋል።

እረኛው መንጋውን ከጥቃት ይከላከላል

ዮሐ 10:11-12ን አንብብ። "ትጠብቁእት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ..... እኔ

አውቃለሁ" (የሐዋ 20:28-29)። ይህ የመጋቢ - አስተማሪው ታላቅ ሃላፊነት ነው። መንጋውን ከጥቃት ለመከላከል ሊያደርግላቸው የሚችለው ብርቱ መከታ የተማሳ የእግዚአብሔር ቃል መረዳት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው።

አረኛው የመንጋውን መብዛት ዓላማ ያደርጋል

አረኛ በጎቹ እንዲዋለዱና እንዲበዙለት ይፈልጋል። የሚያደርገው ነገር ሁሉ በአብዛኛው በዚህ ዓላማ የተመራ ነው። የመጋቢ - አስተማሪም ልብ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ዓላማ አለው። የእረኞቹ አለቃ እንዲህ በማለት የተናገረውን ልብ አድርግ። "ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል" (ዮሐ 10:16)። በዚህ ምክንያት ነበር ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ "የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ" ብሎ የፃፈለት (2ጢሞ 4:5)። መጋቢ - አስተማሪው እንደ ወንጌላዊ ሆኖ ሊያገለግል ሁለት ነገሮች ይሆናሉ። በቅድሚያ ወደ ክርስቶስ አካል አዲስ አባላትን ያመጣል። በሁለተኛ ደረጃ፥ በሚያሳየው ምሳሌነት፥ ምዕመናኑ አዳዲስ አባላትን ወደ መንጋው እንዴት እንደሚያመጡም ያስተምራቸዋል።

9. የሚከተለውን ዓረፍተ ነገር በትክክል ሊያጠናቅቅ ከሚችለው መግለጫ አንጻር ያለውን ፊደል ክበበው።

መጋቢ - አስተማሪ እረኛን ይመስላል፤ ምክንያቱም. . .

ሀ. ምዕመናኑን ይወዳል፣ ይንከባከባቸውማል።
ለ. ለምዕመናኑ የእግዚአብሔርን ቃል፣ ወተትና ጠንካራ ምግብ ይመግባቸዋል።
ሐ. ጠላቶቻቸውን እንዴት መዋጋት እንዳለባቸው እንዲያውቁ እንደ ፈለጋቸው እንዲኖሩ ይፈቅድላቸዋል።
መ. በእነርሱ ላይ ገዢ ይሆናል።

የምዕመናን መብዛት ዓላማው የክርስቶስን አካል ለማነፅ ነው። አካሉን በማነፅ የክርስቶስ ዓላማ ምንድን ነው? የዚህን ጥያቄ መልስ ጳውሎስ በኤፌ 4:13-16 ላይ ያብራራልናል። የተጠቀሰውን ምንባብ በሚገባ ከመረመርህ በኋላ የሚከተሉትን ነጥቦች አስተውል።

የእምነት አንድነት

የእገልግሎት ስጦታ በተሰጣቸው ሰዎች ላይ ምን ዓይነት ታላቅ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል! በአካሉ ውስጥ ያሉትን አማኞች ወደ እምነት አንድነት በማምጣት በዙሪ ጥረት ሊያደርጉ ይገባል። ሕብረት ማለት አንድነት ማለት ነው (መዝ 133:1)። ይህ የእምነት አንድነት ሊደረስበት የሚችልበት በጣም ቀላሉ ሁኔታ የመንፈስ አንድነትን በመጠበቅ ነው (ኤፌ 4:3)። የመንፈስ አንድነት፥ የእምነት አንድነት እንደሚገባ ፍሬ የሚያፈራበት ለምለም አፈር ነው። የመንፈስ አንድነት ከሌለ የእምነት አንድነት ቀዝቃዛ፥

እንዲያውም ሙት ነው። የመንፈስ አንድነት በቀላሉ የሚጠበቅ አይደለም። ስለዚህም ጉዳዩ ብዙ ጥረት ይጠይቃል። የፍቅርንና ይቅርታ የማድረግን አመለካከት የሚጠይቅ ይሆናል።

የእምነት አንድነት ማለት "ተመሳሳይ በሆኑ ነገሮች ማመን ማለት ነው። ይህንን ደግሞ በድጋሚ ስንፈታው መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው ማመን" ነው። ስለዚህም የአገልግሎት ስጦታዎች ክፍል ዓላማ የክርስቶስ አካልን ወደ እምነት ማምጣት ነው።

የመረዳት አንድነት

መረዳት በጣም ለየት ያለ እውቀት ነው። ይህ "የእግዚአብሔርን ልጅ የምናውቅበት" እውቀት ነው (ኤፌ 4:13)። እንዲሁ ስለ ክርስቶስ ማወቅ ብቻ አይደለም። ስለ ክርስቶስ ማንነት መረዳት ወይም ቢያንስ ቢያንስ እርሱን በሦስት አንጻር ማወቅ ነው (ፊልጵ 3:10)።

1. የትንሣኤውን ኃይል መለማመድ
2. የመከራው ተካፋይ መሆን
3. በሞቱ፥ ከእርሱ ጋር አንድ መሆን

የአገልግሎት ስጦታዎች በእነዚህ አስፈላጊ እውቀቶች ወይም መረዳቶች መላውን አካል ወደ አንድነት ያመጡ ዘንድ የተሰጡ ናቸው።

በማስተዋል የበሰሉ ምዕመናን

መጽሐፍ ቅዱስ "ፍጹማን ስለሆኑ ሰዎች" ይናገራል። ፍጹም ማለት "ሙሉ መሆን" ማለት ነው። ለቤተ ክርስቲያን ስጦታ ሆነው የተሰጡ ሁሉ ሊጠቀሙበት የሚገባ መሣሪያ መላው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ሰዎችን እንደ መመሪያ ቃል አድርገው ሊጠቀሙበት ይገባል። "... የክርስቶስም ሙላት፥ ወደሚሆን ወደ ሙላት፥ ልክ እስክንደርስ..." የሚለው ሊሆን ይገባል (ኤፌ 4:13)።

በማስተዋል የበሰሉ ምዕመናንን ማሳደግ በሚለው ከፍተኛ ዓላማና እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ባለው እጅግ ከፍተኛ ዓላማ መካከል አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት አለ። ያም ዓላማ የልጁን መልክ በግርማ የሚያንጸባርቁ ብዙ ልጆችን ማስገኘት ነው (ሮሜ 8:28-30)። የአገልግሎት ስጦታዎች እንደሚገባ በሚሠሩበት ጊዜና አማኞችም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሲያድጉ አዳዲስ አባላት ወደ አካሉ ይጨመራሉ። ጤናማ የደረጀ አካል ራሱን የመሰለ ሌላ አካል ያፈራል።

የአገልግሎቱ ዕድገት ሲገለጽ

የመጋቢ-አስተማሪዎችን አገልግሎት ለማሳደግ የሚፈለጉት ሁኔታዎች የወንጌል አገልግሎት ስፋትን ለማሳደግ ከሚፈለጉት ሁኔታዎች ጋር በጣም የተቀራረበ ነው።

10. አማኝ እንደመሆንህ የስጦታዎች ሰጪ የሆነው ክርስቶስ በአንተ ሕይወት ውስጥ ሲሠራ ምን እንደሚለማህ በራስህ አገላለጽ ጻፍ። ያህንን ጥያቄ ለመመለስ በማስታወሻ ደብተርህ ተጠቀም።

የአገልግሎት ስጦታዎችን ማዳበርን በተመለከተ የተማርካቸውን ትምህርቶች በድጋሚ ከለሳቸው።

የመከራ ፈተና

ምርጫህ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ በትክክለኛው መልስ አንጻር ያለውን ፊደል ክበበው።

1. የአገልግሎት ስጦታዎች_____ናቸው።

ሀ. መጋቢ - አስተማሪዎች
ለ. የመንፈስ አንድነት
ሐ. አጵሎስ
መ. ወንጌላውያን
ሠ. ሐዋርያት
ረ. ፍቅር
ሰ. ነብያት

2. በትምህርታችን ውስጥ የአገልግሎት ስጦታዎች ሰጪ የሆነው ማንነቱን ልንረዳ ከሚያስችሉን ስሞች ጋር እንደተነጻጸረ ተመልክተናል። ከስጦታዎቹ ሰጪ ከክርስቶስ ጋር ሊገናዘቡ የማይገባቸውን ስሞች ወይም ቃላት ክበባቸው።

ሀ. ራስ
ለ. መንፈስ ቅዱስ
ሐ. አካል
መ. እግዚአብሔር

3. የአገልግሎት ስጦታዎች ዋና ተግባር _____ማነጽ ነው።

ሀ. የቤተ ክርስቲያን መጋቢውን
ለ. ግለሰብ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላትን
ሐ. ቤተ ክርስቲያንን እንደ አንድ አካል

4. የአገልግሎት ስጦታዎች ሊዳብሩ እንደሚችሉ ተመልክተናል፣ ይህንንም ማድረግ የሚቻለው

ሀ. በጸሎት ነው
ለ. የጌታን ድምፅ ሰምቶ መታዘዝን በመማር ነው
ሐ. የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ነው
መ. ስጦታውን በመለማመድ ነው

5. በቃልህ ያጠናኸውን 1ቆሮ 13:5-6 ጻፍ።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

1. ለ. መቆጣጠር መ. ማወቅ ሠ. ማቅረብ

6. ሀ. እውነት ሐ. ሐሰት
   ለ. ሐሰት መ. እውነት

2. ለ. የቤተ ክርስቲያን ራስ (አ.የሱስ)

7. ምዕመናንን የሚወድና የሚንከባከብ ሰው ይፈልጋል።

3. ሀ. በእምነትና በጎይል የተሞላ
   ሐ. በቤት ክርስቲያን ታማኝ የሆነ
   መ. በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞላ

8. እረኛ በጎቹን ይወዳል ይንከባከባቸውማል።

4. ሀ. ሐሰት ሐ. ሐሰት
   ለ. እውነት መ. ሐሰት

9. ሀ. ምዕመናኑን ይወዳል ይንከበከባቸውማል።
   ሰ. የእግዚአብሔርን ቃል ወተትና ጠንክር ያሰ ምግብ ሰምእመናኑ ይመግባል።

5. ሀ፣ ሰ እና ሐ

10. የአንተ መልስ።

5 ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች 1

ትምህርት

ማገልገል፣ ማስተማር፣ መምከር

የአገልግሎት ስጦታዎች ስለተሰጡት የጀመርነውን ጥናታችንን በሚገባ እከናውነናል። በኤፌሶን ምዕራፍ 4 ላይ የተዘረዘሩት እምስት ስጦታዎች ሲሆኑ እኛ ግን መጋቢያንና አስተማሪዎችን እንደ አንድ ስጦታ አድርገን በመውሰድ አቅርበናቸዋል።

ባለፈው ክፍለ ትምህርታችን ስለ ወንጌል ሰባኪዎችና ስለ መጋቢ አስተማሪዎች አጥንተናል። አያንዳንዱ አማኝ የወንጌል ስብከትን ሥራ መሥራት ቢኖርበትም፥ አንዳንድ አባላት ግን ወንጌል ሰባኪዎች ለመሆን የተለየ ጥሪ ይኖራቸዋል። ከዚህም ሌላ ከሌሎቹ ሦስት ስጦታዎች ይልቅ ብዙ አማኞች መጋቢ - አስተማሪዎች ሰመሆን የበሰጠ እድል እንዳላቸው ተመልክተናል። ኢየሱስ ክርስቶስ የአገልግሎት ስጦታዎችን በመስጠት ያለው የተለየ ዓላማ ምን እንደሆነ ለማወቅ እንድንችል የተለይ ትኩረት ተሰጥቶታል።

አሁን ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች ስለተባሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ምድቦች ለማጥናት ዝግጅታችን እንቀጥላለን። ብዙ መጋቢ-አስተማሪዎች ቢኖሩም እንኳን በክርስቶስ አካል ውስጥ በዚህ ወይም በሌሎች በተመለከትናቸው ስጦታዎች ለማገልገል ስጦታዎቹ ያልተሰጡአቸው በርካታ አባሎች አሉ። ይህም ሲባል ታዲያ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሏቸውም ማለት አይደለም። በዚህ ክፍለ ትምህርት ስለ ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎችና ብዙ አማኞችም እነዚህ ስጦታዎች እንዲት ሊኖሯቸው እንደሚችሉ እንመለከታለን።

ከአገልግሎት ስጦታዎች እንዱን በተመለከተ ምንም የተለየ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ካልተሰጠህ፥ ይህን ክፍለ ትምህርት ከማጠናቀቅህ በፊት እግዚአብሔር ቀደም ብሎ የሰጠህ አንድ ስጦታ እንዳለ ልታውቅ የመቻልህ ዕድል በጣም ከፍ ያለ ነው። መንፈስ ቅዱስ እንዲመራህ፥ ትምህርቱን እያጠናህ እያለህ ጸልይ።

የክፍለ ትምህርቱ እከፋፈል

- የማገልገል ስጦታ
- የማስተማር ስጦታ
- የመምከር ስጦታ

ይህንን ክፍለ ትምህርት በምታጠናቅቅበት ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

- ከአገልግሎት ስጦታዎች ሦስቱን መዘርዘርና እንዴት እንደሚሰሩ መግለጽ
- ሦስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች የተሰጡበትን ዓላማ መግለጽ
- አማኞች እንዴት የአገልግሎት ስጦታዎችን ማዳበር እንደሚችሉ መረዳት።

1. የሐዋ. ምዕራፍ 1-6 አንብብ። እያንዳንዱን ምዕራፍ ስታነብ በማስታወሻ ደብተርህ የተገነዘብካቸውን ልዩ ልዩ የአገልግሎት ዓይነቶች መዝግባቸው። ለምሳሌ፦ ምዕራፍ 4 ላይ የመስጠት አገልግሎትን እናገኛለን። ከዚህ ምዕራፍ ቁ. 34-37 ተመልከት።

2. 1ቆሮ ምዕራፍ 13 በቃልህ ማጥናት ቀጥል። በማስታወሻ ደብተርህ ከቁ. 1-7 በቃልህ ያጠናኸውን ጻፍ። ይህንን ክፍለ ትምህርት በምታጠናቅቅበት ጊዜ የመጀመሪያዎቹን ስምንት ቁጥሮች በቃልህ መናገር መቻል አለብህ።

3. ይህንን ክፍለ ትምህርት በሙሉ በጥንቃቄ አንብበው። በተለይ ልታስታውሳቸው የምትፈልጋቸውን ክፍሎች አስምርባቸው።

4. በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ላሉት የመከራ ፈተናዎች መልስ ስጥ። በትክክል ያልመለስካቸው ጥያቄዎች ካሉ ወደ ክፍለ ትምህርቱ መለስ ብለህ ትክክለኛውን መልሶች ሰማግኘት ሞክር።

የማገልገል ስጦታ

ዓላማ 1 የማገልገልን ስጦታ ምንነት መግለጽና በዚህ ስጦታ ሊካተቱ የሚችሉትን የተግባር ዓይነቶችን መዘርዘር።

በተለይ በሮሜ 12 በተዘረዘሩት ስጦታዎች ላይ የተመሠረተውን ይህንን ክፍለ ትምህርት ለመጀመር የተዘጋጀን ቢሆንም ጥቂት መግለጫ መስጠት አስፈላጊ ይሆናል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በትክክል መመደብ በጣም አስቸጋሪ ነው። ስለሆነም ከአንዱ ክፍለ ትምህርት ወደ ሌላው ክፍለ ትምህርት ስንሸጋገር አንዳንድ የሃሳብ ድግግሞሽ እንዳለ እንገነዘባለን። ይህ ሊያሳስበን አይገባም፣ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ ስጦታዎች የሚገኙት ከዚያው ከአንዱ ምንጭ ስለሆነ ነው።

በሮሜ ምዕራፍ 12 የስጦታዎቹ ዝርዝር በትንቢት ስጦታ ይጀምራል። የትንቢት ስጦታ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ዝርዝር ውስጥ ስለተጠቀሰ በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ትኩረት አንሰጠውም። በ1ቆሮ 12 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተዘርዝረዋል። በዚህም ዝርዝር በሦስት ምድቦች ያሉት ስጦታዎች ይገኙበታል።

የስጦታው ምንነት ሲገለጽ

"..... አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ ....." (ሮሜ 12:7)። «ማገልገል" የሚለው ቃል በግሪክ አዲስ ኪዳን ብዙ ጊዜ ተጠቅሶአል። በቅድሚያ የተጠቀሰው በሮሜ 12:7 ላይ ሲሆን በተጨማሪ በ2ቆሮ 8:4 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል። "ለቅዱሳን በሆነው አገልግሎት እንዲተባበሩ ይህን ቸርነት በብዙ ልመና ከእኛ ይለምኑ ነበር" ይላል። ይህ ጥቅስ በመቄዶንያ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ የተወሰኑ ሰዎች፣ ጳውሎስና ከእርሱ ጋር ያገለግሉ የነበሩት፣ በችግር ውስጥ ለነበሩት ለአንዳንድ አማኞች የሚያስፈልጋቸውን በማቅረብ በኩል እንዲተባበሯቸው እንደጠየቁ የሚልጽ ነው።

«ማገልገል" የሚለው ቃል ከነዚህ በተጨማሪ የተጠቀሰበት አንድ ሌላ ሰፍራ በ2ቆሮ 9:1 ላይ ሲሆን "ሰቅዱሳን ስለሚሆነው አገልግሎት....." ይላል። በዚህም ላይ ያለው በ2ቆሮ 8:4 ላይ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ነው። ስለሆነም ሃሳቡን ስናጠቃልል በአጠቃላይ የማገልገል ስጦታ ሌሎችን በች ግራቸው ከመርዳት ጋር የተያያዘ ነው። ይህ በጣም ሰፊ ግንዛቤ ሊኖረው ይችላል። በአንድ በኩል የማገልገል ስጦታ ሌሎቹን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በሙሉ የሚመለከት ነው። ይህም ሊሆን የቻለው ስጦታዎች በሙሉ የተሰጡን ሰዎችን እንድናገለግል እንዲረዱን ነው። በዚህ ክፍለ ትምህርት ይህ ስጦታ በተሰየ የሰዎችን ቁሳዊ ፍላጎት በማሟላት በኩል የሚኖረውን ድርሻ እንመለከታለን።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

በሐዋ 9:36-41 ላይ የዶርታን ታሪክ እናገኛለን። ዶርታ የማገልገል ስጦታ ነበራት። "እርሷም መልካም ነገር የሞላባት ምጽዋትም የምታደርግ ነበረች" (የሐዋ 9:36)። እንዴት ዓይነት ነገሮችን ነበር የምታደርገው? ለድሀ መበለቶች ልብስ ትሰፋላቸው ነበር። በድንገት በሞተች ጊዜ ጴጥሮስ ወደ ቤቷ ሄደ። "መበለቶችም ሁሉ እያለቀሱ ዶርታ ከእነርሱ ጋር ሳለች ያደረገቻቸውን ቀሚሶችንና ልብሶችን ሁሉ እያሳዩት በፊቱ ቆሙ" (የሐዋ 9:39)።

ዛሬም ቢሆን በዓለም ውስጥ መበለቶችና ወላጆች የሌሏቸው ልጆች አሉ። በመላው ዓለም በዙሪያችን ብዙ ችግረኞች ሰዎች አሉ። በማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል ቢሆን እንደዚህ ዓይነት ሰዎች አይታጡም። በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ዶርታ የነበራትን የመሰለ የማገልገል ስጦታ ያላቸው አንዳንድ ሰዎችን ማግኘት ቢቻል እንዴት ድንቅ ይሆን ነበር? ዶርታ የስፌትና ልብሶችን የመሥራት የተፈጥሮ ተሰጥኦ ሊኖራት ይችላል። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በተፈጥሮ ተሰጥኦ ላይ ለተቸገሩ ሰዎች ጥልቅ የሆነ ሸክም ጨምሮላታል። የዚህም ውጤት የማገልገል ስጦታ ነበር። የተፈጥሮ ተሰጥኦ ማግኘት ብቻውን በቂ አይደለም። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተፈጥሮ ተሰጥኦቻችንን ሲረክበው፥ በድንቅ ሁኔታ ወደ አገልግሎት ስጦታዎች የሚለውጥበት ድንቅ መንገድ ይኖረዋል።

ስለ እስጢፋኖስና ስለ ፊሊጶስ ቀደም ብለን አጥንተናል። ሁለቱም ወንጌል ሰባኪዎች ሆነው ነበር። ሆኖም የወንጌል ስብከት ስጦታን ከማግኘታቸው በፊት የማገልገል ስጦታ ነበራቸው። የቤተ ክርስቲያንን ግንዘብ እንዲያስተዳድሩ መመረጣቸውን ቀደም ሲል ተመልክተናል። ምናልባት እነዚህ ሁለቱ እያንዳንዳቸው የተወሰነ የገንዘብ አያያዝ ስጦታ ሳይኖራቸው አይቀርም ይሆናል፥ ሆኖም የመንፈስ ቅዱስ አሠራር እስካልተጨመረበት ጊዜ ድረስ ያ ተሰጥኦ የማገልገል ስጦታ አልነበረም። ያንን የማገልገል ስጦታ ባገኙ ጊዜ ግን በቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን መበለቶች ችግር ለማቃለል በቁ።

ብዙዎች፥ የተፈጥሮ ስጦታዎች በማገልገል ስጦታነት ሊያገልግሉ ይችላሉ። ይህም ሊሆን የሚችለው ተሰጥኦው ያለው ሰው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞላ እንደሆነ ነው። ለምሳሌ ያህል የድምጻዊነት ተሰጥኦ ስላለው ሰው ብናስብ መቼም ድምጻዊነት ወይም በዘፈን ጣፋጭ ዜማን ማሰማት የማገልገል ስጦታ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ ተሰጥኦ ነው። ሆኖም ይህ ተሰጥኦ ያለው ሰው በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ጊዜ ተሰጥኦው የማገልገል ስጦታ ሊሆን ይችላል።

በተፈጥሮ ያገኘኸው ተሰጥኦ አለህ? ካለህ ያንን ተሰጥኦ ለጌታ አስረክበው፥ ጌታም ብዙዎች ሊባረኩበት የሚያስችላቸው ስጦታ እድርጎ ሊጠቀምበት ይችላል።

(1). በተፈጥሮ ተሰጥኦና በማገልገል ስጦታ መካከል ያለው ልዩነት

ሀ. ስጦታ ስትወለድ ከአንተ ጋር የነበረው ሊሆን የተፈጥሮ ተሰጥኦ ግን አይደለም።

ለ. ማንኛውም ሰው የተፈጥሮ ተሰጥኦ ሊኖረው ይችላል፥ ሆኖም የማገልገል ስጦታ ባለው ሰው ውስጥ ሆኖ ሥራውን የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ነው።

ሐ. የተፈጥሮ ተሰጥኦ ሊገዛ ይችላል፥ ስጦታን ግን መግዛት አይቻልም።

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

የማገልገል ስጦታ የተሰጠው በክርስቶስ አካል ውስጥና ከአካሉም ውጪ የሚገኙ ሰዎችን ችግር ለመፍታት ነው። ሰዎችን ለክርስቶስ ለመማረክ እጅግ ውጤታማ ከሆኑት መንገዶች አንዱ በችግራቸው ወቅት አገልግሎት መስጠት ነው። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ላይ ኢየሱስ አንድ ዓይነ ስውር ሰው እንደፈወሰ እናነባለን። ዕውሩ ሰው ታላቅ ችግር ነበረበት፥ ኢየሱስም ያንን ችግር አስወገደለት። በእርሱ ላይ መተማመን እንዲያድርበት ካደረገ በኋላ ጌታ ኢየሱስ "በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን? ሲል ጠየቀው። ዕውሩም፣ "ጌታ ሆይ፣ በእርሱ አምን ዘንድ ማን ነው" ሲል መለሰ (ዮሐ 9:35-36)። ጌታ ኢየሱስ ሥጋዊ ፍላጎቱን ወይም ችግሩን በማስወገድ በኩል የሰጠው አገልግሎት ዕውሩን እንዲያምን ልቡን አዘጋጀው። በእውነተኛ ልብ የሌሎችን ችግር ለማስወገድ ስንነሣ የሰዎች ችግር ይወገዳል፥ የእግዚአብሔርም ሥራ በዚሁ ምክንያት እየሰፋ ይሄዳል።

(2). የአንድን ሰው ልብ በወንጌል ለመድረስ እጅግ ከሚመረጡት መንገዶች አንዱ

የማስተማር ስጦታ

ዓላማ 2 በማስተማር ስጦታና በመጋቢ - አስተማሪ ስጦታ መካከል ያለውን ልዩነት መግለጽ።

የስጦታው ትርጓሜ

"..... የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ....." (ሮሜ 12:7)።

በዚህ ላይ በተገለጸው ዓይነት ማስተማር ማለት "አንድን ነገር እንዴት እንደሚደረግ ማሳየት፣ ማሰልጠን፣ ማስተማር ነው።" ስለዚህ የማስተማር ስጦታ ማለት

1. አንድን ነገር እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ለሌሎች የማሳየት ስጦታ

2. አንድ ነገር እንዴት እንደሚደረግ ሌሎችን ማሰልጠን

3. ሌሎችን የማስተማር (እውቀት ማካፈልን ጨምሮ ስጦታ እንደሆነ እንረዳለን።

በመጋቢ - አስተማሪነትና በአስተማሪነት ስጦታ መካከል ያለው ልዩነት መጋቢ አስተማሪነት ከእመራር አገልግሎት ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው። በሌላ በኩል ግን የማስተማር ስጦታ በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ብቻ የተወሰነ አይደለም። በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም አባል የማስተማር ስጦታ ሊኖረው ይችላል። አንዳንዶች በተፈጥሮ የማስተማር ተሰጥኦ አላቸው። ይህ የተፈጥሮ ተሰጥኦ ያለው ሰው በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ጊዜ፣ ተሰጥኦው የማስተማር ስጦታ ሆኖ እንደተለወጠ የመገንዘቡ ዕድል እጅግ ከፍ ያለ ነው።

ታዲያ ይህ ማለት ሴቶችም ሊያስተምሩ ይችላሉ ማለት ነው? በእርግጥ አንዳንዶች በ1ጢሞ 2፡11-12 ላይ የተጻፈውን በሚያነቡበት ጊዜ ይህን የመሰለ ጥያቄ ያሳድርባቸዋል። ሆኖም ጳውሎስ ሴት የማስተማር ስጦታ ሊኖራት አይችልም አላለም። ለቲቶ በጻፈው መልእክት፣ "..... እንዲሁም አሮጊቶች ሴቶች.....በጎ የሆነውን ነገር የሚያስተምሩ ይሁኑ.... ቆነጃጅትም ... ለባሎቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ ይምከሩአቸው" ይላል (ቲቶ 2፡3-5)።

የጳውሎስ አባባል የተመሠረተው ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኙ ወንዶች ላይ የማስተዳደር ሥልጣን ሊኖራቸው አይገባም በሚለው መርህ ላይ ነው። በዚህ ምክንያት በአንድ የተወሰነ ሁኔታ ውስጥ ሴቶች የማስተማሩን አገልግሎት እንዳያገለግሉ ይህንንም ኃላፊነት እንዳይወስዱ ማድረግ የተሻለ ሆኗል። ሴቶች ማስተማራቸው ምንም ስህተት የለውም፣ ሆኖም ከዚህ የተነሣ ችግር የሚፈጠር ከሆነ ማንንም ሰው ቅር አለማሰኘት የተሻለ ይሆናል። አንዲት ሴት የማስተማር ስጦታ ካላት እግዚአብሔር ምሪትን እንዲሰጣት ልትጠይቅና መንፈስ ቅዱስም እንደሚገባ እንድታዳብር እንዲረዳት መፍቀድ ይኖርባታል።

(3). ማስተማር ማለት

ሀ. መመሪያ መስጠት
ለ. እውነትን ማካፈል
ሐ. ምሳሌ መሆን
መ. ማሰልጠን

(4). የማስተማር ስጦታ ለአንዲት ሴትም ሊሰጥ የሚችለው ሴቲቱ፡-

ሀ. የተፈጥሮ ተሰጥኦ ስላላት ስጦታው ይሰጠኝ ብላ ከጠየቀች ነው።
ለ. ስጦታውን መንፈስ ቅዱስ እንደሚገባ እንዲያዳብርላት ስትፈቅድ ነው።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

ማስተማር በልዩ ልዩ ዓይነት መንገድ ሊከናወን ይቻላል። እዚህ ላይ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ሁለቱን መንገዶች ብቻ እንመለከታለን።

ማስተማር ምሳሌ በመሆን ሊከናወን ይችላል

ጳውሎስ መጋቢ-አስተማሪ ለነበረው ለቲቶ ስለዚህ ጉዳይ በቲቶ 2፡3-5 ላይ ጽፎለት ነበር። ከቲቶ ሥራ አንዱ ማስተማር ነበር። አሮጊቶች ሴቶች ወጣቶቹን ሴቶች እንዴት እንደሚያስተምሩ ማስተማር ነበረበት። ይህንንም የሚያደርገው አሮጊቶቹ ሴቶች ለወጣቶቹ ሴቶች እንዴት ጥሩ ምሳሌዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ በማሳየት ነበር። አሮጊቶቹ ሴቶች ሊያደርጉት ስለሚገባቸው ነገር የነገራቸው ዝርዝር ሃሳብ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተጠቅሷል።

- በቅድስና የሚኖሩ ሴቶችን ኑሮ ሊኖሩ ይገባል።

- የማያሙ ማለትም ሌሎችን የሚነዛ ውሸት የማያወሩ ሊሆኑ ይገባል።

- የወይን ጠጅ ተገዢዎች ወይም ሱሰኞች መሆን የለባቸውም።

- ባሎቻቸውን የሚወዱ ሊሆኑ ይገባል።

- ራሳቸውን የሚገዙና ንጹሐን ሊሆኑ ይገባል።

- መልካም የቤት እመቤቶች ሊሆኑ ይገባል።

- ለባሎቻቸው ሊታዘዙ ይገባል።

- የእግዚአብሔርን ቃል የማያስድቡ ሊሆኑ ይገባል።

አሮጊቶች ሴቶች ወጣቶች ሴቶችን በማነጋገር ሊያስተምሩ ይችላሉ። ይህንን ሊያደርጉ ቢችሉም ከዙሉም በላይ ግን በምሳሌነታቸው ሊያስተምሯቸው ይችላሉ። ይህም ዓይነት ማስተማር በማንኛውም ባሕል ሊካሄድ ይችላል። በምሳሌነት ማስተማር ማለት እንደ ሥራ እንዴት እንደሚሠራ ማሳየት ነው። በመንፈስ ቅዱስ ለተሞላ ሰው ይህ የማስተማር ስጦታ ሊሆን ይችላል።

ማስተማር እውቀትን በማካፈል ሊከወን ይችላል

ጌታ ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ የሚያደርገው ይህንን ነበር። በማቴዎስ ምዕራፍ 5 ላይ ባቀረበው የተራራ ስብከቱ ላይ "ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀረቡ አፋንም ከፍቶ አስተማራቸው" ይላል (ማቴ 5:2)። በትምህርቱም እግዚአብሔርን ደስ ስለሚያሰኘው ዓይነት ሕይወት ሊያውቁ የሚገባቸውን ነገራቸው። ቀደም ባለው የትምህርት ክፍላችን እውቀት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተመልክተናል። እውቀት ለእምነት መሠረት እንደሆነም ተምረናል። በማስተማር እውቀትን የሚያካፍሉ እምነት እንዲፈጠር ያደርጋሉ። ይህም ደግሞ የማስተማር አገልግሎት ከሚያከናውናቸው እጅግ አስፈላጊ ተግባሮች አንዱ ነው።

አስተማሪው ሊሰጥ የሚገባው እውቀት በተለይ የእግዚአብሔርን ቃል እውቀት የሚመለከት ሊሆን ይገባል። አስተማሪው የእግዚአብሔርን ቃል ትርጉም ይሰጣል። አንድ ወላጅ ለልጆቹ የእግዚአብሔርን ቃል በሚያስተምርበት ጊዜ የማስተማር ስጦታም ተግባራዊ ሊሆን ይችላል። የሰንበት ትምህርት አስተማሪው ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አስተማሪው በሚያስተምርበት ጊዜ የማስተማር ስጦታ ተግባር ላይ ሊውል ይችላል። አለዚያም ማንኛውም አማኝ ጎደኛውን ወይም የተወሰኑ ጎደኞቹን በሚያስተምርበት ጊዜ ተግባር ላይ ይውላል። በማንኛውም የቀለም ትምህርት ቤት የሚያስተምር አስተማሪ በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ጊዜ የማስተማር ስጦታ ሊኖረው እንደሚችል መዘንጋት የለብንም።

(5). በሚከተሉት መግለጫዎች እውነት በሆነው አንጻር "እ" ሐሰት በሆነው አንጻር ደግሞ "ሐ" ብለህ ጻፍ።

ሀ. ማስተማር በተለያየ መንገድ ሊከናወን ይችላል
ለ. ማስተማር እምነት ሊፈጥር የሚችለውን እውቀት ያስተላልፋል።
ሐ. በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር የምናሳይ ከሆነ በምሳሌነት እያስተማርን ነው።

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

የማስተማር ዋና ተግባር እውቀትን ማካፈል ነው። ዓላማውም እምነት፣ የጽድቅ አኗኗርና አሰራር እውን እንዲሆን ማድረግ ነው። እምነት፣ የጽድቅ አኗኗርና አሰራር ለክርስቶስ አካል ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ እናውቃለን። እነዚህ ከሌሉ ደግሞ የክርስቶስ አካል ሊኖርም አይችልም። ይህ የማስተማር ስጦታን ከፍተኛ ዋጋ እንድንገነዘብ ያደርገናል።

(6). የማስተማር ስጦታ አስፈላጊ የሆነው፦
ሀ. ማንኛውም ሰው ሊኖረው ስለሚችል ነው።
ለ. መልካም ምሳሌዎች ያደርገናል።
ሐ. ለእምነት መልካም መሠረት ያኖራል።

የመምከር ስጦታ

ዓላማ 3 የመምከር ስጦታን ምንነት መግለጽ።

የስጦታው ምንነት ሲገለጽ

መምከር ወይም ማበረታታት (exhortation) ማለት "ማቅረብ ወይም ማደፋፈር" ማለት ነው። ይህ ማለት ከመምከር ስጦታ ጋር በተገናዘበ መልኩ አማኞችን ወደ እግዚአብሔር ወይም ወደ እግዚአብሔር ዓላማ ማቅረብ ነው። በተጨማሪም አማኞችን ለአንድ ድርጊት ማንቃት ማለት ሊሆን ይችላል። ስለሆነም የመምከር ስጦታ ያለው አማኝ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ወይም ወደ አንድ የእግዚአብሔር ዓላማ ያቀርባል።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

"..... የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ..... " (ሮሜ 12:8)።

"መምከር" የሚለው ቃል በእንግሊዝኛው ትርጉም (KIV) ላይ "ማበረታታት"፣ "ማደፋፈር" ይለዋል።

አሁን እያጠናናቸው ስላሉት ስጦታዎች ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 12 ላይ በሰጠው መምሪያ ላይ ምንም ትኩረት አላደረግንም። ይህንን ግን ችላ ልንለው አይገባንም። መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ስጦታዎች ያሏቸው መትጋት እንዳለባቸው ይናገረናል። ስለ መትጋት ሲናገር ምን ማለቱ ነው? ስጦታዎቹን ሁሉ ማዳበርና መጠቀም እንደሚገባ ማሳሰቡ ነው። በተቻለን መጠን ስጦታዎቻችን ሌሎችን የሚጠቅሙ እንዲሆኑ መማር ይኖርብናል። "የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ" (ሮሜ 12:8)። ይህም ማለት የመምከር ስጦታ ያለው በስጦታው ሊጠቀምበትና ሊያሻሽለው ጥረት ማድረግ አለበት ማለት ነው።

በክርስቶስ አካል ውስጥ ብዙዎች የመምከር ስጦታ ሊኖራቸው ይችላል። በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ይህ ስጦታ ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት በቅርበት ስንመለከት ይህንን ሃሳብ የበለጠ እንድንረዳ ያደርገናል። "መምከር" የሚለውን ቃል ይዘን የእግዚአብሔርን ቃል ስንመረምር ጉዳዩ ከአማኞች ጋር የተያያዘ መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርገናል። አማኞች፦

1. በልባቸው ፈቃድ በጌታ ጸንተው ያኖሩ ዘንድ (የሐዋ 11:23)
2. በእምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ (የሐዋ 14:22)
3. በፈታኝነት በልማስና እንዲሰጡ (2ቆሮ 9:5)
4. እግዚአብሔርንም በይበልጥ ደስ እንዲያሰኙ (1ተሰ 4:1)
5. ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን እንዲገስፁአቸው፣ ድፍረት የሌላቸውን እንዲያጸ ኑአቸው፣ ለደካሞች እንዲተጉላቸው፣ ሰውን ሁሉ እንዲታገሡ።

ማንም ለሌላው በክፉ ፋንታ ክፉ እንዳይመልስ፣ ለሁሉም መልካምን ለማድረግ እንዲተጉ (1ተሰ. 5:14-15)።

6. የገዛ እንጀራቸውን ይብሉ ዘንድ (2ተሰ 3:12)
7. ልመና፣ ጸሎት፣ ምልጃም፣ ምስጋናም ስለ ሌሎች ሁሉ እንዲያደርጉ (1ጢሞ 2:1)
8. ራሳቸውን የሚገዙ እንዲሆኑ (ቲቶ 2:6)
9. ስለተሰጠው እምነት እንዲጋደሉ (ይሁዳ 3) ተጠርተዋል።

እነዚህ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች በአጠቃላይ ስለ መምከር ጠለቅ ያለ መረዳት እንዲኖረን ያደርጉናል። ማንኛውም አማኝ ከዚህ በላይ በተገለጸት በአንደኛው መንገድ ሌሎች ሰዎችን የሚረዳ የመምከር ስጦታ ሊኖረው ይችላል። ሐዋርያቶች፣ ነቢያቶች፣ ወንጌል ሰባኪዎችና መጋቢ - አስተማሪዎች መምከር ይችላሉ። አብዛኛው በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ የመምከር ስጦታ ሊኖረው ይችላል።

አማኞች ሁሉ በዕብ 3:13 ላይ "በእያንዳንዱ ቀን እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ" ለሚለው ቃል ትኩረት ሊሰጡ ይገባል። ከወንድሞቻቸው ወይም ከእህቶቻቸው ጋር በየዕለቱ፣ የሚመካከሩና በመንፈስ ቅዱስም የተሞሉ አማኞች በእርግጥ በጌታ ሐሴት የሚያደርጉ ይሆናሉ።

(7). በሚከተሉት መግለጫዎች ውስጥ እውነት ከሆኑት አንጻር 'እ' ሐሰት ከሆኑት አንጻር ደግሞ "ሐ" ብለህ ጻፍ።

____ሀ. እግዚአብሔር የሚሰጠን ማንኛውም ስጦታ መዳበር አያስፈልገውም።
____ለ. ሰዎችን ስንመክር የምናደርገው ዋናው ነገር ጥያቄ መጠየቅ ነው።
____ሐ. የተለዩ ጥቂት ሰዎች ብቻ አማካሪ መሆን ይችላሉ።
____መ. በየቀኑ ሌሎች ሰዎችን በመርዳት ለጌታ ታዛዥ ከሆንን የማማከር ስጦታ ሊኖረን ይችላል።

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

መምከር በክርስቶስ አካል ውስጥ ጠቃሚ ዓላማዎችን ማከናወን ይችላል። ምናልባት ማንኛውም አማኝ በወቅቱ ምክር የሚያሻው ይሆናል። በተለይ በኑሮአቸው ችግር ወይም ፈተና የገጠማቸው አንዳንድ አማኞች አዘውትረው ምክር መቀበል ያስፈልጋቸዋል። ስለሆነም የመምከር ስጦታ ዓላማ አማኞችን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ወይም ወደ አንድ የእግዚአብሔር ዓላማ ማቅረብ ይሆናል። መምከር ባለ ስጦታዎቹን ወይም ሌሎች ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖራቸው ጉዞ ለመርዳት ወደሚያስችል ተግባር መምራት ማለትም ነው።

(8). ብዙ አማኞች የበለጠ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንዳለባቸውና አንድን ተግባር ለማከናወን መበረታታት እንደሚያስፈልጋቸው ያውቃሉ። አማኞች እርስ በርሳቸው መረዳዳት ይችላሉ።

የመከራ ፈተና

እውነት - ሐሰት።

በሚከተሉት መግለጫዎች እውነት በሆኑት አንጻር 'እ' ሐሰት በሆኑት አንጻር 'ሐ' ብለህ ጻፍ

___1. የጸጋ ስጦታዎችን በትክክል መመደብ በጣም አስፈላጊ ነው።

___2. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሚገኙት ከእግዚአብሔር ነው።

___3. ማገልገል ማለት ሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማሟላት ነው።

___4. የተፈጥሮ ተሰጥኦዎችና የፀጋ ስጦታዎች ተመሳሳይ ናቸው።

___5. ማስተማር ማለት አንድ ተግባር እንዴት እንደሚከናወን ማሳየት ነው።

___6. የማገልገል ስጦታ የወንጌል ተልዕኮን ለማከናወን አይረዳም።

___7. አማኝ የማስተማር ስጦታ እንዲኖረው መጋቢ መሆን ይገባዋል።

___8. ወላጅ በቤቱ የማስተማር ስጦታ ሊኖረው ይችላል።

___9. ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በፍጹም ማስተማር አይገባቸውም።

___10. የአስተማሪ እጅግ አስፈላጊው ተግባር የእግዚአብሔርን ቃል እውቀት ማካፈል ነው።

___11. እውቀት የእምነት መሠረት ነው።

___12. መምከር የወንጌል ስብከት አገልግሎት ከመስጠት ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው።

___13. አማኞች እርስ በርሳቸው መመካከር ይችላሉ።

___14. የመምከር ዓላማ ምዕመናን እግዚአብሔርን በቅርበት እንዲከተሉ መጥራት ነው።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

5. ሀ. እውነት ለ. እውነት ሐ. እውነት

1. ለ

6. ሐ

2. እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ወቅት መርዳት ነው።

7. ሀ. ሐ ሐ. ሐ
ለ. ሐ መ. እ

3. ሀ፣ ለ፣ ሐ እና መ
የተሰጡት መልሶች በሙሉ ትክክል ናቸው።

8. በመምከር ስጦታ

4. ለ

6 ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች 2

ትምህርት

መለገስ፣ ማስተዳደር፣ ምሕረት ማድረግ፣ መርዳት

ቀደም ባለው ክፍለ ትምህርታችን በሮሜ ምዕራፍ 12 ላይ ከተጠቀሱት የአገልግሎት ስጦታዎች ስለ ሦስቱ ማጥናታችን ይታወሳል። ክፍለ ትምህርቱን እያጠናን ስንሄድ በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ አባል በስጦታዎቹ እንዴት እንደሚያገለግል መመልከት ጀምረናል። አንዳንዶች ለየት ያሉ ስጦታዎችን ይቀበላሉ፣ ሆኖም ለእነሱ በተሰጡት ስጦታዎች ያገለግላሉ።

አሁን ደግሞ አራት ተጨማሪ ስጦታዎችን ለማጥናት ዝግጅታችንን እንቀጥላለን። እነዚህ የአገልግሎት ስጦታዎች እያንዳንዳቸው አስፈላጊ ተግባርና ዓላማ ያላቸው ናቸው። ስለእነዚህ ስጦታዎች ያለን እውቀት በጨመረ ቁጥር ከስጦታዎቹ የምንቀበለው በረከትም እየጨመረ ይሄዳል።

ትምህርቱን እያጠናህ እያለህ ልብህን ለመንፈስ ቅዱስ ክፍት በማድረግ በፀሎት ወደ እርሱ ቅረብ። በግል ሕይወትህ የአገልግሎት ስጦታዎችን አስፈላጊነት በተረዳህ ቁጥር እግዚአብሔርን ማመስገንህን በጸሎት መንፈስ አታቋርጥ።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የልግስና ስጦታ
- የአገዛዝ ወይም የአስተዳደር ስጦታ
- ምሕረት የማድረግ ስጦታ
- የመርዳት ስጦታ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ፦

- በዚህ ምድብ ያሉትን ስባት የአገልግሎት ስጦታዎች መዘርዘርና መግለጽ።
- የእያንዳንዱን የአገልግሎት ስጦታ ዓላማ መግለጽ
- ስጦታዎቹን በሕይወትህ ውስጥ ለማሳደግ ምን ማድረግ እንደምትችል መግለጽ

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

5. ሀ. እውነት ለ. እውነት ሐ. እውነት

1. ለ

6. ሐ

2. እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ወቅት መርዳት ነው።

7. ሀ. ሐ ሐ. ሐ
ለ. ሐ መ. እ

3. ሀ፣ ለ፣ ሐ እና መ
የተሰጡት መልሶች በሙሉ ትክክል ናቸው።

8. በመምከር ስጦታ

4. ለ

6 ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች 2

ትምህርት

መለገስ፣ ማስተዳደር፣ ምሕረት ማድረግ፣ መርዳት

ቀደም ባለው ክፍለ ትምህርታችን በሮሜ ምዕራፍ 12 ላይ ከተጠቀሱት የአገልግሎት ስጦታዎች ስለ ሦስቱ ማጥናታችን ይታወሳል። ክፍለ ትምህርቱን እያጠናን ስንሄድ በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ አባል በስጦታዎቹ እንዲጎ እንደሚያገለግል መመልከት ጀምረናል። አንዳንዶች ለየት ያሉ ስጦታዎችን ይቀበላሉ፣ ሆኖም ለአካሉ በተሰጡት ስጦታዎች ያገለገላሉ።

አሁን ደግሞ አራት ተጨማሪ ስጦታዎችን ለማጥናት ዝግጅታችንን እንቀጥላለን። እነዚህ የአገልግሎት ስጦታዎች እያንዳንዳቸው አስፈላጊ ተግባርና ዓላማ ያላቸው ናቸው። ስለእነዚህ ስጦታዎች ያለን እውቀት በጨመረ ቁጥር ከስጦታዎቹ የምንቀበለው በረከትም እየጨመረ ይሄዳል።

ትምህርቱን እያጠናህ እያለህ ልብህን ለመንፈስ ቅዱስ ክፍት በማድረግ በፀሎት ወደ እርሱ ቅረብ። በግል ሕይወትህ የአገልግሎት ስጦታዎችን አስፈላጊነት በተረዳህ ቁጥር እግዚአብሔርን ማመስገንህን በጸሎት መንፈስ አታቋርጥ።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የልግስና ስጦታ
- የአገዛዝ ወይም የአስተዳደር ስጦታ
- ምሕረት የማድረግ ስጦታ
- የመርዳት ስጦታ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ፦

- በዚህ ምድብ ያሉትን ስባት የአገልግሎት ስጦታዎች መዘርዘርና መግለጽ።
- የእያንዳንዱን የአገልግሎት ስጦታ ዓላማ መግለጽ
- ስጦታዎቹን በሕይወትህ ውስጥ ለማሳደግ ምን ማድረግ እንደምትችል መግለጽ

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. 1ቆሮ 13 በታልሀ ማጥናትህን ቀጥል። ይህንን ክፍለ ትምህርት በምታጠናቅቅበት ወቅት መጽሐፍ ቅዱስህን ሳትመለከት ከምዕራፉ የመጀመሪያዎቹን ዘጠኝ ቁጥሮች በታልሀ ማለት መቻል ይኖርብሃል።

2. በማስታወሻ ደብተርህ በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉትን ሰባት የእገልግሎት ስጦታዎች በዝርዝር አስፍር።

3. ይህንን ክፍለ ትምህርት በጥንቃቄ አንብበው። በክፍለ ትምህርቱ ውስጥ በምታገኛቸው ጊዜ እያንዳንዱን የአገልግሎት ስጦታ ክበበው። ይህንን ማድረግህ እንድታስታውሰው ይረዳሃል።

4. ቀደም ባሉት ክፍለ ትምህርቶች እንዳደረግኸው ሁሉ እሁንም የመከራ ፈተናዎቹን ሥራቸው።

የትምህርቱ ዝርዝር

የልግስና ስጦታ

ዓላማ 1 የልግስና ስጦታን ዓላማና ተግባር መግለጽ።

የስጦታው ምንነት ሲገለፅ

"... የሚሰጥ በልግስና ይስጥ ...." (ሮሜ 12:8)

መስጠት ምንም መግለጫ የሚያስፈልገው ነገር እይደሰም። መስጠት ምን ማለት እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን። ሆኖም ***የልግስና ስጦታ*** ምን ማለት እንደሆነ መተርጎም ያስፈልገዋል። ***የልግስና ስጦታ*** በምንልበት ጊዜ እንድ አማኝ ካለው ሀብት ወይም ገንዘብ ሌሎች ሰዎችን ለመርዳት ወይም ለእግዚአብሔር ሥራ በነፃነትና በቸርነት ለመስጠት የሚያስችለው የእግዚአብሔር ስጦታ ማለታችን ነው። የልግስና ስጦታ ገንዘባችንን የሚመለከት ነው፣ ሆኖም ከጊዜያችን፣ ከጉልበታችን፣ ከተፈጥሮ ችሎታችንም ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

የልግስና ስጦታ የሚገኘው የሰውን ችሎታ ከእግዚአብሔር ችሎታ ጋር በማጣመር ነው። የሰው ችሎታ አንዳንድ ጊዜ በጣም ውስን ሲሆን የእግዚአብሔር ችሎታ ግን ውስን አይደለም። የአንድ ሰው ትንሽ ችሎታ ከእግዚአብሔር ታላቅ ችሎታ ጋር በሚጣመርበት ጊዜ እንዴት ድንቅ ነገር ነው? የልግስና ስጦታ በሚዳብርበት ወቅት የሚሆነው ይህ ነው። ሐዋርያው

ጳውሎስ በ2ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8 እና 9 ላይ የተናገረውን በጥንቃቄ ስናነበው ስለልግስና ስጦታ መረዳት የሚያስችሉን በጣም ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች እናገኛለን። በእነዚህ ምዕራፎች ከምናገኛቸው ሃሳቦች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. ***የሌሎች አማኞችን ምሳሌዎች በምንከተልበት ጊዜ የልግስና ስጦታ ሊዳብር ይችላል።*** "በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን (የመቄዶንያ ሰዎች) ለጌታ ለእኛም ሰጡ" (2ቆሮ 8:5)።

2. ***የልግስና ስጦታ በአማኙ ሕይወት አስፈላጊ ነው።*** "በነገር ሁሉ በእምነትና በቃል በእውቀትም በትጋትም ሁሉ ለእኛም በፍቅራችሁ እንደተረፋችሁ በዚህ ጸር ሥራ ደግሞ ትረፉ" (2ቆሮ 8:7)።

3. ***የልግስና ስጦታ የሚሠራው በሕግ አይደለም።*** "ትዕዛዝ እንደምሰጥ አልልም" (2ቆሮ 8:8)።

4. ***የልግስና ስጦታ እንደሚገባ በተግባር የተገለጸው በራሱ በጌታ በኢየሱስ ነው።*** "ሀብታም ሲሆን እናንተ በእርሱ ድህነት ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ" (2ቆሮ 8:9)።

5. ***የልግስናን ስጦታ የሚያገኙት በበጎ ፈቃድ የሚሰጡ ናቸው።*** "እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና" (2ቆሮ 9:7)።

6. ***የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደምናገኝ ተስፋ ተገብቶልናል።*** "ሁልጊዜ በሁሉ ነገር የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አግኝታችሁ . . ." (2ቆሮ 9:8)።

7. ***የልግስና ስጦታ፣ የአምላካችን ፍላጎት ለበጎ ስራ ሁሉ መብዛት እንደሆነ ይገልጸል።*** ". . .ለበጎ ሥራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ፣ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል" (2ቆሮ. 9:8)።

8. ***የልግስና ስጦታ ታላቅ ብድራት ሊያስገኝ ይችላል።*** ይህ የመጨረሻው ነጥብ የተጠቀሰው በፊል 4:17 ላይ ሲሆን ቃሉም "በስሌታችሁ የሚበዛውን ፍሬ እንጂ ስጦታውን ፈላጊ እይደሰሁም" ይላል።

በ1ነገ 17:8-16 ስለ ልግስና ስጦታ ብዙ ትምህርት ሊያስተምረን የሚችል አንድ ታሪክ አለ። ነብዩ ኤልያስ በረሃው ዘመን አንዲት መበለት ለመጠየቅ ሄዶ ነበር። ወደ እርሷ ቤት በመጣ ጊዜ እንጨት ከጓሮ ስትለቅም አገኛትና አንጀራና ውኃ እንድትሰጠው ጠየቃት። እርሷም በቤቷ ያላት በማድጋ አፍኝ ዱቄትና በማሰሮ ጥቂት ዘይት ብቻ እንደሆነ ነገረችው። ይህንንም ካለች በኋላ ይህ የመጨረሻ ምግባቸው እንደሆነና ከዚህ በኋላም በረሃብ እንደሚሞቱ ገለጸችለት።

የምትሰጠው ምንም ነገር እንዳልነበራት ግልጽ ነው። ሆኖም ኤልያስ ታላቅ ትምህርት አስተማራት። ያሰቻትን ዱቄት ተጠቅማ ለእርሱ እንጎቻ እንድትጋገርለት መበለቲቱን ጠየቃት። የታሪኩን መጨረሻ ካላወቅን ከአንዲት ድሃ መበለት ይህንን ለመጠየቅ ነቢዩ ያሳየው ድፍረት እንዴት ያለ ጭካኔ ነው! ልንል እንችላለን። ኤልያስ ግን እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ ያውቅ ነበር። በዚህም ምክንያት ያላትን ሁሉ እንድትሰጠው ጠየቃት። ይህ የአንድ ታላቅ መገለጥ ቁልፍ ነው። ልብ እናድርግ፣ በምንሰጥበት ጊዜ ለልግስና ስጦታ መሠረት እየጣልን ነው። የልግስና ስጦታ ከሰማይ ወደ ልባችን እንደዚሁ ጥልቅ አይልም። ስጦታውን ለመቀበል እኛም እርምጃ መውሰድ አለብን። እኛ ካሰን ለሌሎች መስጠት ይኖርብናል።

አንዳንድ ሰዎች የነቢዩን ጥያቄ ይቃወሙ ይሆናል። እንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች የልግስናን ስጦታ አይቀበሉም። መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኩል ለመበለቲቱ እንደተናገረ ለእኛም እንድንሰጥ ሊናገረን ይችላል። የልግስናን ስጦታ የምናገኘው ስንታዘዝ ብቻ ነው።

ለመበለቲቱ አስደናቂ ነገር ሆነላት። ለኤልያስ በመታዘዝ በሰጠች ጊዜ፣ ለነቢዩ እንጎቻ ለመጋገር በተነሳችበት ጊዜ፣ የነበረው ዱቄትና ዘይት እንደዚያው እንደነበረ ተመለከተች። ከዚያም በስተቀር አንድ ሌላ ተጨማሪ ነገርም ተረዳች። የረሃቡ ዘመን አስከሚያበቃ ድረስ የሚቆይ ብዙ ዱቄትና ዘይት እንዳላት አወቀች። ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ችግር ማቃለያ የሚሆን በቂ ዱቄትና ዘይት እንዳላት ተገነዘበች። "እርሷና እርሱ ቤትዋም ብዙ ቀን በሉ" (1ነገ 17:15)።

ምንም እንኳ ብዙውን ጊዜ የልግስናን ስጦታ ከገንዘብ ጋር የምናያይዘው ቢሆንም፣ ይህን ስጦታ ማግኘት ማለት ማንኛውንም ያለንን ነገር በመስጠት ሐሴት ማድረግ ማለት ነው። ስጦታው ቁሳቁስን፣ጊዜን፣ ጉልበትንና የተፈጥሮ ችሎታን መለገስን ሊያጠቃልል ይችላል።

ካሰን ነገር በቸርነት በመስጠት ለመንፈስ ቅዱስ ታዛገሮች ከሆንን የራሳችንም ችግር ይቃለላል። ከዚህ ይልቅ አስደናቂው ነገር ለሌሎችም ልንሰጠው የምንችለው ተጨማሪ ነገር ይኖረናል። እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ይህ ስጦታ በእኛ ውስጥ ሲሠራ ልግስናችን እኛ መስጠት በምንችለው መጠን የተገደበ አይሆንም። ለመበለቲቱ ሴት እንደሆነው ልግስናችን በእግዚአብሔር ችሎታ መጠን የተወሰነ ይሆናል። ስለሆነም የልግስና ስጦታ ዋናው ምክንያት ለሌሎች አብዝተን መስጠት እንድንችል ብርታት ማግኘታችን ነው።

(1). የልግስና ስጦታ _____ ስጦታ ነው።

ሀ. ለራሳችን ብዙ ማግኘት እንድንችል እግዚአብሔር የፈለገበት
ለ. ገንዘብ እንዲኖረን የሚጠይቅ

ሐ. በነፃነትና በቸርነት እንድንሰጥ የሚረዳን
መ. በይበልጥ መስጠት እንድንችል በቅድሚያ መስጠት የሚያስችለን

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

የዚህ ስጦታ ዓላማው ምንድን ነው? አያንዳንዱ ስጦታ የተሰጠው ለአንድ የተለየ ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው። ስጦታዎች ሁሉ የተሰጡት ለክርስቶስ አካል የሚያስፈልገውን ለማሟላት ነው። ይህም በተራው አካል ተልእኮውን እንዲያሟላ ያስችላል። የልግስና ስጦታ የተለየ ዓላማ በክርስቶስ አካል ያለውን ችግር ለመፍታትና ለማቃለል እንዲሁም የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንዲሟላ ማድረግ ነው።

(2). የልግስና ስጦታ ለአማኞች የተሰጠበት ምክንያት

ሀ. በአካሉ ውስጥ ያለውን ቁሳዊ ፍላጎት ስለሚያሟላ ነው።
ለ. አማኞች ለራሳቸው ገንዘብ የሚያገኙበት መንገድ እንዲሆን ነው።
ሐ. ምዕመናን ገንዘብ መስጠት ስለሚወዱ ነው።

የአገዛዝ ወይም የአስተዳደር ስጦታ

ዓላማ 2 የአገዛዝ ወይም የአስተዳደር ስጦታን ተግባርና ዓላማውን መግለጽ።

የስጦታው ምንነት ሲገለጽ

"ማስተዳደር ከሆነም በትጋት ያስተዳድር" (ሮሜ 12:8)። *ማስተዳደር* ማለት "ከፊት መቅደም ወይም መምራት" ማለት ነው። በ1ቆሮ 12:28፥ የቀድሞው ትርጉም ላይ የማስተዳደር ስጦታ "አገዛዝ" ተብሎ ተጠርቷል። ስለሆነም የአገዛዝ ስጦታ በክርስቶስ አካል ውስጥ የተወሰኑ አባላት በአካሉ ፊት በመቅደም ወይም በመምራት በአካሉ ላይ የበላይ ኃላፊነትን ስፍራ በመያዝና ለአካሉ መመሪያ በመስጠት እንዲያገለግሉ የተሰጠ ስጦታ ነው።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

ጄኔራሎችና ሌሎች የጦር መኮንኖች የሌሉት ሠራዊት ምን መምሰል እንደሚችል እናስብ። እያንዳንዱ በፊቱ መልካም የመሰለውን የሚያደርግ (መሳፍንት 17:6) ከሆነ፣ ሠራዊቱ ምን ችግር ሊገጥመው እንደሚችል በቀላሉ መገመት እንችላለን። ይህን መሳይ ሠራዊት በጦርነት ምንም ዓይነት ድል ሊጎናጸፍ አይችልም። የክርስቶስ አካልም በፊቱ የሚወጡ፣ በበላይነት የሚመሩትና በጉዳዩ ሁሉ መመሪያ የሚሰጡት ሰዎች ያስፈልጉታል።

የአካሉ ራስ የሆነው ክርስቶስ ከአንድ ታላቅ የሠራዊት መሪ ጄኔራል ጋር ሊነጸጸር ይችላል። ሆኖም በአካሉ ላይ የበላይ መሪ በመሆን ለጉዳዮቹ ሁሉ መመሪያ ይሰጣል። በመላው ዓለም ያለው የአካሉ ክፍል የሆኑ፥ በብዙ የሚቆጠሩ የአማኞች ስብስቦች ላይ የበላይ መሪዎች የሚሆኑና መመሪያ የሚሰጡ ክርስቲያኖች ያስፈልጋሉ። ማንኛውም የአማኞች ስብሰባ የአስተዳደር ተሰጥኦ ያለው አንድ ሰው ያስፈልገዋል። አማኞች ሁሉ "ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ" ተብለው ታዘዋል (ዕብ 13:17)። በዚህም ምክንያት የአካሉ ራስ ሰተወሰኑ ክርስቲያኖች የአገዛዝ ወይም የአስተዳደር ስጦታ ይሰጣቸዋል።

መቼም አማኞች ሁሉ አስተዳዳሪዎች ሊሆኑ አይችሉም፣ ሆኖም የማስተዳደር ስጦታ ያላቸው አንዳንዶች መኖር ይገባቸዋል። ይህን መሳይ ስጦታ የተሰጣቸው የማደራጀት፣ የመቆጣጠርና የመምራት ልዩ ችሎታ ይሰጣቸዋል። እነርሱ የሚያከናውኑት ተግባር ለአካሉ እጅግ አስፈላጊ ነው። "ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል" (1ጢሞ 3:1)።

በክርስቶስ አካል ውስጥ የመግዛት ወይም የማስተዳደር ስጦታ ላላቸው አባላት በእግዚአብሔር ታል ውስጥ የተሰጡዋቸው አንዳንድ ስሞች አሉ።

1. ኤጲስ ቆጶስ (ሽማግሌ) (የቤተ ክርስቲያን መሪ)፦ "ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?" (1ጢሞ 3:4-5)።

የቤተ ክርስቲያን መሪው ወይም የመጋቢው አገልግሎት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ካሉት ከፍተኛ የሃላፊነት ቦታዎች አንደኛው ነበር። በእረኛነት ወይም በበላይ ሃላፊነት እንዲያገለግል በምዕመናኑ የተመረጠ ነበር።የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ተብሎም ይጠራ ስለ ነበረ፣ በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ አስተዳዳሪ ነበር። ከአዲስ ኪዳን ዘመን በኋላ እያደገ የመጣው የማኅበረ ምዕመናን ቁጥርና የእያንዳንዱም ማኅበረ ምዕመናን መጠን ከፍ እያሰ መሄድ፥ የአደረጃጀት መንገዱ ሰፋ እንዲል አደረገው። አንዳንድ የምዕመናን ስብስቦች መሪዎች ለራሳቸው ጳጳስ ወይም መጋቢ የሚለውን ሹመት በመውደዳቸው "ሽማግሌ" የሚለው ስያሜ ዝቅተኛ የአመራር አገልግሎት ለሚሰጡት ተሰጠ። በአዲስ ኪዳን የምንመለከተው ለዚህ ፍላጎት መልስ የሚያስገኘውን የአደረጃጀት መልክ ነው።

ሽማግሌ - ኤጲስ ቆጶስ ወይም ጳጳስ የሆነው ሊያስተምር ይገባዋል፤ ሆኖም የመጋቢ አስተማሪነት አገልግሎት የሚሰጡትንም በስሩ ማስተባበር ይችላል። የሽማግሌ ጳጳስ ዋና ሃላፊነት የክርስቶስ አካል የሆኑትን አማኞች መምራትና በጉዳዮቻቸው ላይ ውሳኔ መስጠት ነው።

2. ዲያቆን (ረዳት)፦ የሙሉ ጊዜ መንፈሳዊ መሪዎች ያልሆኑና ከፍ ብለው የተጠቀሱትን የመሰሉ አንዳንድ አማኞች የማስተዳደርም ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ በመሪዎች አመራር ስር ያገልግላሉ። እነርሱም "የቤተ ክርስቲያን ረዳቶች" ይባላሉ። ምክንያቱም የተወሰኑ የአማኞች ቡድንን በመመራት መሪዎችን ይረዳሉ። "ወንድሞች ሆይ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፣ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን" (የሐዋ 6:3)።

በክርስቶስ አካል ውስጥ አገዛዝ ወይም አስተዳደር አስፈላጊ ስለሆነ የአገዛዝ ወይም የአስተዳደር ስጦታን አስፈላጊነት በቀላሉ መረዳት ይቻላል። የሚመሩ፣ የሚያስተዳድሩ ወይም መመሪያ የሚሰጡ በሌሉበት አስተዳደርም የለም። አስተዳደር በሌለበት ደግሞ አስተዳደር የሚያስፈልጋቸው ምንም ያህል ሰዎች አይቀሩም። አስተዳደርና የማስተዳደር ስጦታ ከሌለ የክርስቶስ አካል ደካማና ተግባሩን ማከናወን የማይችል ይሆናል። በዚህም ምክንያት የማስተዳደር ስጦታ በጣም አስፈላጊ ነው።

(3). የማስተዳደር ስጦታ _____ ነው

ሀ. የተወሰኑ የአማኞች ሕብረትን ማስተባበር ወይም መምራት
ለ. ብዙ አማኞች ሊኖራቸው የሚገባ ስጦታ
ሐ. ለእግዚአብሔር ሥራ እድገት አስፈላጊ ያልሆነ

(4). የአስተዳደር ስጦታ ያላቸው _____፣_____እና_____ማድረግ ይችላሉ፡

(5). የአስተዳደር ስጦታ ያላቸው ከሚጠሩበት የአገልግሎት ስሞች ጥቂቱ፦

ሀ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች
ለ. የወንጌል ሰባኪዎች
ሐ. ሽማግሌዎች

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

የአገዛዝ ስጦታ ተግባር "ማስተዳደር" ነው። የዚህ ስጦታ ዓላማ በዚህ ዓለም ሊያከናውነው የሚገባውን ተግባር እንዲፈጽም ለክርስቶስ አካል አንድነትንና ብርታትን መስጠት ነው። እያንዳንዱ ወታደር ወዴት መሄድና ምን ማድረግ እንዳለበት ለራሱ የሚወስን ከሆነ አንድ ሠራዊት ምን እንደሚመስል ማሰብ አያዳግትም። በእርግጥ ድብልቅልቅ ያለ ሁኔታ ይፈጠራል። የጦር መኮንን ተግባር፥ መምራትና ማስተባበር እንደዚሁም ሠራዊቱ ግቡን ይመታ ዘንድ ለሌሎቹ ወታደሮች መመሪያ መስጠት ነው። በክርስቶስ አካልም ያለው ሁኔታ ይህንኑ የሚመስል ነው።

(6). የአስተዳደር ስጦታ ለክርስቶስ አካል የተሰጠው

ሀ. እንደ ሠራዊት መሆን እንድትችል ነው።
ለ. በምንችለው የተሻለ መንገድ ሁሉ እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው።
ሐ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ሽማግሌዎችና የወንጌል ሰባኪዎች እንዲኖሩት ነው።

ምሕረት የማድረግ ስጦታ

ዓላማ 3 ምሕረት የሚያደርግን ስጦታ ተግባርና ዓላማ መግለጽ።

የስጦታው ትርጓሜ

"የሚምር በደስታ ይማር" (ሮሜ 12:8)።

ምሕረት ማለት "ርኅራኄ" ወይም "የአንድን ሰው ስሜት መጋራት ወይም ሌላው የሚሰማውን ስሜት መካፈል" ማለት ነው። ስለሆነም ምሕረትን የማድረግ ስጦታ የሌሎችን ስሜት የምንካፈል መሆናችንን የምንገልጽበት ስጦታ ነው። የሌሎችን ሀዘን የመካፈል ስጦታ ነው።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

በክርስቶስ አካልም ውስጥ ሆነ አማኞችም ባልሆኑት ዘንድ ምሕረት የማድረግ ስጦታ ከፍተኛ ተፈላጊነት አለው። ሰዎች ሀዘን፣ ብቸኝነት፣ ፀፀት በሚሰማቸው ጊዜ፣ በአጠገባቸው የሚቆምና ርኅራኄ የሚያሳያቸው ሰው የማግኘት ታላቅ ፍላጎት አላቸው። የሚፈልጉትም ምሕረት የማድረግ ስጦታ ያለው ሰው ነው። ምሕረት የማድረግ ታላቁ ምሳሌና መማለጫ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ነው። ስለዚሁ የተጻፈውን ከዚህ በታች በቅደም ተከተል አስፍረነዋል።

1. "ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው" (ማቴ 9:36)።

2. "ወጥቶም ብዙ ሕዝብ አየና አዘነላቸው ድውዮቻቸውንም ፈወሰ" (ማቴ 14:14)።

3. "ኢየሱስም አዘነላቸውና ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ" (ማቴ 20:34)።

4. "ኢየሱስም አዘነለት እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፦ እወዳለሁና ንጻ" አለው (ማር 1:41)።

5. "ሕዝቡ ከእኔ ጋር እስካሁን ሦስት ቀን ውለዋልና የሚበሉት ስለሌላቸው አዝንላቸዋለሁ" (ማር 8:2)።

6. "ጌታም ባያት ጊዜ አዘነላትና፦ አታልቅሽ አላት" (ሉቃ 7:13)።

ጌታ ኢየሱስ ስለ ሰዎች ጥልቅ ስሜት ይሰማው እንደነበርና ለእነዚህም ሰዎች ርኅራኄውን ያሳይ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይነግረናል። ጌታ ኢየሱስ "አዘነላቸው" የሚለው ቃል በተጠቀሱባቸው ስፍራዎች ሁሉ ሊያደርግላቸው የሚገባውን ሁሉ እንዳደረገላቸው ግልጽ ነው። ስለ ሰዎች ማዘንና የሰዎችንም ስሜት መካፈል ብቻውን በቂ አይደለም። ለሰዎች ማዘናችንና ስሜቶቻቸውን መካፈላችንን ለእነርሱ አገልግሎት በመስጠት መግለጥ አለብን። ለሚያዝኑት የመጽናናት ቃል ተስፋ ለቆረጡት የማበረታቻ ቃል ልንለግሳቸው ዝግጁ መሆን ይገባል። ለኃጢአተኛው እንድናስብ በፍቅር ግድ ሊለን ይገባል።

ለምሳሌ ያህል፦ አባት ለሌላቸውና ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ማዘን መልካም ነው። ሆኖም ስለ እነርሱ ማዘንና ስሜቶቻቸውን መካፈል በቂ አይደለም። በአንዳንድ ተግባራዊ መንገዶችም ልንረዳቸው ይገባል። "ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፣ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ... " (ያዕ 1:27)።

በቤተ ክርስቲያን ምሕረት የማድረግ ስጦታ ያላቸው አማኞች በብዛት መኖራቸው አስፈላጊ ነው። ሌሎችን አገልግሎቶች ሁሉ የሚደግፈው ይህ ስጦታ ነው። ለምሳሌ ያህል፦ የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ ያለው ምሕረት የማድረግ ስጦታ ሊኖረው ይገባል። ምሕረት የማድረግ ስጦታ ወንጌል ሰባኪው ላልዳኑ ሰዎች እንዲያዝንና እንዲራራላቸው ይረዳዋል። የወንጌል ስብከት አገልግሎቱ ውጤታማ የሚሆነው የዚያን ጊዜ ነው።

ምሕረት የማድረግ ስጦታ ያለው ሰው ምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ በርናባስ ጥሩ ምሳሌ ነው። እርሱ ታላቅ ርኅራኄ የነበረው ሰው በመሆኑ ይህም ለአንዳንድ በጣም ችግረኛ ለነበሩ ሰዎች አገልግሎት እንዲሰጥ አድርጎታል። ስለ በርናባስ የተጻፉትን የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት (የሐዋ 9:27፤ 11:25-26 ፤ 15:37-39)።

(7). ምሕረት ማለት

ሀ. ኃይል
ለ. ፍቅር
ሐ. ሐዘኔታ
መ. ርኅራኄ

(8). ሰዎች _____ በሆኑበት ጊዜ አንድ ሰው ርኅራኄ እንዲያሳያቸው ይፈልጋሉ።
ሀ. ጠንካራና ጤናማ
ለ. ሐዘንተኛና ብቸኛ
ሐ. የወንጌል ሰባኪዎች
መ. ኃጢአተኞች

(9). ምሕረት የማድረግ ስጦታ

ሀ. ብዙ አማኞች ሊኖራቸው የሚገባ ስጦታ ነው።
ለ. የወንጌል ሰባኪው ብቻ የሚያስፈልገው ስጦታ ነው።
ሐ. የብዙ ሰዎችን ችግር የሚያስወግድ አገልግሎት ነው።

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

ምሕረት የማድረግ ስጦታ ተግባር አማኞች የሌሎች ሰዎችን ስሜት እንዲካፈሉ ወይም እንዲያዝኑላቸው መርዳት ነው። ምሕረት የማድረግ ስጦታ ዓላማ በችግሮቻቸው ጊዜ በጎናቸው በመቆምና በመርዳት ለችግረኞች ምሕረትን ማሳየት ነው። ምን አይነት ርካታን የሚያስገኝ ስጦታ ነው!

(10). የሚከተለውን መግለጫ የተማሃላ ለማድረግ ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛ የሆነውን ፊደሉን በመክበብ አመልክት። አንድ አማኝ ሃዘን ለደረሰበት ሌላ አማኝ የጎዘኑ ተካፋይ መሆኑን ሲገልጽ . . .

ሀ. ምሕረት የማድረግ ስጦታ ተግባር እንለዋለን።
ለ. ምሕረት የማድረግ ስጦታ ዓላማ እንለዋለን።

የመርዳት ስጦታ

ዓላማ 4 የመርዳትን ስጦታ ተግባርና ዓላማን መግለጽ።

የስጦታው ምንነት ሲገለጽ

"እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን .... አርዳታንም ....አድርጓል" (1ቆሮ 12:28)።

የመርዳት ስጦታ አማኙን የሚረዱ ድርጊቶችን በመፈጸም የሌሎች ሰዎችን ችግር ለማቃለል ወይም ለመርዳት ከመንፈስ ቅዱስ ብርታትን እንዲቀበል የሚያደርግ ስጦታ ነው።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

ማንኛውም የክርስቶስ አካል ብልት የሆነ ሰው የጸጋ ስጦታ እንዳልተሰጠው ሊሰማው አይገባም። መቼም ሁሉም አማኝ ሐዋርያ፣ ነቢይ፣ የወንጌል ሰባኪ፣ ወይም መጋቢ- አስተማሪ ሊሆን አይችልም፣ ሆኖም ማንኛውም አባል የመርዳት ስጦታ ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን አንዳንድ አማኞች ሌሎችን የመርዳት ከመንፈስ ቅዱስ የተሰየ ስጦታ የተቀበሉ ይመስላል። እንደዚህ አይነት ሰዎች የሌሉትን ችግር ለማስወገድ ልዩ

ችሎታ የተሰጣቸው ናቸው። የመርዳት ስጦታ በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን እንዲት በተግባር ላይ ይውል እንደነበረ የሚያሳዩንን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መመልከት ይረዳል።

1. "እርሱም ወደ አካይያ ማለፍ በፈቀደ ጊዜ ወንድሞቹ አጽናኑት፥ ይቀበሉትም ዘንድ ወደ ደቀ መዛሙርት ጻፉለት" (የሐዋ 18:27) በአዲሱ ትርጉም አጵሎስን ወንድሞች "አበረታቱት" ይላል፥ ይህም የመርዳት ምሳሌ ነው።

2. "በክርስቶስ አብሮን ለሚሠራ ለኢሩባኖን. . . ለላምታ አቅርቡልኝ" (ሮሜ 16:9)። ይህ ሰው ጳውሎስን በመርዳት በኩል ምን እንዳደረገ አልተገለጸልንም። ምናልባት ጥቂት የስብከትና የማስተማር አገልግሎት አበርክቶ ይሆናል። ወይንም ምዕመናኑን መዝሙር በማዘመር ወይም በመምራት ረድቶም ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ጳውሎስ በሚሠራው የአገልግሎት ቡድን ገንዘብ ያዥ በመሆን ረድቶ ሊሆን ይችላል። አለዚያም አዲስ አማኞችን በመጎብኘት ተባብሮ ሊሆን ይችላል። እንዲት እንደረዳ ማወቅ የምንችለው በመገመት ብቻ ነው። ይሁን እንጂ የመርዳት ስጦታ ያላቸው አማኞች ለክርስቶስ አካል ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ መገመት አያዳግትም።

3. "አንተም ደግሞ..... እንድታግዛቸው አለምንሃለሁ..... በወንጌል ከእኔ ጋር አብረው ተጋድለዋልና" (ፊልጵ 4:3)።

የዚህን ጥቅስ መሠረተ ሃሳብ ስንመለከት ሴቶችም የመርዳት ስጦታ ሊኖራቸው እንደሚችል ልንገነዘብ እንችላለን። እዚህም ላይ በድጋሚ እንዲት እንደረዱ በግልጽ አናውቅም። አዲሶችን ሴቶች አማኞች አግኝተው በማነጋገር ረድተው ሊሆን ይችላል። ለጳውሎስና በእርሱ ለሚመራው ቡድን ምግብ በማዘጋጀት ረድተው ሊሆን ይችላል። በምልጃና በጸሎት አገልግሎት ረድተው ሊሆን ይችላል። ለጳውሎስና በእርሱ ለሚመራው ቡድን ልብሶችን በመስፋትና ልብሶቻቸውን በማጠብ አገልግለው ሊሆን ይችላል። ስጦታው ይህን የመሰሉትን የጉልበት ሥራዎችንም ስለሚያጠቃልል አማራጮቹ ብዙዎች ናቸው።

በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን የመርዳት ስጦታ ላላቸው ሴቶች የተለጠ የተለየ መጠሪያ ስም "አገልጋይ" ወይም "ዲያቆኒት" የሚለው ነበር። "አገልጋይ የምትሆን እኅታችንን ፌበንን አደራ ብያችኋለሁ" (ሮሜ 16:1)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ አገልጋይ የሚለውን በግሪኩ "ዲያቆኒት" ይለዋል። የተለየ የመርዳት ስጦታ ያላቸው ወንዶች ደግሞ "ዲያቆን" ተብለው ይጠሩ ነበር። "በዲቁና ሥራ በመልካም ያገለገሉ ለራሳቸው ትልቅ ማዕረግ ... ያገኛሉ" (1ጢሞ 3:13)።

በደቡብ አሜሪካ ውስጥ ታላቅ የእግዚአብሔር ኃይል እንቅስቃሴ የሚታይባት አንድ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። በዚያች ቤተ ክርስቲያን

ብዙ ሰዎች ድኅነትን አግኝተው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተዋል። የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ- አስተማሪም ታማኝ ስለ ነበረ የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ይስብካል፣ ምዕመናንን ይጎበኛል። በምዕመናኑ መካከል አንድ ምንም የማትታወቅ ዝምተኛ ታናሽ ሴት ነበረች። በጉባኤው መካከል የምትናገረው ነገር አልነበራትም፣ ሆኖም ብዙውን ጊዜ በጸሎት በማሳለፍ መጋቢውን በከፍተኛ ደረጃ ትረዳው ነበር። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የመርዳት ስጦታ ተስጥቷት ነበር።

(11). ከዚህ በታች ከቀረቡት መግለጫዎች እውነት ከሆኑት ከፊደሎች አንጻር 'እ' ሐስት ከሆኑት ከፊደሎች አንጻር 'ሐ' ጻፍ

_____ሀ. የመርዳት ስጦታ ለሌሎች ሰዎች እርዳታን የሚሰጥና ችግራቸውን የሚ ያቃልል ነው።
_____ለ. የመርዳት ስጦታ ሊኖራቸው የሚገባው ጥቂት አማኞች ብቻ ናቸው
_____ሐ. ወንዶችም ሴቶችም የመርዳት ስጦታ ሊኖራቸው ይችላል።
_____መ. በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን የመርዳት ስጦታ የነበራቸው ሴቶች አገልጋይ - ዲያቆኒት ተባሉ ይባሉ ነበር።

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

የመርዳት ስጦታ ተግባር በክርስቶስ አካል ውስጥ ለሚገኙ አባሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና ባጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንን መርዳት የሚችሉበትን ጉልበት ወይም ብርታት መስጠት ነው። የስጦታው ዓላማ የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲስፋፋ ማከናወን የሚገባው ሥራ እንዲሠራ መርዳት ነው። ተግባሩ የመርዳት ችሎታን የሚያመለክት ሲሆን ዓላማው ደግሞ ስለሚሰጠው እርዳታ በቀጥታ የሚናገር ነው።

ለምሳሌ ያህል አንድ ወንድም ለሌሎች የመጸለይ የተለየ ችሎታ አለው ስንል ይህ የመርዳት ስጦታ ተግባር ነው። ይሁን እንጂ ስጦታው መጸለይ ቢሆንም በመጸለይ ስጦታውን ተግባር ላይ ካላዋሰው ለቤተ ክርስቲያን ምንም አይጠቅማትም። በሚጸልይበት ጊዜ ግን ስጦታው የታቀደበትን ዓላማ ግብ ይመታል።

(12). በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አንድ ወንድም መጋቢው የታመሙ ሰዎችን በሚጎበኝበት ጊዜ ልዩ የመርዳት ችሎታ አለው። ይህ መግለጫ የሚያመለክተው የስጦታውን ተግባር ነው ወይስ ዓላማውን?

ሀ. ተግባሩን ለ. ዓላማውን

የሙከራ ፈተና

1. አንድ ሰው በልግስና ስጦታ አማካኝነት ሊያገለግል የሚችልባቸውን ሦስት መንገዶች ግለጽ።

2. የማስተዳደር ስጦታ ላላቸው የምንጠቀምባቸውን ሦስት ስሞች ግለጽ።

3. ከዚህ በታች ከተሰጡት ከእያንዳንዱ መግለጫ ቀጥሎ ባለው መስመር የተገለጸውን ስጦታ ስም ጻፍ።

ሀ. አንድን የአማኞች ሕብረት በበላይነት መቆጣጠር ወይም መመሪያ መስጠት _____
ለ. የሚረዱ ድርጊቶችን በመፈጸም የሰዎችን ችግር ማቃለል ወይም መርዳት _____
ሐ. የሌሎች ሰዎችን ችግር ለማስወገድ በነፃነት ወይም በልግስና መስጠት _____
መ. ለሌሎች ሰዎች ስሜታቸውን የምትካፈልና የምታዝንላቸው መሆንክን ማሳየት _____

4. _____ስጦታን የሚለማመድ ሰው ሰዎችን የማደራጀት፣ የመቆጣጠርና የመምራት ችሎታ አለው።

5. ዓላማው የሌሎችን ሰዎች የገንዘብ ችግር ማስወገድ የሆነው ስጦታ የ _____ ስጦታ ነው።

6. የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተመልከትና ከእያንዳንዱ ጥቅስ በኋላ የተገለጸውን ስጦታ ጻፍ

ሀ. የሐዋ 15:37-39 _____
ለ. የሐዋ 18:27 _____
ሐ. 1ነገ 17:8-16 _____
መ. የሐዋ 6:1-3 _____
ሠ. ማር 1:41 _____

7. ቀደም ባለው ክፍለ ትምህርት ያጠናሃቸውን ሦስት ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች ግለጽ። _____
_____

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. ሐ እና መ

7. ሐ እና መ

2. ሀ

8. ለ እና መ

3. ሀ

9. ሀ እና ሐ

4. መምራት፣ በበላይነት ማስተባበርና አቅጣጫ ማሳየት

10. ሀ

5. ሀ እና ሐ

11. ሀ. እ
ለ. ሐ
ሐ. እ
መ. ሐ

6. ለ

12. ለ

7 የጥበብ ቃል፣ የእውቀት ቃል፣ እምነት

ትምህርት

ባለፉት አራት ክፍለ ትምህርቶች ያጠናናቸው የመጀመሪያዎቹን ሁለት የአጋ ስጦታ ምድቦች ሲሆን፣ እነርሱም የአገልግሎት ስጦታዎችና ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች የተባሉት ናቸው። የመጀመሪያው ምድብ በክርስቶስ አካል ውስጥ በሚገኙ መሪዎች ላይ ያተኮረ እንደነበረ ተገንዝበናል። በዚህም ምክንያት እነዚህን ስጦታዎች የሚቀበሉት አማኞች ብዛት የተወሰነ እንደሆነ ተመልክተናል። ሁለተኛው የስጦታዎች ምድብ ለየት ያለ ሲሆን፣ ማንኛውም አማኝ ከእነዚህ ስጦታዎች አንደኛው ሊኖረው እንደሚችል ተረድተናል።

የአሁኑን ክፍለ ትምህርት የምንጀምረው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በተባለው በመጨረሻው ምድብ ነው። በዚህ ክፍለ ትምህርት የተለየ ትኩረት በመስጠት የምንመለከታቸው ስጦታዎች በመንፈስ ቅዱስ የተሰጡ መሆናቸውን የሚገልጸውን የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ እውነት ነው። ይህም ከእነዚህ ስጦታዎች አንዳቸውም በሰዎች ችሎታ ወይም ተሰጥኦ ሊከናወኑ እንደማይችሉም እንድንገነዘብ ያደርገናል።

ከዚሁ ጋር አያይዘን የምንመለከተው ሌላው ጉዳይ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካኝነት የተገኘው ተጨማሪ ኃይል በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አማካኝነት መገለጽ እንዳለበት ይሆናል። እግዚአብሔር በእያንዳንዱ አማኝ አማካኝነት ኃይሉ እንዲገለጽ ይፈልጋል። እነዚህን ስጦታዎች እንደሚገባ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ለመግለጽ እንደምንችል ማረጋገጥ የምንጀምረው ስለ ስጦታዎቹ ተገቢውን ግንዛቤ በሚገባ ስናገኝ ነው።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የጥበብ ቃል
- የእውቀት ቃል
- እምነት

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት በምታጠናቅቅበት ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ፦

- ሦስት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለይተህ ማወቅ
- የምታጠናቸውን ሦስት ስጦታዎች ተግባርና ዓላማ መግለጽ

- *መንፈስ ቅዱስ ከእነዚህ በእንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ስጦታዎች እንደ*ት ሊጠቀምብህ እንደሚችል *መረዳት*

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. 1ቆሮ ምዕራፍ 12 አንብብ።

2. የክፍለ ትምህርቱን ማጠናከሪያ አንብብ። በማስታወሻ ደብተርህ በዚህ ክፍለ ትምህርት ለተጠቀሱት ለሦስቱ ስጦታዎች አጠር አጠር ያሉ *መግለ*ጫዎችን ጻፍ።

3. ቀደም ብለህ እንዳጠናሃቸው ክፍለ ትምህርቶች ሁሉ በዚህም ክፍለ ትምህርት የተሰጡትን የ*መ*ከራ ፈተናዎች አጠናቅ።

4. 1ቆሮ 13 በቃልህ ማጥናት ቀጥል። የ*መ*ጀ*መ*ሪያዎቹን ዘጠኝ ቁጥሮች በማስታወሻ ደብተርህ ጻፋቸው። ይህንን ክፍለ ትምህርት በምትጨርስበት ጊዜ የ*መ*ጀ*መ*ሪያዎቹን አስር ቁጥሮች በቃልህ ማለት *መ*ቻል አለብህ።

የትምህርቱ ዝርዝር

የጥበብ ቃል

***ዓላማ 1** "የጥበብ ቃል" ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ማወቅና የስጦታውን ተግባርና ዓላማ መግለጽ።*

ስለ *መ*ንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለማጥናት *መ*ግቢያ ይሆነን ዘንድ በ*መ*ጀ*መ*ሪያ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 12:1 ላይ ይህንኑ ለማስተዋወቅ የጻፈውን እን*መ*ልከት። "ስለ *መ*ንፈሳዊ ነገር*ም*፣ ወንድሞች ሆይ፣ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ" የሚል ቃል እናገኛለን።

ከአጋ ስጦታዎች ጋር በተያያዘው ትምህርታችን ላይ እንደተረዳነው የእውቀትን አስፈላጊነት በሚገባ ተ*መ*ልክተናል። ጳውሎስ የእውቀትን አስፈላጊነት በሚገባ በ*መ*ረዳቱ፣ የእርሱ ታላቅ ምኞት ክርስቲያኖች ከነበሩበት አላዋቂነት እንዲላቀቁ ለ*መ*ርዳት ነበር። ስለሆነም "ወንድሞች ሆይ፣ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ" በማለት ይናገራል (1ቆሮ 10:1)። በ*መ*ልዕክቶቹ አምስት ጊዜ ይህን የ*መ*ሰለ ነገር ጽፎ እናገኛለን። (ሮሜ 1:1፣ 1ቆሮ 10:13፣ 12:1፣ 2ቆሮ 1:8 እና 1ተሰ 4:13)።

በማንኛውም *መ*ለክ እውነተኛ እውቀት አስፈላጊ እንደሆነ ጳውሎስ ተናግሯል። እግዚአብሔር አንዳቀደው ሁሉ እውቀትን ማግኘት የ*መ*ንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን የበለጠ ትርጉም ያላቸው እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

በቆሮንቶስ ሰዎች እንደሆነው ሁሉ አማኞች ብዙ እውቀት ሳይኖራቸው ስጦታዎቹ ግን ሊኖሯቸው ይችላሉ። ይሁን እንጂ ስጦታዎች ጠቃሚ እንዲሆኑ ከተፈለገ በእውነተኛ እውቀት ላይ የተ*መ*ሠረቱ ሊሆኑ ይገባል።

ስለ እነዚህ ስጦታዎች በምናጠናበት ጊዜ የምንሻው ስለ እያንዳንዱ ስጦታ በ*መ*ጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተ*መ*ሠረተ እውቀት ለማግኘትና፣ እንደሚገባም እንድንጠቀምባቸው ነው። ስለ እነዚህ ስጦታዎች ማወቅ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ላይ ሲውሉ ማየት ስለምንፈልግ *መ*ንፈስ ቅዱስ አእምሮአችንን ለበለጠ *መ*ረዳት ይከፍትልን ዘንድ የዘወትር ጸሎታችን ሊሆን ይገባል።

የጥበብ ቃል ትርጓሜ

"ለእንዱ ጥበብን *መ*ናገር በ*መ*ንፈስ ይሰጠዋልና...." (1ቆሮ 12:8)። ጥበብ በእውቀት ላይ የተ*መ*ሠረተ *መ*ልካም ውሳኔ ነው። ስለሆነም የጥበብ ቃል በእውቀት ላይ የተ*መ*ሠረተ የ*መ*ልካም ውሳኔ ቃል ቢሆንም ስጦታው ከዚህም የላቀ ነው።

እዚህ ላይ ቁልፉ ነገር "ቃል" የሚለው ነው። የቃሉ *መ*ሠረት በግሪክ "ሎጎስ" የሚለው ቃል ነው። በግሪክ ሎጎስ የሚለው ቃል ትርጉም "የእንድ ነገር ይዘት፣ ርዕሰ ጉዳይ የሚያስተላልፈው ስሜት" ማለት ነው። የ*መ*ንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ በቀጥታ ከእግዚአብሔር *መ*ንፈስ የተገኙ እንደ*መ*ሆናቸው መጠን የጥበብ ቃልም ከእግዚአብሔር የሚገኝ *መ*ግለጫ ነው። እዚህ ላይ *መ*ረዳት ያለብን የምናቀርበው ጥበብ የሚ*መ*ጣው ከእግዚአብሔር *መ*ሆኑን ነው። በዚህም ምክንያት በጥበብ ቃል ስጦታ አማካኝነት *መ*ንፈስ ቅዱስ ለእማኙ ከእግዚአብሔር ጥበብ ጥቂቱን ይሰጠዋል። "የጥበብ ቃል" የሚለው አባባል የሚናገረው ጥቂቱን ክፍል ነው። ለአንድ የተለየ ችግር *መ*ፍትሔ ስለሚሆነው የተለየ ጥበብ የሚናገር ይመስላል። ጥቂቱ የእግዚአብሔር ጥበብ በአስፈላጊው ጊዜ የሚነገር ብለን ማለት እንችላለን።

(1). **የጥበብ ቃል ማለት**

ሀ. በትክክለኛው ጊዜ የተነገረ ጥቂት የእግዚአብሔር ጥበብ ክፍል ነው።
ለ. ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ የስጦታ ተቀባዩን ጥበበኛ የሚያደርግ ነው።
ሐ. በ*መ*ንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተሰጠ ተፈጥሮአዊ ጥበብ ነው።

የጥበብ ቃል በምሳሌ ሲብራራ

የጥበብ ቃል *ሙሉ* በ*ሙሉ መ*ለኮታዊ አሠራር እንደሆነ አስቀድ*መን መ*ረዳት ይገባናል። ሐዋርያው ጳውሎስ "ለአንዱ ጥበብን *መ*ናገር በ*መ*ንፈስ ይሰጠዋልና" ይላል (1ቆሮ 12:8)። አንድ ሰው ትምህርት ቤት ገብቶ በ*መ*ማር የሚያገኘው ነገር አይደለም። ሰው በተፈጥሮው ጠቢብ ስለሆነም ሊኖረው አይችልም። ማንኛውም አማኝ የጥበብን ቃል ስጦታ ሊያገኝ የሚችለው በ*መ*ንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ብቻ ነው።

የጥበብን ቃል ምንነት *መ*ረዳት እንድንችል የተለያዩ ጥያቄዎችን እንጠይቅ፣

1. ***የጥበብ ቃል የሚሰጠው ለማን ነው?*** "... አንዱ *መ*ንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል" (1ቆሮ 12:11)።

እያንዳንዱ አማኝ ማንኛውንም ስጦታ በ*መ*ግለጽ በኩል እግዚአብሔር ሊጠቀምበት የሚችልበት ሁኔታ አለ። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ለ*መ*ረዳት የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ በ*መ*ንፈስ ቅዱስ ውስጥ የተካተቱ *መ*ሆናቸውን *መ*ገንዘብ ያስፈልጋል። እንግዲህ *መ*ንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ እስከሆነ ድረስ ስጦታዎቹም በአማኙ ውስጥ ይኖራሉ። ይሁን እንጂ የትኛውን ስጦታ ወይም ስጦታዎች በአማኙ ውስጥ የ*መ*ግለጹ ጉዳይ የ*መ*ንፈስ ቅዱስ ውሳኔ ነው።

የ*መ*ንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ *መ*ገኛ *መ*ንፈስ ቅዱስ ነው። በአማኙ ሕይወት ውስጥ በ*መ*ንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ስጦታዎቹ ይገለጻሉ፣ ከዚያም የተነሣ ለአማኙ የተሰጡ ናቸው ማለት ይቻላል።

የጥበብ ቃልን በ*ሚመ*ለከት በሐዋ 15:5-27 ያለውን ለምሳሌ ያህል ወስደን ብን*መ*ለከት ሁኔታውም፣ ቤተ ክርስቲያን አንድ ከባድ ውዝግብ ተፈጥሮ እንደ ነበር ለ*መ*ረዳት እንችላለን። ጉዳዩም ከአዲሶቹ አሕዛብ አማኞች ጋር የተያያዘ ሲሆን ችግሩን ለ*መ*ፍታት የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች ከሌሎች አማኞች ጋር በ*መ*ነጋገር ቦታዉ ተንጋገሩበት። አንዳንዶች አንድ ዓይነት ሃሳብ ሲያቀርቡ ሌሎች ደግሞ ከዚያ የተለየ ሃሳብ ያቀርቡ ነበር። በ*መ*ጨረሻም ከ*መ*ሪዎቹ አንዱ የነበረው ያዕቆብ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ። ያዕቆብም ተናግሮ ሲያበቃ ".... ያን ጊዜ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ከቤተ ክርስቲያን ሁሉ ጋር ...ፈቀዱ ...." ይላል።

እነዚህን ደረጃዎች ልብ አድርገን ብን*መ*ለከት በጥበብ ቃል ስጦታ አማካኝነት ለችግሩ *መ*ፍትሔ እንደተገኘ ለ*መ*ረዳት እንችላለን።

1. ከባድ ውዝግብ (ቁ. 5)

2. የአማኞች አካላት በአንድነት ተሰበሰቡ (ቁ. 6)

3. *መ*ሪዎቹና አማኞቹ ለውዝግቡ *መ*ፍትሔ ለማግኘት ጥረት አደረጉ (ቁ. 7-12)

4. በያዕቆብ በኩል በተገለጸው የጥበብ ቃል አማካኝነት *መ*ንፈስ ቅዱስ *መ*ልሱን ሰጠ (ቁ. 13-21)

5. የጥበብ ቃል ጉባዔውን ወደ ውሳኔ አ*መ*ጣው (ቁ. 22)

እንግዲህ በእነዚህ ጥቅሶች የጥበብ ቃል የተሰጠው በ*መ*ንፈስ ቅዱስ ሲሆን፣ ያም የጥበብ ቃል ለሕዝቡ *መ*ድረስ ነበረበት። *መ*ንፈስ ቅዱስ በያዕቆብ ውስጥ ስለነበረ በእርሱ አማካኝነት የጥበብን ቃል ለቤተ ክርስቲያን ገለጸ። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን የጥበብ ቃል ስጦታን ተቀበለች።

(2). ከዚህ ቀጥሎ ከተሰጡት *መ*ግለጫዎች እውነት ከሆኑት አንጻር 'እ' ሐሰት ከሆኑት አንጻር ደግሞ 'ሐ' ብለህ ጻፍ።

_____ሀ. የጥበብ ቃል በከፊል *መ*ለኮታዊ አሠራር አለው።
_____ለ. አንድ አማኝ የጥበብ ቃል ስጦታ አለው ማለት ትክክል አይደለም።
_____ሐ. የጥበብ ቃል ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ነው።
_____መ. የጥበብ ቃል ስጦታ ባላ*መ*ኑ ሰዎች አማካኝነት ይገለጣል።

(3). የሐዋ 6:1-7 አንብብ። ከዚህ ምንባብ የጥበብን ቃል የሚያ*መ*ለክተው ቁጥር የትኛው ነው? _____

2. ***የጥበብ ቃል ስጦታ የሚሠራው እንዴት ነው?*** አጥብቆ ማሰብን የሚጠይቅ ይሆን? *መ*ንፈስ ቅዱስ የጥበብ ቃል የሚያስተላልፍበት አማኝ ሊናገር የሚገባውን ሊያውቅ የሚችለው እንዴት ነው? እነዚህ ጥያቄዎች የተሟላ *መ*ልስ ሊያገኙ የሚችሉት የዚህ ስጦታ ልምድ ባላቸው ሰዎች ነው።

ዶናልድ ጂ የተባሉ ብርቱ የ*መ*ንፈስ ቅዱስ አማኝ የሆኑ አስተማሪ፣ "የጥበብ ቃል በሚገለጥበት ጊዜ አንድ ነገር ብልጭ ይላል። አንድ *መ*ለኮታዊ የሆነ *መ*ረዳት፣ ከሰብአዊ ልምዶች *መ*ዛግብት ሁሉ የሚልቅ የድምፅ ሰሜት ግንዛቤ ያለው ሲሆን፣ ይህ ስጦታ ያለው ሰው በዚያን ወቅት ትክክለኛው ነገር እንደተባለ ወይም እንዳለ ጥልቅ *መ*ረዳት ይኖረዋል" ሲሉ ተናገሩ።

የጥበብ ቃል በቀጥታ በ*መ*ንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ሊነገር ይችላል። ይህ ከሆነ ስጦታው ያለው ሰው *መ*ልዕክቱን ለጉባኤው በቀጥታ ያስተላልፋል (ኤፌ 1:17-19)። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጥበብ ቃል ተናግሮአል። ይሁን እንጂ ለእነርሱ ከ*መ*ናገሩ ቀደም ብሎ *መ*ንፈስ ቅዱስ ጥልቅ በሆነ *መ*ንገድ ለልቡ ተናግሮታል (1ቆሮ 2:5-15)።

3. *የጥበብ ቃል የሚገለጠው መቼ ነው?* የጥበብ ቃል የሚገለጽባቸውን ጊዜዎች ሁሉ መዘርዘር አስቸጋሪ ይሆናል። ብዙውን ጊዜ ሁኔታዎች የአጠቃቀሙን ወቅት ይወስናሉ። ከዚህም በተጨማሪ መንፈስ ቅዱስ አንድን ስጦታ በአማኙ ሕይወት የሚገልጸው አማኙ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ዝግጁና ራሱን የሰጠ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው። ጳውሎስ እንደተናገረው "እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን ... በአገልግሎታችን እንትጋ" (ሮሜ 12:6)። በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን የተገለጸበትን ሁኔታ ማስተዋል፥ ስለ ተሰጠን ስጦታ ግንዛቤ እንድናገኝ የሚረዳን መሆኑ ግልጽ ነው።

ሀ. ሰባኪው በሚሰብክበት ጊዜ ስለሚሆነው ነዐብራቅ በሐዋ 2:16-36 በተገለጸው በጴጥሮስ ስብከት ላይ እንመለከታለን። በስብከት ወቅት ስለሚታዩት ሁኔታዎች በሐዋ 7 ላይም ምልክቶችን እናያለን። (በሐዋ 6:10 ላይም የተጠቀሰውን ተመልከት።)

ለ. በቤተ ክርስቲያን ውዝግብ በተነሣ ጊዜ ስለሚከሰተው ሁኔታ (ሐዋ 15 ላይ የተጠቀሰውን ተመልከት።)

ሐ. ስደትም በሚደርስበት ጊዜ ስለሚከሰተው ሁኔታ ሐዋ 5:26-33 ተመልከት። በተለይም ቁ. 29ን ልብ ብሰህ አስተውል። "ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል"። ኃይለኛ የሆነ የጥበብ ቃል ነው። (በተጨማሪም ሉቃስ 12:12 እና 21:15 ተመልከት።)

መ. ምዕመናኑን የግል ችግር በሚያጋጥምበት ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ (የሐዋ 5: 1-11 ተመልከት።)

የጥበብ ቃል እንዴት ትልቅ ዋጋ ያለውና ጠቃሚ ስጦታ ነው! በእርግጥ ከታላላቆቹ ስጦታዎች አንዱ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም። በቤተ ክርስቲያን ሥራ ጠቃሚ ሆነን እንገኝ ዘንድ ይህ ስጦታ እንዲኖረን ብንፈልገው ጥሩ ይሆናል። መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ እንዲገለጽ የሚፈቅድ ከሆነ "አሁን አግኝቼዋለሁ" የሚል አስተሳስብ ሊኖረን አይገባም። ይልቁንም ስጦታዎቹን አካሉ ሰሆነችው ቤተ ክርስቲያን ለመስጠት እንደ አሸንዳ አድርጎ እንደሚጠቀምብን ልናስታውስና በዚህም ምክንያት በትህትናና በምስጋና ልንቀርብ ይገባናል።

(4). አማኞች የጥበብን ቃል የሚያስተላልፉት

ሀ. ያነበቡትን በመድገም ነው።
ለ. እግዚአብሔር እንዲናገሩ ስለሚፈልግባቸው ነገር በማሰብ ነው።
ሐ. መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩትን ቃል ሲሰጣቸው ነው።

(5). ከዚህ በታች ከቀረቡት መግለጫዎች እውነት በሆኑት አንጻር 'እ' ሐሰት በሆኑት አንጻር ደግሞ 'ሐ' ብለህ ጻፍ።

____ሀ. የጥበብ ቃል የሚሰጠው ስጦታው አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ነው።
____ለ. የጥበብ ቃል የሚሰጠው ለወንጌል አገልግሎት ብቻ ነው።
____ሐ. የጥበብ ቃል ለአንድ ግለሰብ በቀጥታ ሊነገረው አይገባም።
____መ. ሰዎች ያለ አግባብ በሚነቀፉበት ጊዜ የጥበብን ቃል ሊቀበሉ ይችላሉ።

የጥበብ ቃል የተሰጠበት ዓላማ

ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በምናጠናበት ጊዜ ዘወትር ልናስታውሰው የሚገባን አንድ ጠቃሚ የሆነ መመሪያ አለ። መመሪያውም፣ "ሁሉን ለማነጽ ይሁን" የሚለው ነው (1ቆሮ 14:26)። ማነጽ ማለት "መገንባት ማለት ነው።" ስለሆነም የጥበብ ቃል የተሰጠበት ዓላማ የክርስቶስን አካል ለመገንባት ነው ማለት እንችላለን። ይህ ሊሆን የሚችለው እንግዲህ የጥበብ ቃል ለአንድ አባል፣ ለአነስተኛ ሕብረት ወይም ጉባኤ ከተነገረ ነው።

አንድ ሰው ከሌሎች የተሻለ ወይም የበለጠ መንፈሳዊ እንደሆነ አድርጎ እንዲሰማው ይህ ስጦታ ፈጽሞ አልተሰጠም። የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆንና የእርሱ መሳሪያ መሆን ልዩ መብት በመሆኑ፥ የክርስቶስን አካል ለማነጽና ለመገንባት በታማኝነት ማገልገል ተገቢ ነው።

(6). በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከሰቱ ነገሮች በጥበብ ቃል አማካኝነት ሲፈቱ ቤተ ክርስቲያን _____ ።

የእውቀት ቃል

ዓላማ 2 የእውቀት ቃልን ተግባርና ዓላማ መግለጽ።

ዓላማ 3 የእውቀትን ቃል ተቀብለህ እንደሆነ እንዴት እንደምታውቅ መግለጽ ።

የእውቀት ቃል ትርጓሜ

"ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል" (1ቆሮ 12:8)። እውቀት ማለት "ማወቅ ነው።" የጥበብን ቃል ስናጠና እንደተመለከትነው ቃል የሚለው አገላለጽ በግሪክ ቋንቋ *ሎጎስ* ከሚለው የተገኘ ነው። *ሎጎስ* ማለት "የአንድ ነገር ይዘት፣ርዕሰ ጉዳይ፣ የሚያስተላልፈው ስሜት ማለት ነው።" ስለሆነም የእውቀት ቃል የእውቀት መግለጫ ሲሆን፣ የማን እውቀት መግለጫ እንደሆን መረዳት ይኖርብናል።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ *ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኙ* መሆናቸውን በድጋሚ ራሳችንን ብናስገንዝብ፣ የእውቀት ቃልን ስጦታ የሚሰጠውም የጥበብን ቃል በሚሰጠው በዚያው *በመንፈስ ቅዱስ* እንደሆነ በቀላሉ

ለመረዳት እንችላለን። መንፈስ ቅዱስ ከሥላሴ ሦስተኛው አካል እንደመሆኑ መጠን፣ ከእግዚአብሔር ስፉ የጥበብ መዝገብ ጠልቆ ሊያወጣ ይችላል።

እግዚአብሔር ምን ያህል እውቀት እንዳለው የሚገልጽ አንድ የላቲን ቃል አለ። ቃሉም "አምንሽንት" የሚል ነው። አምንሽንት የሚለው ቃል ከሁለት ቃላት የተውጣጣ ሲሆን ኦምኒ ማለት "ሁሉ" ማለት ነው። ሽአንት ደግሞ "ማወቅ" ማለት ነው። ሁለቱን ቃላት በአንድነት ስናቀናጃቸው "ሁሉን አዋቂ" የሚለውን ትርጉም እናገኛለን። ስለሆነም "እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው" ማለት ነው። እርሱ ማንኛውንም ነገር ያውቃል።

በእውቀት ቃል አማካኝነት መንፈስ ቅዱስ አማኙን ወሰን ከሌለው የእግዚአብሔር እውቀት ጥቂቱን እንዲናገር ያስችለዋል። በሌላ አነጋገር አማኙ በራሱ ችሎታ በምንም ዓይነት መንገድ ሊያውቅ የማይችለውን ነገር እንዲናገር ያደርገዋል። መንፈስ ቅዱስ የሚናገረውን ቃል ይሰጠዋል። ያ የተሰጠው ቃል ለአማኙ ወይም ለክርስቶስ አካል የተሰጠ የእውቀት ቃል ስጦታ በመባል ይታወቃል። ለአካሉ ጥቅም የተሰጠ በመሆኑ ለማያምን ሰው የተነገረ ቢሆንም እንኳ ስጦታው ለአካሉ የተሰጠ ነው።

(7). የእውቀት ቃል _____ ነው።

ሀ. ከጥበብ ቃል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ስጦታ
ለ. በጥናት አማካኝነት የሚገኝ እውቀት
ሐ. በሰዎች አማካኝነት የሚተላለፍ ከፊል የእግዚአብሔር እውቀት
መ. ተናጋሪው ቀደም ሲል ያልነበረው እውቀት

የእውቀት ቃል ሲዘራራ

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በአማኙ ሕይወት ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ኃይል እንዲጨምር ያደርገዋል። "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ" (የሐዋ 1:8)። ያ ኃይል የሚገለጸው በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አማካኝነት ሲሆን እያንዳንዱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የእግዚአብሔርን ኃይል ያሳያል። በበዓለ ሃምሳ ዕለት የቀድሞዋ ቤተ ክርስትያን የእግዚአብሔርን ኃይል ከተቀበለችበት ጊዜ ጀምሮ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ያ ኃይል እየተገለጸ ሄደ። አሁን እስቲ የእግዚአብሔር ኃይል በእውቀት ቃል አማካኝነት እንዴት እንደተገለጸ እንመልከት።

በመንፈስ የተሞሉ ሰዎችና የእውቀት ቃል

በመላው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የእውቀት ቃል መገለጦችን እንመለከታለን። የእውቀት ቃል የተናገረው እያንዳንዱ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር በምንም መንገድ ማወቅ የማይችለውን ነገር እንደተናገረ ለመረዳት እንችላለን።

1. የሐዋ 5:1-10 አንብብ። ሐናንያና ስጲራ በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንደዋሹ ጴጥሮስ *ያውቅ* ነበር። ለመዋሸት በምስጢር እንደተሰማሙ *ያውቅ* ነበር።

2. የሐዋ 8:23 *ተመልከት*። ስምዖን መራራ ቅንዓትና ኃጢአት በልቡ እንዳለ ጴጥሮስ *ያውቅ* ነበር።

3. የሐዋ 9:1-18 አንብብ። ሐናንያ (በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 5 ላይ የተጠቀሰው ሳይሆን) በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ስለ ሳውል ብዙ ነገሮችን ያውቅ ነበር።

ሳውል የት እንደነበረ *አውቋል* (ቁ. 11)

በዚያ ይጸልይ እንደነበር *አውቋል* (ቁ. 11)

ሳውል ራዕይ አይቶ እንደነበር *አውቋል* (ቁ. 12)

ሳውል የተመረጠ ዕቃ እንደሆነ *አውቆ* ነበር (ቁ. 15)

ሳውል በጌታ ምክንያት መከራ እንደሚቀበል *አውቋል* (ቁ. 16)

4. ሐዋ 10:19 *ተመልከት*። በቆርኔሌዎስ የተላኩ ሦስት ሰዎች ሊያነጋግሩት እንደመጡ ጴጥሮስ *ያውቅ* ነበር።

5. የሐዋ 27:13-44 አንብብ። በማዕበል በተናወጠችው መርከብ ውስጥ የነበሩት ተሳፋሪዎች በመርከቢቱ ውስጥ ካልቆዩ ሊድኑ እንደማይችሉ ጳውሎስ *ያውቅ* ነበር።

(8). ዮሐ 4:7-19 አንብብ። ጌታ ኢየሱስ የእውቀትን ቃል የተናገረው በየትኛው ቁጥር ላይ ነው?

በመናፍስት የተደፈኑ ሰዎችና የእውቀት ቃል

ጠንቋዮችን የመሰሰሉ ሰዎች ባልተለመደ ዓይነት መንገድ አንዳንድ ነገሮችን የማወቅ ኃይል ያላቸው ይመስላሉ። ታዲያ እነርሱ የእውቀት ቃል ስጦታ አላቸው ማለት ነው? አይደለም። ይሁን እንጂ ባልተለመደ ዓይነት መንገድ እውቀት ማግኘታቸው እውነት ነው። ግን እንዴት? መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ሁሉ ዕርኩሳን መናፍስትም እንዳሉ ማስታወስ ይገባናል። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። ዕርኩሳን መናፍስት ግን ከክፋው ከሰይጣን ናቸው።

ሰይጣን ሰዎች በራሳቸው ኃይል ሊያውቁ የማይችሏቸውን አንዳንድ ነገሮችን ያውቃል። ይሁን እንጂ ሰይጣን እንደ እግዚአብሔር አያደለም። *አንዳንድ ነገሮችን ብቻ ያውቃል* እንጂ ሁሉን ነገር አያውቅም።

ለምሳሌ ያህል በጌርጌሴኖን ብዙ አጋንንት ወይም ዕርኩሳን መናፍስት በውስጡ የነበሩበት አንድ ሰው ነበር። ጌታ ኢየሱስ ወደ እርሱ እጠገብ በደረሰ ጊዜ ዕርኩስ መንፈሱም፣ "የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፣ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? እንዳታሠቃየኝ እለምንሃለሁ" በማለት ፈጭኽ (ሉቃስ 8:28)።

ኢየሱስ ማን እንደሆነ ያ ሰውዬ እንዴት አወቀ? ጌታ ኢየሱስ እሱን ለመቅጣት ኃይል እንዳለው እንዴት አወቀ? እነዚህን ነገሮች ሊያውቅ የቻለው በውስጡ በነበሩት አጋንንት ወይም ርኩሳን መናፍስት አማካኝነት ነበር። ይህ እውቀት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገኘ አይደለም።

የምንናገረው የእውቀት ቃል ከመንፈስ ቅዱስ አማኝተን እንደሆነ እንዴት እርግጠኞች መሆን እንችላለን? ምናልባት በዕርኩስ መንፈስ ተገፋፍተን ተናግረን ይሆናል ብለን ልንፈራ ይገባናል? አማኙ ይህንን የመሰለ ፍርሃት ፈጽሞ ሊኖረው አይገባም። በእግዚአብሔር መንፈስ ከተሞላን ዕርኩሳን መናፍስትን መናገራት ፈጽሞ አይገባንም። እነርሱ ከእኛ ጋር ምንም ዕጣ ክፍል የላቸውም። "በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና" (1ዮሐ 4:4)።

(9). ከዚህ በታች ከቀረቡት መግለጫዎች እውነት ከሆኑት አንጻር "እ" ሐሰት ከሆኑት 'ሐ' ብለህ ጻፍ።

___ሀ. ጠንቋዮች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሆነው የእውቀት ቃል ስጦታ አላቸው።
___ለ. ሰይጣን ሁሉን አዋቂ ነው።
___ሐ. አማኞች በዕርኩስ መንፈስ ተገፋፍተው እንዳይናገሩ እጅግ ሊፈሩ ይገባቸዋል።
___መ. ዕርኩሳን መናፍስት ከመንፈስ ቅዱስ ይልቅ ብርቱዎች ናቸው።
___ሠ. የእግዚአብሔር መንፈስ ባለበት ዕርኩሳን መናፍስት ስፍራ የላቸውም።

የሰው መንፈስና የእውቀት ቃል

የእውቀት ቃል ስጦታ ከሰው ሃሳብ ይልቅ ይበልጣል። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ልዩነቱን አይረዱም። በአእምሮአቸው አንዳንድ ነገሮችን ያሰላስሉና ያንን የእውቀት ቃል ነው ብለው ይገምታሉ። አስተሳሰባችን ሊያታልለን ይችላል። ይህንን ነጥብ ሊያስረዳ የሚችል አንድ የገጠመኝን ነገር ልንገራችሁ። አንድ ምሽት በአንድ የቤት ሕብረት የጸሎት ስብሰባ ላይ የተገኙት አማኞች በዝማሬ አገልግሎታቸው ላይ ሊረዳቸው የሚችል የሙዚቃ መሣሪያ እንደሚያስፈልጋቸው በመገንዘብ መጸለይ ጀመሩ። ያ የሚፈልጉት ትክክለኛው መሣሪያ እዚያው ቤት ነበረ። ከሕብረቱ አባላት አንዱ የሆነ አንድ ሰው ከጌታ ዘንድ የእውቀት ቃል ስጦታ እንዳገኘ

በማመን ወዲያውኑ የቤቱን ባለቤት የሙዚቃ መሣሪያውን በዚያ ለሚገኘው የቤት ሕብረት እንድትሰጣቸው ነገራት።

ሴቲቱ ይህንን በሰማች ጊዜ ነገሩን በሚገባ ልትረዳው አልቻለችም። መሣሪያው የእርሷ እንዳልሆነና ከሌላ ሰው የተዋሰችው እንደሆነ ለሰውየው ነገረችው። ሰውዬው የተናገረው ከልቡ አውጥቶ እንጂ በእውቀት ቃል ስጦታ አማካኝነት አልነበረም።

የእውቀት ቃል እንዳገኘን እንዴት እርግጠኞች መሆን እንችላለን? ለሚያጋጥሙን አንዳንድ ሁኔታዎች እንደ መፈተኛ አድርገን የምንጠቀምባቸውን ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን መጠይቆች እንመልከት።

1. የራሴ ወይም የግሌ መሻት እንድናገር ገፋፍቶኝ ይሆን?

2. ከመንፈስ ቅዱስ የእውቀት ቃል ስጦታ እንዳገኘሁ እርግጠኛ ነኝ?

3. የእግዚአብሔር ሰላም በልቤ ይሰማኛል?

4. የተበሳጨሁበት ወይም ደስ ያልተሰኘሁበት ሰው ወይም ሁኔታ ይኖር ይሆን?

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥያቄዎች ለእንደኛው የምትሰጠው መልስ የሚያስጨንቅህ ከሆነ ከመናገርህ በፊት ጌታ ፊት በጸሎት መቅረብ የተሻለ ይሆናል። ለመናገር ነፃነት ሊሰማህ የሚገባው የቀረቡትን ጥያቄዎች ሁሉ በደስታ የምትመልስ ከሆነ ነው። እውነተኛን የእውቀት ቃል የሚያስተላልፍ አማኝ መናገር ስላለበት ቃል ጠንካራ ውስጣዊ ግፊት እንደሚሰማው ልታውቅ ይገባሃል። ልምምድ የመንፈስ ቅዱስን መነሳሳትን ለይተህ እንድታውቅ ይረዳሃል።

(10). አንድ የእውቀት ቃል በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ መሆኑን ማወቅ የምንችለው

ሀ. መልካም እስተማሪዎች ከሆንን
ለ. የጌታ ሰላም በልባችን የሚታወቀን ከሆነ
ሐ. በእንደ ሰው ተበሳጭተን ከሆነ
መ. ከጉዳዩ ጋር ምንም ግላዊ ፍላጎት ከሌለን ነው።

የእውቀት ቃል የተሰጠበት ዓላማ

የጥበብ ቃልና የእውቀት ቃል ስጦታ ዓላማ ተመሳሳይ ነው። የሁለቱም ዓላማ የክርስቶስን አካል ለማነጽ ነው። እነዚህ ሁለት ስጦታዎች የሚሠሩት በጉበረት ቢሆንም፣ የእውቀት ቃል ከጥበብ ቃል ቀደም ብሎ ሊመጣ ይችላል። በእውቀት ቃል ስጦታ አማካኝነት ጌታ ኢየሱስ ለሳምራዊቲቱ ሴት

ስሌ ቀድሞ ሕይወታ ነገራት። ከዚያ በኋላም በጥበብ ቃል ስጦታ አማካኝነት ለነበረባት ችግር መፍትሔ ሰጣት።

(11). በድጋሚ የጥበብ ቃል ስጦታ ዓላማን አንብብ። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የስጦታዎችን ሁሉ ዓላማ የሚገልጸው የትኛው ቃል ነው?

እምነት

ዓላማ 4 የእምነት ስጦታን ተግባርና ዓላማ መግለጽ።

ዓላማ 5 የእምነት ስጦታ እንዳለህ እንዴት ማወቅ እንደምትችል መረዳት።

የእምነት ትርጓሜ

"ለእንዱም በዚያው መንፈስ እምነት" (1ቆሮ 12፡9)። በአጠቃላይ አነጋገር እምነት የማመን ችሎታ ነው። አንድ ሰው እምነት ካለው ያ ሰው ያምናል እንላለን። ይሁን እንጂ የእምነት ስጦታ ሁሉም አማኞች ካላቸው የተለመደ እምነት ለየት ያለ ነው። የተለዩ ዓይነት ችግሮችን ለማስወገድ የሚያስችል በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ የተለየ ዓይነት እምነት ነው። እግዚአብሔር ሊሰጥ ከሚችለው ፍጹም እምነት ትንሹ ክፍልና ለእንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚሰጥ ነው ማለት እንችላለን፡

የእምነት ስጦታ መንፈስ ቅዱስ ስጦታውን በውስጡ የሚገልጽበት አማኝ ንብረት አይደለም። ስጦታው በአንድ ሰው ልብ ውስጥ የሚገባው በአንድ የተለየ ጊዜና አንድ የተለየ ችግርን ለማስወገድ ነው። ስጦታው ይሰጣል፣ ችግሩም ይወገዳል፤ ስጦታውም የታቀደለትን ዓላማ ግብ ይመታል።

(12). ከሚከተሉት መግለጫዎች እውነት ከሆኑት አንጻር 'እ' ሐሰት ከሆኑት አንጻር 'ሐ' ብለህ ጻፍ።

_____ሀ. ማንኛውም አማኝ የእምነት ስጦታ ሊቀበል ይችላል።
_____ለ. በእምነት ስጦታ አማካኝነት አማኝ የተለየ ዓይነት እምነት ይቀበላል።
_____ሐ. በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ስላለው የእምነት ስጦታን ሊቀበል ይችላል።

የእምነት ስጦታ በምሳሌ ሲብራራ

እምነት ምንጊዜም በእውቀት ላይ የተመሠረተ ነው። ለእምነታችን ማነስ እንዱ መግለጫም ይኸው ነው። አነስተኛ እውቀት ስላለን አነስተኛ እምነት አለን። እግዚአብሔር ፍፁምና ትክክለኛ እምነት ስላለው፥ የእምነትን ስጦታ ሊሰጠን ይችላል። ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት እርሱ ሁሉን ስለሚያውቅና ፍጹም እውቀት ስላለው ነው። በእምነት ስጦታ አማካኝነት፥

እንዳንድ የተሰዩ አስፈላጊ ነገሮች እንዲሚሉ ከፊሉ የእግዚአብሔር እምነት ይሰጣል። የእምነት ስጦታ ሲገለጽ ብዙውን ጊዜ ሦስት ነገሮች ይኖራሉ።

1. መፍትሔ የሌላቸው የሚመስሉ ሁኔታዎች ይከሰታሉ።
2. የእምነት ስጦታ ይሰጣል።
3. መፍትሔ ወታየት ይጀምራል።

ጴጥሮስና ዮሐንስ ለመጸለይ ወደ ቤተ መቅደስ በሄዱበት ጊዜ የሆነው ነገር የእምነት ስጦታ እንዴት እንደሚሠራ እንድንገነዘብ ይረዳናል። የሐዋ 3፡1-11 እንብበህ ሁኔታውን ሰራስህ ተረዳ። በዚህ ታሪክ ውስጥ ከፍ ብለው የተጠቅሱት ሦስቱም ነገሮች ተከናውነዋል።

1. ተስፋ የሌለው ሽባ ሰው መልካም በተባለችው የቤተ መቅደስ ደጃፍ ተቀምጦ ነበር። በሕይወት ዘመኑ በሙሉ ማለትም፥ ለእርባ ዓመት፥ ሽባ ሆኖ ቆይቷል። ኑሮውን ለመግፋት ማድረግ የሚችለው መለመን ብቻ ነበር። ሰዎች ሊረዱት ፈጽሞ አልቻሉም።

2. ከዚያም ጴጥሮስ ልዩ የሆነ እምነት እንዳለው ተገነዘበ። ይህም በእርግጥ ከእግዚአብሔር የሆነ እምነት ስለነበረው ለሽባው ሰውዬ "በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ" አለው (የሐዋ 3፡6)።

3. ለሽባው በሆነለት ነገር ምክንያት ጴጥሮስ በእርግጥም የእምነት ስጦታ እንደነበረው እናውቃለን። "በዚያን ጊዜ እግሩና ቁርጭምጭሚቱ ጸና፣ ወደ ላይ ዘሎም ቆመ፣ ይመላለስም ጀመር" (የሐዋ 3፡7)። የሽባው እግር ተፈታ።

መንፈስ ቅዱስ ባረገም በዚህ ሁኔታ መሥራት ይፈልጋል። ታላላቅ ችግሮችንና ጥያቄዎችን ሊፈታ የሚችለውን ከእግዚአብሔር የሚሰጠውን የተለየ እምነት ሊሰጠን ይፈልጋል። መንፈስ ቅዱስን በልባችን ባስቀመጠ ጊዜ እንደ ጴጥሮስ እርምጃ ሰመውሰድ የሚያፍሩ አማኞችን መንፈስ ቅዱስ ያለጥርጥር ይፈልጋል። ብዙውን ጊዜ አማኞች እርምጃ ለመውሰድ ይፈራሉ። በዚህም ምክንያት እምነት ሳይሠራ ይቀራል።

የእምነት ስጦታ እንዳሰኝ እንዴት ማወቅ እችላለሁ? የዚህ ስጦታ እንዳለን በውስጠኛው የሰውነት ክፍላችን ወይም በመንፈሳችን ማወቅ እንችላለን። በእንድ በኩል ስንመለከተው እምነት ማለት "ጥልቅ የሆነ እርግጠኛነት" ነው። መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የሆነውን እምነት ከፊል ሲሰጠን እግዚአብሔር አንድን ነገር እንደሚያደርግ ጥልቅ የሆነ እርግጠኛነት በሕይወታችን ይሰጥናል። ይህን መሳዩን እምነት የተቀበለ አማኝ እግዚአብሔር አንድ ነገር ያደርጋል ብሎ ተስፋ ማድረግ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እርምጃ እንደሚወስድ ያውቃል።

(13). የሚከተሉትን መግለጫዎች አጠናቅ።

ሀ. የእምነት መሠረት _____ ነው።
ለ. ፍጹም እውቀት ለፍጹም_____አስፈላጊ ነው።
ሐ. አማኞች ጴጥሮስ "መልካም በተባለችው ቤተ መቅደስ በር" ካደረገው ጋር ተመሳሳይ የሆነ ድርጊት ሊፈጽሙ የሚችሉት_____ካላቸው ነው።
መ. በእምነት ስሞታ አማካኝነት አግዚአብሔር _____እናውቃለን።

የእምነት ስሞታ የተሰጠበት ዓላማ

ለጥበብ ቃልና ለእውቀት ቃል ስጦታዎች ተመሳሳይ ዓላማ እንዳላቸው ተመልክተናል። ሁለቱም ስጦታዎች የክርስቶስን አካል እንዲያንጹ ተሰጥተዋል። የክርስቶስን አካል ለማነፅ ሁለቱ ስጦታዎች በሕብረት እንዲሠሩ እንደሚሠሩ ተገንዝበናል። የእምነት ስሞታም ዓላማ ከእነዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። አሁን እያጠናናቸው ያለነውን ዘጠኝ ስጦታዎች ከመዘርዘሩ በፊት ሐዋርያው ጳውሎስ በተለየ መንገድ ገልጾታል፣ "መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል" በማለት ነበር (1ቆሮ 12:7)።

በእምነት ስሞታ አማካኝነት መላው አካል ይጠናከራል፣ ይታነፅማል። በእምነት ስሞታ መገለፅ አንድ አባል ብቻ የሚጠቀም እንኳ ቢሆን፣መላው አካል ታንጿል ማለት ይቻላል። አንድ አባል በሚታነፅበት ጊዜ አባሎች በሙሉ ይታነፃሉ። "አንድም ብልት ቢሰቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሰቃያሉ፣ አንድ ብልትም ቢከበር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል" (1ቆሮ 12:26)።

(14). የእምነት ስሞታ የተሰጠበት ዓላማ፦

ሀ. ከጥበብ ቃል ስጦታ ዓላማ ጋር በመጠኑ የተቀራረበ ነው።
ለ. ከጥበብ ቃል ስጦታ ዓላማ የተለየ ነው።
ሐ. ከጥበብ ቃል ስጦታ ዓላማ ጋር ተመሳሳይ ነው።

የመከራ ፈተና

እውነት - ሐሰት። ከሚከተሉት መግለጫዎች እውነት ከሆኑት አንጻር 'እ' ሐሰት ከሆኑት አንጻር ደግሞ 'ሐ' ብለህ ጻፍ።

___1. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በአማኙ ውስጥ ይኖራሉ።

___2. በሐዋ 8:23 የእውቀት ቃል ስጦታ ሲሠራ ታይቷል።

___3. እግዚአብሔር "አምኒሽንት" ነው ሰንል በሁሉም ስፍራ ይገኛል ማለታችን ነው።

___4. አማኙ የእግዚአብሔርን ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን በማስተላለፍ እንደ አሽንዳ ያገለግላል።

___5. በዚህ ክፍለ ትምህርት ያጠናናቸው ስጦታዎች ለአማኞች ሁሉ ከመሆን ይልቅ በተለይ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚሆኑ ነበሩ።

___6. የጥበብ ቃል ማለት በትክክለኛው ጊዜ የተነገረ የሰው ጥበብ "ጥቂት ክፍል" ነው።

___7. የጥበብ ቃል፣ የእውቀት ቃልና የእምነት ስጦታ ዓላማ ቤተ ክርስቲያንን ማነፅ ነው።

___8. አንድ አማኝ የእውቀት ቃል ሲናገር በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር በምንም መንገድ ሊያውቀው የማይችለውን ነገር ይናገራል።

___9. የእምነት ስጦታ የተሰጠበት ዓላማ ሌሎች ስጦታዎች ከተሰጡበት ዓላማ ጋር ተመሳሳይ ነው፥ ሆኖም ተግባሩ ይለያል።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. ሀ

8. በቁ. 17 እና 18 "ኢየሱስ ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ እምስት ባሎች ነበሩሽና፥ አሁን ከእንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፥ በዚህስ እውነት ተናገርሽ አላት"።

2. ሀ. ሐ ሐ. እ
ለ. እ መ. ሐ

9. ሀ. ሐ ሐ. ሐ ሠ. እ
ለ. ሐ መ. ሐ

3. "ወንድሞች ሆይ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፥ ለዚህም ጉዳይ እንሾማትዋለን" (ቁ. 3)

10. ለ እና መ

4. ሐ

11. ማነፅ፣ መግንባት

5. ሀ. እ ሐ. ሐ
ሰ. ሐ መ. እ

12. ሀ. እ ሰ. እ ሐ. እ

6. ትታነሣለች፣ ትነሳለች

13. ሀ. እውቀት ሐ. የእምነት ስጦታ
ለ. እምነት መ. እርምጃ እንደሚወስድ

7. ሐ እና መ

14. ሐ

8 የፈውስ ስጦታዎች፣ ተዓምራትን ማድረግና ትንቢት

ትምህርት

በትምህርታችን ውስጥ የመጨረሻዎቹ ሦስት ክፍለ ትምህርቶች በ1ቆሮ 12፡ 8-10 በተዘረዘሩት ዘጠኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ባለፈው ክፍለ ትምህርታችን ስለ መጀመሪያዎቹ ሦስት ስጦታዎች ማለትም ስለ ጥበብ ቃል፣ ስለ እውቀት ቃልና ስለ እምነት ባጠናንበት ወቅት እነዚህ ስጦታዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል መግለጫዎች እንደሆኑ ተመልክተናል። እነዚህ ስጦታዎች ሁሉ ልዕለ - ተፈጥሮአዊ በሆነ ሁኔታ እንደሚሠሩም ተረድተናል። ከስጦታዎቹ ማንኛውንም እንኳ ቢሆን በስብእዊ መንገድ ማግኘት አይቻልም። የተማርነው ሌላው ነገር ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ የጋራ ዓላማ እንዳላቸው ሲሆን፣ ዓላማውም የክርስቶስን አካል ለማነጽ ነው።

በዚህ ክፍለ ትምህርት የምናጠናው ስለ ሦስት ተጨማሪ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ነው። ስስ ስጦታዎቹ የምናጠናው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀረቡት ቅደም ተከተል መሠረት ይሆናል። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች በተለየ ቅደም ተከተል ያስቀምጧቸዋል። ይሁን እንጂ ሁሉም ከመንፈስ ቅዱስ የተገኙ በመሆናቸው ስለ ስጦታዎቹ የምናጠናበት ቅደም ተከተል አስፈላጊ አይደለም። የእነዚህ ስጦታዎች አሠራር አንዳንድ ጊዜ የሚወራረሱ መሆናቸውንም ተገንዝበናል። አንዳንድ ጊዜ አያሌ ስጦታዎች በአንድ ጊዜ የሚገለጹ ይመስላል። የእነዚህን ስጦታዎች አሠራር በተመለከተ አሁንም መንፈስ ቅዱስ በሚናገርህ ጊዜ ድምፁን ስምተህ ለመታዘዝ ዝግጁ ሁን። በሕይወትህ ላይ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ሲሰማህ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈቃዱን ለማድረግ ቀላል ላይሆን ይችላል። ሆኖም ለእርሱ ፈቃድ ራስህን አሳልፈህ ከሰጠህ ለክርስቶስ አካል ወይም ለቤተ ክርስቲያን በረከት እንድትሆን ያደርግሃል።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የፈውስ ስጦታዎች
- ተዓምራት ማድረግ
- ትንቢት

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

- ሦስት ተጨማሪ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን መዘርዘር።

- በዚህ ክፍለ ትምህርት የተጠቀሱትን ሦስት ስጦታዎች ተግባርና ዓላማ መግለጽ።
- ከእነዚህ ስጦታዎች አንዱ ወይም ከዚያም በላይ በአንተ ላይ እንዲት እንደሚገለጽ መዘርዘር።
- በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተጠቀሱ ሁኔታዎችን በመጥቀስ የእያንዳን ዱን ስጦታ አጠቃቀም መግለጽ።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ሮሜ 12:3-6ና 1ጴጥ 4:10-11 አንብብ።

2. የክፍለ ትምህርቱን ማጠናከሪያ አንብብ። ባለፈው ክፍለ ትምህርት የመጀመሪያዎቹን ሦስት ስጦታዎች መግለጫ በማስታወሻ ደብተርህ አስፍረሃል።

3. በመጨረሻ የመከራ ፈተናዎች አጠናቀህ ሥራ።

4. 1ቆሮ 13:11-12 በቃልህ አጥና።

የትምህርቱ ዝርዝር

የፈውስ ስጦታ

ዓላማ 1 የፈውስ ስጦታዎችን ተግባርና ዓላማ መግለጽ።

ዓላማ 2 የፈውስ ስጦታዎችን በመግለጽ በኩል መንፈስ ቅዱስ እየተጠቀ መብህ እንደሆነ እንዲት እንደምታውቅ መግለጽ።

የስጦታዎቹ ትርጓሜ

"ለእንዳም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ" (1ቆሮ 12:9)።

ፈውስ ማለት "ሙሉ ወይም ጤናማ ማድረግ ነው።" *ስጦታ* ማለት "ፀጋ፣ ውሰታ፣ ቸርነት" ማለት ነው። ስጦታ ስለሚለው ቃል ማሰባችን አስፈላጊ ነው። *ስጦታዎች* የሚለው የብዙ ቁጥር ስለሆነ ከአንድ በላይ የሆኑ የፈውስ ስጦታዎችን ያመለክታል። ስለዚህ ጉዳይ በይበልጥ ወደኋላ እንመለከታለን።

የፈውስ ስጦታዎች በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔር ፀጋ፣ የውሰታውና የቸርነቱ መግለጫዎች ናቸው። ሀዋርያ ካርተር ሲናገሩ "የፈውስ ስጦታዎች በበሽታዎች ክልል ላይ የተገለጸ የእግዚአብሔር ኃይል ነው" ብለዋል።

እነዚህ ስጦታዎች ከመንፈስ ቅዱስ የሚፈልቁና በአማኙ አማካኝነት ፈውስ ለሚያስፈልጋቸው የሚደርስ በመሆኑ፣ የፈውስ ስጦታዎች የሚሰጡት ለሚያስፈልጋቸው ነው። ስጦታዎቹ የሚገለጹት በአማኞች በኩል ሲሆን፣ አንድ የተሰየ አማኝ ብቻ የፈውስ ስጦታ አለው ከማለት ይልቅ፣ የፈውስ ስጦታዎች መንፈስ ቅዱስ በተሞሉ አማኞች አማካኝነት በቤተ ክርስቲያን ይገለጻሉ ማለት የተሻለ ነው።

(1). የሚከተሉትን መግለጫዎች አጠናቃቸው።

ሀ. የፈውስ ስጦታ የሚሰጡት በ _____ አማካይነት ነው።
ለ. ፈውስ የሚለው ቃል ትርጉም _____ ነው።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

በሽታ፣ ደዌና አካለ ስንኩልነት በሰዎች ዘንድ የተለመዱ ናቸው። አማኞች እንኳ ሳይቀሩ እነዚህ ችግሮች ሊያጋጥማቸው ይችላል። ሕመም፣ደዌና አካለ ስንኩልነት የሰው ልጅ በኃጢአት የመውደቅ ውጤቶች ናቸው።

ይህንን ስንል ታዲያ አንድ ሰው የሚታመመው ኃጢአት ስለሠራ ነው ማለታችን አይደለም። የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት፣ "መምህር ሆይ፣ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሰራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ" ብለው በጠየቁት ጊዜ፣ "የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሰሩም" ብሎ መለሰላቸው (ዮሐ 9:2-3)።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ኃጢአት በማድረጋቸው ምክንያት ይታመማሉ። ጌታ ኢየሱስ፣ "እነሆ ድነሃል፣ ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደፊት ኃጢአት አትሥራ" በማለት የተናገረው ስለዚሁ የሚያስረዳ ነው (ዮሐ 5:14)።

የበሽታችን፣ የደዌያችን ወይም የአካለ ስንኩልነታችን ምክንያት ምንም ዓይነት ቢሆን እግዚአብሔር ግን እንድንፈወስ ይፈልጋል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ፈውስ ለሚያስፈልጋቸው አንዳንድ ሰዎች እንኳ ፈውስን ሳይሰጥ ይቀራል። ለዚህም ሁሌታ አያሌ ምክንያቶች ይኖራሉ።

1. *አለማመን*:- ኢየሱስም "ለሚያምን ሁሉ ይቻላል" አለው። ወዲያው የብላቴናው አባት ፈጠነ፣ "አምናለሁ አለማመኔን እርዳው" አለ (ማር 9:24)።

2. *ከክርስቶስ አካል ጋር ያለን ግንኙነት የተሰናከለ ሲሆን*:- "ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ለለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፣ ይጠጣልምና። ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ አያሌዎችም እንቀላፋተዋል" (1ቆሮ 11:29-30)። በዚህ ላይ *የጌታን ሥጋ*

ለለማይለይ የሚለው ሌሎቹን የክርስቶስ አካል ብልቶች እንደ ብልት አለመቁጠር ማለት ነው።

3. *የተለዩ ምክንያቶች*፦ 2ቆሮ 12:7-10 እንብብ።

(2). አንዳንድ ጊዜ ፈውስ የማይከናወንበት ምክንያት፦

ሀ. በታመመ ሰው ሕይወት ውስጥ አንድ ነገር ለመፈጸም እግዚአብሔር ሕመምን ይጠቀማል።
ለ. ሕመምተኛው ብዙ ማመን ስለሚያስፈልገው ነው።
ሐ. ሕመምተኛው ሌሎች ወንድሞችን ስለሚያሳዝን ነው።
መ. አለማመን እግዚአብሔርን እንዳይሠራ ስለሚከለክለው ነው።

የፈውስ ስጦታዎች እንዴት እንደሚሠሩ መረዳት ያስፈልጋል። ለመረዳትም የምንችለው ለእያሌ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ነው።

ፈውስን ለማስገኘት መንፈስ ቅዱስ የሚጠቀምበት ማንን ነው?

የፈውስ ስጦታዎችን መግለፅ ከተወሰኑ ሰዎች ጋር ብቻ የተያያዘ ነው? መንፈስ ቅዱስ በእርግጥ ፈውስ ለሚያስፈልጋቸው ፈውስን ለማምጣት ማንኛውንም ሰው ሊጠቀምበት ይችላል። ሆኖም ይህ ስጦታ በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቁ ሰዎች አማካኝነት በበለጠ ነፃነት ሊተላለፍ ይችላል።

ይሁን እንጂ የፈውስ ስጦታዎች ብዙውን ጊዜ የሚገለጡት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች አማካኝነት ነው። ይህም ሊሆን የሚችልበት ምክንያት መላ ሕይወታቸውን ምዕመናንን ለማገልገል የሰጡ በመሆናቸው ነው። ከዚህም በስተቀር ፈውስ ከሚያስፈልጋቸው ሰዎች ጋር የመገናኘት እድላቸው ከፍ ያለ ነው።

በሐዋርያት ሥራ ፈውስን ለማስገኘት እነማንን እንደተጠቀመባቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በእርጋታ ተመልከት።

1. ጴጥሮስና ዮሐንስ - (ሐዋርያት) የሐዋ 3:1-11

2. ጴጥሮስ - (ሐዋርያ) የሐዋ 5:15

3. ፊልጶስ - (ወንጌላዊ) የሐዋ 8:5-7

4. ሐናንያ - (ያልታወቀ አማኝ) የሐዋ 9:17-18
5. ጴጥሮስ - (ሐዋርያ) የሐዋ 9:32-34

6. ጳውሎስ - (ሐዋርያ) የሐዋ 14:8-10
7. ጳውሎስ - (ሐዋርያ) የሐዋ 28:7-9

ከዚህ በላይ በቀረበው ዝርዝር አማካኝነት የምንረዳው አብዛኛው ፈውስ የተፈጸመው በሐዋርያት አማካይነት እንደሆነ ነው። ይህ ሊሆን የቻለው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ፣ የራሳቸው የሐዋርያት ዘገባ በመሆኑ ሊሆን ይችላል።

የፈውስ አገልግሎት ላላቸው የተለዩ ቡድኖች ሐዋርያው ያዕቆብ ልዩ መመሪያ ሰጥቷል። መመሪያውንም የሰጠው ለምዕመናንና ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ነው። "ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ" (ያዕ 5:14)። ይህም የሚያስተምረን መንፈስ ቅዱስ የፈውስ ስጦታዎችን በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አማካኝነት እንደሚሰጥ ነው። ሐናንያን እንደተጠቀመበት መንፈስ ቅዱስ ማንኛውንም አማኝ በፈውስ ስጦታ ሊጠቀምበት ይችላል።

ምን ዓይነት ሕመም፣ ደዌና የአካል ጉድለት ሊፈወስ ይችላል?

"ኢየሱስም፣ በሕዝቡም ያሰውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ ይዞር ነበር" (ማቴ 9:35)። ይህንኑ የመሰለ ነገር በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል። "በኢየሩሳሌም. . . ዙሪያ ካለችው ከተማ ድውያንንና በርኩሳን መናፍስት የተሰቃዩትን እያመጡ ብዙ ሰዎች ይሰበሰቡ ነበር፣ ሁሉም ይፈወሱ ነበር" (የሐዋ 5:16)።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እንደተፈወሱ የተገለጹትን የበሽታዎች፣ የደዌዎችና የአካል ስንኩልነት ዝርዝር በጥንቃቄ ተመልከት።

1. እንካሳነት - (አካል ስንኩልነት) የሐዋ 3:2

2. ድውይነት - (ደዌ) የሐዋ 5:16

3. ሽባዎች፣ አንካሶች - (አካል ጎደሎ) የሐዋ 8:7

4. እውርነት - (ሕመም ወይም አካል ጎዶሎነት) የሐዋ 9:17-18

5. ሽባነት - የሐዋ 9:33

6. የእግር መስለል (አካል ጎደሎነት) - የሐዋ 14:8-10

7. ንዳድ - (ሕመም)፣ ተቅማጥ - (ደዌ) የሐዋ 28:8

ያለ ምንም ማወላወል በፈውስ ስጦታዎች አማካይነት ሊፈወስ የማይችል በሽታ፣ ደዌና አካል ስንኩልነት የለም ሚለት እንችላለን።

እዚህ ላይ "የፈውስ ስጦታዎች" ስለሚለው ሰብራራት ጠቃሚ ይሆናል። ይህ ስጦታ በ1ቆሮ 12 ውስጥ ሦስት ጊዜ 9፣28፣ 30 ላይ ተጠቅሷል።

በተጠቀሱበት ስፍራዎች ሁሉ በብዙ ቁጥር ነው የተጠቀሱት። ከዘጠኙ የጸጋ ስጦታዎች ይህ ሁኔታ የሚታየው በፈውስ ስጦታ ብቻ ነው። ሌሎቹ ሁሉ "ስጦታ" በሚለው በነጠላ ቁጥር ብቻ ነው የተጠቀሱት። በዚህ በኩል በሌሎቹና በነዚህ ስጦታዎች መካከል ሰምን ልዩነት እንደተደረገ እርግጠኛ ባንሆንም የፈውስ ስጦታዎች ለማንኛውም የፈውስ ሩጫነት በቂ እንደሚሆኑ እርግጠኛ መሆን እንችላለን።

ይህ "ስጦታዎች" የሚለው ቃል ምናልባት የሚያመለክተው አንዳንድ አማኞች የተወለኑ በሽታዎችን፣ ደዌዎችንና አካለ ስንኩልነትን በመፈወስ በኩል ሊጠቀምበቸው እንደሚችል ሊሆን ይዘናል። ለምሳሌ በሐዋ 8 ላይ ፊልጶስ ሽባዎችንና አንካሶችን በመፈወስ በኩል መንፈስ ቅዱስ ተጠቅሞበት ነበር። ባለፉት ቅርብ ዘመናት ደግሞ በፈውስ አገልግሎት እግዚአብሔር በድንቅ ሁኔታ የተጠቀመባቸው ስሚዝ ዊግልስወርዝ የተባሉ አገልጋይ ነበሩ። የውስጥ ደዌዎችን በመፈወስ በኩል እግዚአብሔር ተጠቅሞባቸዋል። እዚህ ላይ "አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል" የሚለውን ልናስታውስ ይገባናል (1ቆሮ 12:11)።

የፈውስ ስጦታዎች የሚሠሩት እንዴት ነው?

ለዚህ ምንም የተወሰነ ድንበር ወይም ሥርዓት እንደሌለ ልናውቅ ይገባናል። ይህንንም የሚያመለክተን በአዲስ ኪዳን የተጠቀሱትን ዋና ዋና የፈውስ ሁኔታዎች ስናጠና ነው። በዚያን ጊዜ ፈውስ የተፈጸመው ፦

1. በመዳሰስና ቃል በመናገር (ማቴ 8:3)

2. ቃል በመናገር (ማቴ 8:5-13) (ተፈዋሹ ተገኝቶ ቃሉን አልሰማም)

3. በመዳሰስ (ማቴ 8:15)

4. በመዳሰስና ቃል በመናገር (ማቴ 9:29)

5. በማዘዝ (ማቴ 12:13)

6. ጭቃ በመቀባትና ቃልን በመናገር (ዮሐ 9:6)

7. በማዘዝና እጅ በማንሣት (የሐዋ 3:6-9)

8. ቃልን በመናገርና በማዘዝ (የሐዋ 9:34)

የተሰመደው የፈውስ አሠራር ቃልን በመናገር እንደነበረ ልብ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በእጅ መዳሰስ፣ ማንሣት ወይም ሌላ ድርጊት፣ የሚጸለይለትን ሰው እምነት ሊረዳ ይችላል። ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር በሚነገር ቃል አማካይነት የስራ ይመስላል። የቀድሞዋ ቤተ

ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎታቸውን ያከናወኑት በሚነገር ቃል አማካኝነት ነበር። ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር ለታመሙ ሰዎች ፈውስን ለማስገኘት በተመሳሳይ መንገድ ይጠቀማል ብሎ ማሰብ ተገቢ ይመስላል። በመጨረሻ የምንደርስበት ግንዛቤ የፈውስ ስጦታ እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ በአማኞች ውስጥ እንደሚገለጽ ነው።

አማኙ ሊያገለግልበት የሚችለው የፈውስ ስጦታ እንዳለው እንዴት ማወቅ ይችላል?

እንደገና እንደሌሎቹ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ ስጦታው የሚገለጽበት ሰው በራሱ መንፈስ ጥልቅ የሆነ ስሜት ይሰማዋል። በብሉይ ኪዳን የተገለጸው የሳምሶን ልምምድ ለዚህ ምስክር ነው። "የእግዚአብሔርም መንፈስ በኃይል ወረደበት፣ ክንዱም የታሰረበት ገመድ በእሳት እንደተበላ እንደ ተልባ እግር ፈትል ሆነ" (መሳ 15:14)። ሳምሶንን ለፈውስ አገልግሎት መንፈስ ቅዱስ አልተጠቀመበትም። ሆኖም ድንቅ ሥራዎችን ለመሥራት እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል። ከዚህ ከሳምሶን ልምምድ በመነሣት በእርሱ ሕይወት የተጠቀመው መንፈስ ቅዱስ ራሱን በእኛ ሊገልጽ በፈለገ ጊዜ ምን ዓይነት ልምምድ ሊኖረን እንደሚችል መገመት እንችላለን።

ማንም አማኝ የፈውስ ስጦታን እንደራሱ ሊያዝበት አይችልም። መንፈስ ቅዱስ እንደፈቀደ ብቻ ሊጠቀምበት ይችላል። ከሌሎቹ ይልቅ በአንዳንዶች ዘንድ ስጦታው የበለጠ ይሠራል። ይሁን እንጂ ይህ ሊሆን የቻለው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በእምነት መራመድን ስለተማሩ ነው። ይህ ደግሞ ታላቅ ምስጢር ነው።

(3). ከሚከተሉት መግለጫዎች አውነት ከሆኑት አንጻር 'እ' ብለህ ጻፍ።

___ሀ. የፈውስ ስጦታ የሚገለጸው በቤተ ክርስቲያን መሪዎች አማካይነት ብቻ ነው።
___ለ. የፈውስ ስጦታዎች" የሚለው በትክክል አሥራ ሁለት የተለያዩ የፈውስ ስጦታዎች መኖራቸውን የሚያመለክት ነው።
___ሐ. "የፈውስ ስጦታዎች" የሚለው የተመረጡ አማኞችን መንፈስ ቅዱስ በተለያዩ ብዙ መንገዶች እንደሚጠቀምባቸው የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።
___መ. የፈውስ ስጦታ ብዙውን ጊዜ የሚሠራው የታመመውን በእጅ በማንሣት ነው።
___ሠ. ማንኛውም ዓይነት ሕመም፣ ደዌና አካለ ስንኩልነት በፈውስ ስጦታ አማካይነት ሊፈወስ ይችላል ብለን መጠበቅ እንችላለን።

የፈውስ ስጦታ የተሰጠበት ዓላማ

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ አጠቃላይ ዓላማ የክርስቶስን አካል ማነፅ ነው። ይህንኑ ዓላማ አንዳንዶች

በአንድ ዓይነት መንገድ ሲያከናውኑ ሌሎች ደግሞ በሌላ ዓይነት መንገድ ይፈጽሙታል። የፈውስ ስጦታዎች ያሏቸው የቤተ ክርስቲያን አባላት ጤናማና በአካላዊ አቋማቸው ሙሉ እንዲሆኑ በማድረግ ዓላማውን ይፈጽማሉ። መላው የአማኞች ጉባረት ግለሰብ አባላት በሰውነታቸው ጤናማ በመሆናቸው ምክንያት ጉልበት ያገኛሉ።

ብዙውን ጊዜ የፈውስ ስጦታ በወንጌል ስባኪ አገልግሎት ይከሰታል። የፈውስ ስጦታም ሰዎች የወንጌሉን ቃል እንዲሰሙ ይስባቸዋል። የጥንቶቹ አማኞች፣ "ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው" ብለው ጸልየው ነበር (የሐዋ 4:30)። ከዚያም እግዚአብሔር ሲመልስ፣ "..... ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር .... የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨመሩለት ነበር..." (የሐዋ 5:12፣14)። ስለሆነም የፈውስ ስጦታ ዓላማ የነርስቶስን አካል፥ አካላዊ ፍላጎት የሚያሟላና ሰዎች ወደ ጌታ ኢየሱስ እንዲመጡ መርዳት እንደሆነ ተመልክተናል።

ተግባሬት ማድረግ

ዓላማ 3 ተዓምራት የማድረግ ስጦታን ተግባርና ዓላማ መግለጽ።

ዓላማ 4 በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ተዓምራቶች የትኞቹ እንደሆኑና ተዓምራት መሆናቸው እንዴት እንደ ሚታወቅ መግለጽ።

የስጦታው ትርጓሜ

"ለአንዱም ተዓምራትን ማድረግ ..ይሰጠዋል" (1ቆሮ 12:10)። በግሪክ ቋንቋ "ተዓምራት" የሚለው ቃል "ዱናሚስ" ይሰዋል። በእንግሊዝኛ "ዳይናማይት" የሚለው ቃል ከዚህ የተገኘ ነው። ዳይናማይት ወይም በአማርኛ ድማሚት የሚፈነዳ ነገር ሲሆን፥ ታላቅም ኃይል አለው። ታላላቅ አለቶችን ለማንቀሳቀስ አሮጌ ሕንጻዎችን ለማፈራረስና ለሌሎች ብዙ ዓላማዎች ደማሚትን እንጠቀምበታለን።

ይኸው ቃል "ተዓምራት ማድረግ" በሚለው ሐረግ ውስጥ ሲገባ "በሌላ መንገድ ሊከናወኑ የማይችሉ ተግባሮችን ለመፈጸም የሚያስችል ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል" የሚል ትርጉም ይይዛል። ሃዋርድ ካርተር የተባሉት ሰው ሲናገሩ "ተዓምራት የማድረግ ስጦታ ..የተፈጥሮ ሕግጋትን በመለወጥ፣ በመነደብና ወይም በሌላ ሁኔታ በመቆጣጠር ልዕለ - ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔር ኃይል መግለጫ ነው።" ብለዋል።

(4) በሐዋርያት ሥራ 13 የተፈጸመው ተዓምራት ምን ነበር?

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፈፀሙ አንዳንድ ተዓምራቶችን በመመልከት ስለዚህ ስጦታ ያለንን መረዳት ማሳደግ እንችላለን።

በብሉይ ኪዳን የተፈጸሙ ተዓምራቶች

በብሉይ ኪዳን ብዙ ተዓምራቶች ተፈጽመዋል። እዚህ ላይ ጥቂቶቹን ብቻ እንዘረዝራለን። እያንዳንዱን ታሪክ በጥንቃቄ አንብብ።

1. ሙሴ ከዓለት ውኃ አፈለቀ (ዘጸአት 17:1-6)

2. እስራኤሎች በደረቅ ምድር ተሻግረው ዮርዳኖስን አቋረጡ (ኢያሱ 3:15-17)

3. ኢያሱ ፀሐይ እንድትቆም አደረገ (ኢያሱ 10: 12-13)

4. ኤልያስ ከሰማይ እሳት እንዲወርድ አደረገ (1ነገ 18:37-38)

5. ኤልሳ የመጥረቢያ ምላር እንዲንሳፈፍ አደረገ (2ነገ 6:1-7)

በጌታ ኢየሱስ የተፈጸሙ ተዓምራቶች

1. ኢየሱስ ውኃን ወደ ወይን ጠጅ ለወጠ። (ዮሐ 2:1-11)

2. ኢየሱስ የሚናወጠውን ማዕበል ጸጥ አደረገ (ማቴ 8:23-26)

3. ኢየሱስና ጴጥሮስ በውኃ ላይ ተራመዱ (ማቴ 14:22-31)

4. ኢየሱስ በአንድ ልጅ ምሳ ብዙ ሰዎች መገበ (ዮሐ 6:5-14)

5. ኢየሱስ የሞተ ሰው አስነሣ (ዮሐ 11: 1-44)

በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን የተፈጸሙ ተዓምራቶች

በብሉይ ኪዳን ለተፈጸሙት ተዓምራቶች ምናልባት መግለጫ የሚሆነው አብዛኛቹ ተዓምራት በነብያት መፈጸማቸው ነው። ጌታ ኢየሱስ ለፈጸማቸውም ተዓምራቶች መግለጫው በእግዚአብሔር ልጅ መደረጋቸው ሊሆን ይችላል። በሐዋርያት ሥራ ለተፈጸሙት ተዓምራት ግን ሌላ መግለጫ ሊኖራቸው ይገባል። በሐዋርያት ሥራ የተጠቀሱት ተዓምራት የተከናወኑት በጣም ተራ በሆኑ ሰዎች ማለትም በዓሣ አጥማጆች፣ ቀራጮችና በመሳሰሉት ሰዎች ነበር። ሆኖም እነዚህ ሰዎች እንዴት ተዓምራት ሊያደርጉ ቻሉ?

ይህንን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተገለጹትን አያሌ ተዓምራት መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል። የትኛው ድርጊት ተዓምራት፣ የትኛው ደግሞ የፈውስ ስጦታ መሆኑን መናገር ቀላል አይሆንም። ነገር ግን ከእንዱ መንፈስ የሚፈሱ ስለሆነ ብዙም ልዩነት አያመጡም። "እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተዓምራት ያደርግ ነበር፥ ስለዚህም ከእካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር፥ ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር" (የሐዋ 19:11-12)። ዝርዝሮቹ እነሆ፦

1. ከወኅኒ ቤት ማምለጥ (የሐዋ 5:17-20)

2. የመታን መነሣት (የሐዋ 9:36-41)

3. ከወኅኒ ቤት ማምለጥ (የሐዋ 12:5-17)

4. የወንጌል ተቃዋሚ የሆነ ሰው መታወር (የሐዋ 13:6-11)

5. በእባብ ተነድፎ አለመጎዳት (የሐዋ 28:1-6)

ለእነዚህ ሁሉ ተዓምራት መፈጸም ምክንያት የሆነ አንድ ምስጢር አለ። እነዚህ እግዚአብሔር ተዓምራትን ለመፈጸም የተጠቀመባቸው ታላላቅ ሰዎች ስለነበሩ ወይም የራሳቸው የሆነ የተለየ ኃይል ያላቸው ሰዎች ስለነበሩ አይደለም። ሰዎች በትምህርት ቤት የሚያገኙት ችሎታ እንኳ አይደለም። ያንን በእርግጥ ያደረገው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር። የክርስቶስን እካል ታላቅ ፍላጎት መልስ ለመስጠት የተገለጠ የመንፈስ ቅዱስ "ድማሚት" ነበር። ብዙውን ጊዜ የሚገለጠው እንቅፋትን ለማስወገድና የወንጌል መሰናክሉት እንዲቀጥል ለማድረግ ነበር።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከተጠቀሱት ተዓምራት አንዱን ቀረብ ብለን በሐዋርያት ሥራ 9 ላይ የተጠቀሰውን ብንመለከት የዶርቃን ከሞት መነሣት ይነግረናል። ዶርቃ ከሞተች በኋላ ጴጥሮስ እንዲጸልይላት ተጠርቶ ነበር። ጴጥሮስ ራሱም፥ የሞተ ሰው ሊያስነሣ እንደማይችል፣ ሆኖም እግዚአብሔር እንደሚችል ያውቅ ነበር። ተዓምራትን ለማየት ከፈለገ ደግሞ መጸለይ እንዳለበት ያውቅ ነበር። ጸሎት መጸለይ የእግዚአብሔር ኃይል ማስተላለፊያ እንዲሆንና ተዓምራትም እንዲከናወን ያደርጋል። ጴጥሮስ ጸለየ፣ ተዓምራትም ተፈጸመ። መንፈስ ቅዱስ ጥልቅ በሆነ ሁኔታ በጴጥሮስ ልብ ውስጥ ይንቀሳቀስ ነበር። ለዶርቃ ተናገራት! እርሷም ስለሞተች ተጨናንኖ የነበረው ዐይኗ ተከፈተ፣ በጣምም ንቁ ሆና ተቀመጠች።

በሌላ ክፍለ ትምህርት "አምኒሽንት" ማለት ሁሉን እዋቂ ማለት እንደሆነ ተምረናል። እግዚአብሔር ሁሉን እዋቂ ነው። አሁን ደግሞ "አምኒፖተንት" የሚል አዲስ ቃል እንጨምራለን። "አምኒፖተንት" ማለትም "ሁሉን ቻይ" ማለት ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ተዓምራት በማድረግ ስጦታ አማካይነት መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ኃይል በአማኙ ውስጥ ይገልጻል። ያ ኃይል ደግሞ የማይቻለው እንዲቻል ያደርጋል።

(5). የሚከተሉትን መግለጫዎች እጠናቃቸው።

ሀ. የእግዚአብሔር ኃይል በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን በ_____. አማካይነት ተገልጿል።
ለ. ኢየሱስ የፈጸማቸው ተዓምራት በ_____ላይ የተመሠረቱ ናቸው፥ በማለት መግለጫ መስጠት ይቻላል።
ሐ. በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተገለጹት ተዓምራት ብቸኛ የሆነው መግለጫ___ _____ነው።
መ. ጴጥሮስ _____ መተላለፊያ እሸንዳ ነበር።
ሠ. የእግዚአብሔርን ኃይል የሚገልጸው ቃል _____የሚለው ነው።

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

ተዓምራት ለምን እስፈለገ? እንዳንዶች እንደሚሉት ተዓምራት ያስፈለገው ተዓምራት ማየት ስለሚፈልጉ ነው። ማየትም የሚፈልጉት ባልተለመዱ ክስተቶች ደስ ስለሚሰኙ ነው። ሌሎች ደግሞ ተዓምራትን የሚፈልጉት ለተለዩ በጣም ግላዊ ለሆኑ ምክንያቶች ነው። በአንድ ወቅት፥ በአንድ መንደር በነበሩ ሰዎች ዘንድ ጌታ ኢየሱስ ተቀባይነት አላገኘም ነበር። በዚያን ጊዜ ታዲያ ደቀ መዛሙርቱ ተበሳጩና እንዲህ ብለው ጠየቁ፦ "... አሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እንል ዘንድ ትወዳለህን? (ሉቃ 9:54)። ጌታ ኢየሱስ የሰጣቸውን ምላሽ እስኪ አስተውል . . . "ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆነላችሁ እታውቁም፥ የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም" (ሉቃ 9: 55-56)። በሌላ አጋጣር ኢየሱስ ያለው፦ "ለግላዊ ዓላማ ምንም ዓይነት ተዓምራት አይከናወንም።"

ሁሉን ቻይነት----> ተዓምራት----> አካል መታነፅ (ቤተክርስቲያን)

እንደሌሎቹ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ፥ ተዓምራት ማድረግም እንደ መሪ ዓላማ አለው። ይህም የክርስቶስን እካል ማነፅ ነው። ተዓምራት የማድረግ ስጦታ ይህንን ከሚያደርግበት መንገድ አንዱ ለወንጌል እንቅፋት የሚሆኑትን በማስወገድ ነው። አማኞች ለዚህ ምክንያት ተዓምራትን የሚፈልጉ ከሆነ አብዝተው ያያሉ።

በሐዋርያት ሥራ 5 ላይ ለወንጌል መስፋፋት እንቅፋት የሆኑት ተከታታይ የሆኑ የወኅኒ ቤት በሮች ነበሩ። ወንጌልን ስለ ሰበኩ ሐዋርያት ወኅኒ ቤት ተጥለው ነበር። በተፈጸመው ተዓምራት ምክንያት እንቅፋቱ ተወገደ፥ የወኅኒ ቤቱ በሮች ተከፈቱ፥ እነርሱም ወንጌል መስበካቸውን ቀጠሉ።

በሐዋ 13:6-11 ላይ ጳውሎስ አንድን አገረ ገዢ ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ፈልጎ እንደነበር ተገልጿል። ሆኖም እንቅፋት አጋጠመው። ባርየሱስ የተባለው ጠንቋይ አገረ ገዢው ወንጌልን እንዳይቀበል ለማድረግ ሞከረ። ባርየሱስን በማሳወር መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስን ተዓምራት እንዲያደርግ ተጠቀመበት። በዚያም መንገድ እንቅፋቱ ተወገደ።

(6). በሐዋ 12:1-5 ላይ ለወንጌል መስፋፋት እንቅፋት ሆኖ የታየው ምን ነበር?

ትንቢት

ዓላማ 5 የትንቢት ስጦታን ተግባርና ዓላማ መግለጽ።

የስጦታው ትርጓሜ

"ለእንዳንዱም ትንቢት መናገር ..... ይሰጠዋል"

በአንዳንድ መጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች መሠረት ትንቢት ማለት ስለ "ወደፊቱ መናገር" ወይም "መተንበይ" ማለት ነው። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ደግሞ ትንቢት ማለት "በጉባዔ ላይ ቃሉን መግለጥ" ወይም "ማብራራት"፥ ይህም ማለት መስበክ ወይም ማወጅ ነው ይላሉ። ስለ ትንቢት ምንነት እንደሚገባ የምንረዳው መተንበይ ማለትና ማወጅ ማለት ምን እንደሆነ ስንረዳ ነው።

ትንቢት መተንበይ ከተለመደው ዓይነት ስብከት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ሊቆጠር አይገባውም። እንደሌሎቹ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ የትንቢት ስጦታ ከተፈጥሮአዊው አሠራር በላይ ነው። ራልፍ ኤም ሪግስ የተባሉት አሜሪካዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ እንደሚሉት፦ ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በራሱ ቋንቋ መናገር ወይም ለመተንበይና የእግዚአብሔርን ቃል ለማወጅ መለኮታዊ ኃይል ማግኘት ነው ብለዋል።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

በክፍለ ትምህርት 3 ላይ ስለ አገልግሎት ስጦታ አጥንተናል። በዚያን ጊዜም ከስጦታዎቹ አንዱ "የትንቢት ስጦታ" እንደሆነ ተምረናል። የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ የእነዚህ ስጦታዎች ሰጪ እንደሆነ ተገልጿል። አሁን የምናጠናው ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ነው። በአሁኑ ክፍለ ትምህርታችን የትንቢት ስጦታን የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እንመለከታለን። "...ለእንዳንዱም ... ትንቢትን መናገር ይሰጠዋል" (1ቆሮ 12:8-10)።

በነብያትና በትንቢት ስጦታ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? የነብይነት ስጦታ ለክርስቶስ አካል የተሰጠ የመሉ ጊዜ የመሪነት ስጦታ

ነው። የትንቢት ስጦታ በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት የሚነገር ቃል ነው። የነብይነት ስጦታ ከክርስቶስ አካል ለጥቂቱ ብቻ የሚሰጥ ነው። የትንቢት ስጦታን በክርስቶስ አካል ብልቶች ወይም አባላት በሙሉ ሊለማመዱት ይችላሉ። "..... ሁላችሁ በእያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ" (1ቆሮ 14:31)። በነብይነት ስጦታና በትንቢት ስጦታ መካከል ያለው ልዩነት ይህ ነው። በነብይነት አገልግሎት የሚያገለግሉ ሁሉ ይተነብያሉ፣ ሆኖም የሚተነብዩ ሁሉ የነብይነት አገልግሎት የላቸውም።

ከአገልግሎቱ ባሕርይ የተነሣ ትንቢት በ1ቆሮ 12:8-11 ላይ ከተጠቀሱት ስጦታዎች ሁሉ ምናልባት እጅግ ታላቅ ሳይሆን አይቀርም። ሐዋርያው ጳውሎስ "መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ" ብሏል (1ቆሮ 14:1)።

ስለሆነም የትንቢት ስጦታ እጅግ አስፈላጊ ስጦታ እንደሆነ ነው የምንረዳው። በዚህም ምክንያት ልንሻው ይገባናል። ከዘጠኙ የጸጋ ስጦታዎች የክርስቶስን አካል በመገንባት ወይም በማነጽ በኩል እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ስላለው ልዩ አስፈላጊነት አለው። በተለየ መንገድ የክርስቶስ አካል እንዲነቃቃ የሚያደርገው ይህ ስጦታ ነው። በዚህ ስጦታ አማካይነት አማኞች ይታነጻሉ፣ ያልዳኑ ኃጢአተኞችም ወደ እግዚአብሔር ያዘነብላሉ። "ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን የማያምን ወይም ያልተማረ ሰው ቢገባ በሁሉ ይወቀሳል።" (1ቆሮ 14:24)

(7). እውነተኛ ከሆነው መግለጫ አንጻር ያለውን ፊደል ክበቡ።

ሀ. ማወጅ በምንልበት ጊዜ "ስለ ወደፊቱ መናገር ማለት ነው።"
ለ. የነብይነት ስጦታና የትንቢት ስጦታ ተመሳሳይ ነው።
ሐ. የክርስቶስ አካል ብልቶች ወይም አባላት በሙሉ "የነብይነት ስጦታ" ሊኖራቸው ይችላል።
መ. አማኞች የሆኑትንና ያልሆኑትን ሊረዳ የሚችል በመሆኑ የትንቢት ስጦታ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ስጦታ ነው።

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

1. የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ

የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ ታላቅ አገልግሎት ግልጽ ሆኖ የታየው በበዓለ ሃምሳ ቀን ነበር። በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደ፣ ወዲያውም በጴጥሮስ ስብከት የትንቢት ስጦታ ተገለጸ። የዚያን ጊዜ ጴጥሮስ የሰበከው ተራ ስብከት አልነበረም። ከአንድ ቀን በፊት ቢሆን ኖሮ ጴጥሮስ ያን የመሰለ ስብከት መስበክ አይችልም ነበር። የጴጥሮስ ስብከት ዋነኛ ክፍል በታላቅ ኃይልና በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ የተሞላ ነበር። ጴጥሮስ ከራሱ ያልሆኑትን ሃሳቦች ይናገር ነበር፣ እነዚያ ሃሳቦች የተገኙት ከመንፈስ ቅዱስ ነበር።

ትንቢት *መናገር* በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት የተለመደ ውጤት ነው። ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ስለነበረ *ትንቢት ተናገረ*። በሐዋርያት ሥራ 19 ላይ የተጠቀሱት የኤፌሶን ደቀ መዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ጊዜ በልዩ ልሳን ተናገሩ፣ ትንቢትም ተናገሩ (የሐዋ 19:6)።

እውነተኛ ትንቢት የሚነገረው በእግዚአብሔር ችሎታና ኃይል ነው። አማኞች *የመናገር* ችሎታ ይኖራቸው ይሆናል። ታላላቅ ስብከቶችንም መስበክ ይችሉ ይሆናል። ሆኖም ከመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በስተቀር በእርግጥ ማንም ትንቢት ሊናገር አይችልም (1ጴጥ 4:11)።

ትንቢት የሚናገር አማኝ የሚናገረው ለሰው ነው። "ትንቢት የሚናገር ግን .... ለሰው ይናገራል" ይላል (1ቆሮ 14:3)። ጥያቄው ግን ለሰዎች የሚናገረው ምንድን ነው? የሚል ነው። ምንድን ነው የሚያውጀው? የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል፥ ያውጃልም። ዳሩ ግን ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ይህንን አያደርጉምን? በእርግጥ ያደርጋሉ። ይሁን እንጂ በትንቢት ስጦታ *ምን እንደተነገረና ማን እንደተናገረው* ሳይሆን ዋናው ነገር *እንዴት እንደተነገረ* ነው። የተለመደ ዓይነት ስብከትና ማስተማር በአሳት ላይ ባልተጣደ ማሰሮ ቀዝቃዛ ምግብ እንደማስቀመጥ ነው። የትንቢት ስጦታ ታዲያ ከማሰሮው ሥር እንደሚነደው እሳት ነው።

በትንቢት ስጦታ አማካይነት *መንፈስ ቅዱስ* ተናጋሪው በራሱ ያላሰበበትን ወደ አእምሮው ሊያመጣ ይችላል። በሐዋርያት ሥራ 2 ላይ የተገለጸው የጴጥሮስ ስብከት በእርግጥ ይህንን የሚያመለክት ነበር።

(8). እንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና እነሳሽነት የእግዚአብሔርን ቃል ሊያውጅ ይህ ዓይነቱ ትንቢት _____ ተብሎ ይጠራል

2. *መተንበይ*

መተንበይ ማለት አንድ ነገር ከመፆሉ በፊት *መናገር* ነው። ቀደም ሲል እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እንደሚያውቅ ተምረናል። ይህም ማለት እግዚአብሔር ያለፈውንና የአሁኑን እንዲሁም የወደፊቱን ያውቃል ማለት ነው። ሰው በራሱ ኃይል ስለ ወደፊቱ ሊያውቅ አይችልም። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ብቻ ስለ ወደፊቱ እንዳንድ ነገሮችን ሊያውቅ ይችላል። በትንቢት ስጦታ አማካይነት *መንፈስ ቅዱስ* አማኙን ስለ ወደፊቱ አንድ ነገር እንዲናገር ሊያደርገው ይችላል።

የብሉይ ኪዳን ነብያት ብዙውን ጊዜ ስለ ወደፊቱ ተናግረዋል። ስለ ወደፊቱ *መናገር* የአገልግሎታቸውን በርከት ያለ ጊዜ የሚወስድ ነበር። ብዙውን ጊዜ ይህን የሚያደርጉት ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር *መመለስ* እንደ ሚያስፈልጋቸው ለመግለጽ ነው። ዮናስ ስለ ወደፊቱ ከተናገሩት ነብያት አንዱ ነበር። እርሱም "በሦስት ቀን ውስጥ ነነዌ ትገለበጣለች" ብሎ ተነበየ (ዮናስ 3:4)።

በክፉ *መንፈስ* የተያዙ ሰዎችም እንዳንድ ጊዜ ስለ ወደፊቱ ይተነብያሉ። እነዚህም ጠንቋዮች ወይም ምዋርተኞች ተብለው ይጠራሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ አንድ ጊዜ ይህን ከመሰሉ ሰዎች ጋር ያላለፈው ልምምድ ነበር። "ወደ ጸሎት ስፍራ ስንሄድ የምዋርተኝነት *መንፈስ* የነበረባት ለጌቶችዋም እየጠነቆለች ብዙ ትርፍ ታመጣ የነበረች አንዲት ገረድ አገኘችን" (የሐዋ 16:16)።

እግዚአብሔር ይህን የመሰለውን ስለ ወደፊቱ የመተንበይ አሠራር አጥብቆ ይቃወማል። ይህ መሳይ አሠራር ከሰይጣን ነው። አማኞች እንደመሆናችን መጠን ወደ እንደዚህ ዓይነቱ አሠራር መቅረብ አይገባንም። "ወንድ ልጁን፥ ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ፥ ምዋርተኛም፣ ሞራ ገላጭም፣ አስማተኛም፣ መተተኛም፣ በድግምት የሚጠነቁልም፣ መናፍስትንም የሚጠራ፣ ጠንቋይም፣ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው" (ዘዳ 18:9-12)።

ሰይጣን ምንጊዜም አጥፊ ነውና እምነትን ሊያጠፋ ይፈልጋል። አማኞችንም ሊያጠፋ ይከጅላል። የክርስቶስንም አካል ማጥፋት የእርሱ ፍላጎት ነው። ስለ ወደፊቱ እንዲናገሩ ሰዎችን ለማነሳሳት የሚያደርገው ጥረት ሁሉ ለጥፋት የታለመ ነው። "ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም" (ዮሐ 10፤10)።

የእግዚአብሔር *ሥራ* ምንጊዜም ለማዳን ነው። አንዳንድ ጊዜ በትንቢት ስጦታ አማካይነት *መንፈስ ቅዱስ* የክርስቶስን አካል ከመከራ ያድናታል። (የሐዋ 11:27-30 አንብብ) በሴላ ጊዜ በትንቢት ስጦታ አማካይነት የክርስቶስ አካል ሊመጣ ላሰው መከራ ይዘጋጃል (የሐዋ 20:23፤ 21:10-13)።

ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ያውቁ ዘንድ እንዲረዳቸው አማኞች በትንቢት ስጦታ ሰመጠቀም ይፈተኑ ይሆናል። ሆኖም ይህ የሚያዋጣ እይደለም። ስለልዩ ልሳን ስጦታ በምናጠናበት ጊዜ ስለዚህ በይበልጥ እንማራለን።

(9). ከሚከተሉት *መግለጫዎች* ሐሰት ከሆኑት አንጻር 'ሐ'፥ እውነት ከሆኑት ደግሞ 'እ' ብለህ ጻፍ

___ሀ. *መተንበይ* ማለት አንድ ነገር ከተፈጸመ በኋላ *መናገር* ነው።
___ለ. የብሉይ ኪዳን ነብያት ስለ ወደፊቱ ብዙውን ጊዜ ይናገሩ ነበር።
___ሐ. ምዋርተኞች አማኞችን በማም የሚረዱ ናቸው።
___መ. ሰይጣን ምንጊዜም ለማጥፋት ይፈልጋል፣ እግዚአብሔር ደግሞ ምንጊዜም ማዳን ይፈልጋል።

ስለ ትንቢት ስጦታ አጠቃቀም የተሰጠ መመሪያ

(1ቆሮ 14፡ 29-40)

1. ትንቢት የምንናገረው በእምነታችን መጠን መሆን አለበት (ሮሜ 12፡6 ተመልከት)። መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚሠራው በአማኙ ውስጥ ባለው የእምነት መጠን ነው። እምነት ሳይኖረን መተንበይ ከራሳችን ልብ አውጥተን መናገር ነው። ይህም ሁኔታ የአማኙን አብዝቶ መጸለይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅና በመንፈስ ቅዱስም መሞላት እጅግ አስፈላጊ ያደርገዋል።

2. የትንቢት መልእክት ሊገታና ሊፈተንም ይገባዋል (1ቆሮ 14:29)። እግዚአብሔር በአምልኮ ስብሰባዎች ውስጥ ሥርዓት እንዲኖር ይፈልጋል። እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ፦ ያለማቋረጥ ትንቢት በመናገር አትቀጥሉ፣ እዚያ ተቀምጠው ያሉትን መፈተን እንዲችሉ ጊዜ ስጡ ይላል። መፈተን ማለት "በትክክል መመዘን ማለት ነው።"

ሊሉች አማኞች በትንቢት የሚነገረውን ቃል በጥንቃቄ አገናዝበው ሊፈትኑ ይገባል። ለምንድን ነው ይህን የሚያደርጉት? ምክንያቱም ትንቢት የሚናገሩት ሰዎች ናቸው። ከመንፈስ ቅዱስ የሆነውን ይናገራሉ፣ ሆኖም ከራሳቸው መንፈስ እንዲያውም ከዕርኩስ መንፈስ የሆነውንም የሚናገሩም ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ተቀምጠው የሚያዳምጡት በእግዚአብሔር ቃል ረዳትነት የተነገረው ቃል ከቃሉ ጋር የሚስማማ እንደሆነ ሊፈትኑ ይገባል። ከቃሉ ጋር የማይስማማ ከሆነ የትንቢቱን ቃል ሊጥሉት ይገባል። ለምሳሌ፦ ምዕመናኑ የኢየሱስን ስም እንዲረግሙ የሚናገር የትንቢት ቃል ከተሳለፈ ያ የትንቢት ቃል ሊጣል ይገባል።

3. ሁሉም ትንቢት ሊናገሩ ይችላሉ (1ቆሮ 14፡ 5፣24፣31)። ይህ ቃል ማንኛውም አማኝ ትንቢት እንዲናገር መንፈስ ቅዱስ ሊጠቀምበት እንደሚችል ያሳስበናል። ይህ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቻ የተሰጠ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ለተሞሉ አማኞች ሁሉ ነው።

4. የትንቢት ቃል የተሰጣቸው ወዲያውኑ መናገር አለባቸው ማለት አይደለም። የትንቢት ቃል የተሰጠው ሰው መቼ የትንቢቱን ቃል መናገር እንዳለበትና እንደሌለበት ያወስናል። የራሱን ፈቃድ መቆጣጠር በሚችልበት በአንድ ዓይነት የምትሐት ኃይል የተያዘ ሰው አይደለም (1ቆሮ 14:32-33 አንብብ)።

5. በትንቢት ስጦታ መንፈስ ቅዱስ የሚጠቀምባቸው ምክርን ለመቀበልና ለመስተካከል ፈቃደኞች ሊሆኑ ይገባቸዋል (1ቆሮ 14:37)።

(10). ትክክለኛ በሆነው መግለጫ አንጻር ያለውን ፊደል ክበበው።

ሀ. አንድ ሰው አንድ ጊዜ ትንቢት ከተናገረ ተጨማሪ የትንቢት ቃል ለመናገር ራሱን ማዘጋጀት አያስፈልገውም።
ለ. የትንቢት ቃል ያዳመጡ ሰዎች ቃሉ ከመንፈስ ቅዱስ መጥቶ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ሊጠይቁ አይገባቸውም።
ሐ. የትንቢት ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቻ ነው።
መ. የሚተነብየው አማኝ መቼ መተንበይ እንዳለበት የመወሰን መብት የለውም።

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የተሰጡት የክርስቶስን አካል ለማነፅ ነው። እያንዳንዱ ስጦታ አካሉን የሚያንፅበት የራሱ የሆነ የተለየ መንገድ አለው። ሐዋርያው ጳውሎስ የትንቢት ስጦታ ይህንን እንዴት እንደሚያከናውን ይነግረናል። "ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነፅና ለመምከር ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል" ይላል (1ቆሮ 14:3)። ትንቢት የሚናገር አማኝ ሌሎች አማኞችን ለማበረታታትና ለማፅናናት ይናገራል።ሌሎች በሚበረታቱበትና በሚፅናኑበት ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ይታነጻሉ። እነዚህም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሲታነፁ መላው የክርስቶስን አካል ይረዳል።

(11). ትንቢት የሚናገር አካሉን ይገነባል ስንል አካሉ _____ማለታችን ነው።

የመከራ ፈተና

የምርጫ ፈተና

ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጥ፡ ከዚያም ከትክክለኛው መልስ አንጻር ያለውን ፊደል ክበበው።

1. የፈውስ ስጦታዎች በዋናነት የሚያገለግሉት የሰውን

ሀ. መንፈሳዊ ፍላጎቶች ነው።
ለ. አካላዊ ፍላጎቶችን ነው።
ሐ. ቁሳዊ ፍላጎቶችን ነው።

2. መንፈስ ቅዱስ በፈውስ ስጦታ ሊጠቀምበህ እንደሚፈልግ ማወቅ የምትችለው

ሀ. ፈውስ የሚያስፈልገውን ሰው ስትመለከት ነው።
ለ. አንድ ሰው የፈውስ ስጦታ አለህ ብሎ ሲነግርህ ነው።
ሐ. ፈውስ የሚያስፈልገውን አንድን ሰው እንድታገለግል የመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት በውስጥህ ሲሰማህ ነው።

3. ተዓምራት የማድረግ ስጦታ ነው።

ሀ. በልዕለ - ተፈጥሮአዊ ኃይል የሚከናወን
ለ. ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ሊሆን የማይችል
ሐ. በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የምንማረው

4. ትንቢት _____ ነው።

ሀ. ማንኛውም ዓይነት ስብከት
ለ. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መናገር
ሐ. የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅና የሰዎችን የወደፊት ዕድል መናገር

5. የትንቢት ስጦታ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት

ሀ. በማንኛውም አማኝ ውስጥ ሊገለጥ ስለሚችል ነው።
ለ. በስጦታው አማካይነት ስለ ወደፊቱ መተንበይ ስለሚቻል ነው።
ሐ. የእግዚአብሔር መልዕክት የሚታወጅበት በመሆኑ ነው።

6. ማወጅ ማለት _____ ነው።
   ሀ. አንድ ነገር ከመሆኑ በፊት መናገር
   ለ. የእግዚአብሔርን መልዕክት መናገር
   ሐ. ስለ ወደፊቱ ከመተንበይ ጋር የሚመሳሰል

አጭር መልስ፡- ተገቢውን ቃል በክፍቱ ቦታ በመሙላት መግለጫዎቹን አጠናቃቸው።

7. በዚህ ክፍለ ትምህርት ያጠናናቸው ሦስቱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች፡-
   _____

8. የፈውስ ስጦታ ዋና ዓላማ_____ነው።

9. "አምኒፖተንት" ማለት _____ ማለት ነው።

10. ተዓምራት የማድረግ ስጦታ የክርስቶስን አካል በማነጽ የሚረዳው _____ በማስወገድ ነው።

11. ሰይጣን ስለ ወደፊቱ ሰዎች እንዲተነብዩ በሚያደርግበት ጊዜ ዓላማው አብዛኛውን ጊዜ_____ነው።

12. የትንቢት ስጦታ ዓላማ_____ና _____የክርስቶስን አካል ማነፅ ነው።

የጥናት ማጠናከሪያ መልሶች

1. ሀ. መንፈስ ቅዱስ በተሞሱ አማኞች
   ለ. ሙሉ ወይም ጤናማ ማድረግ ነው።

7. ሀ. ሐሰት ለ. ሐሰት
   ለ. ሐሰት መ. እውነት

2. ሁሉም መልሶች እውነት ናቸው።

8. ታሉን ማወጅ

3. ሀ. ሐ ሐ. እ ሠ. እ
   ለ. ሐ መ. ሐ

9. ሀ. ሐ ሐ. ሐ
   ለ. እ መ. እ

4. የጠንቋዩ መታወር

10. አንዱም መልስ ትክክል አይደሰም።

5. ሀ. ተዓምራቶች
   ለ. እግዚአብሔር ልጅነት
   ሐ. መንፈስ ቅዱስ
   መ. የእግዚአብሔር ኃይል
   ሠ. አምኒፖተንት

11. ይታነጻል

6. የወንጌል ሰባኪ የነበረው ጴጥሮስ ወነኒ ቤት መጣሉ ነበር።

9 መናፍስትን መለየት፣ ልዩ ልሳን፣ ልዩ ልሳንን የመተርጎም ስጦታ

ትምህርት

እስካሁን ከዘጠኙ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ስለ ስድስቱ አጥንተናል። ጥናታችንን እየቀጠልን ስንሄድ የክርስቶስን አካል መገንባት ይቻል ዘንድ መንፈስ ቅዱስ በአስደናቂ ሁኔታ እንዴት የሚያስፈልገውን እንደሚያቀርብ ተመልክተናል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለክርስቶስ አካል የሚገለጸው በአጠቃላይ በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ አማኞች እንደሆነ ተምረናል።

በዚህ የመጨረሻው ክፍለ ትምህርት በ1ቆሮ 12:8-10 ከተጠቀሱት ስጦታዎች ስለ ሦስቱ እንማራለን። በዛሬው ዘመን በዓለም ውስጥ በጣም የተለመደ በመሆኑ ለልዩ ልሳን ስጦታ የተለየ ትኩረት እንሰጣለን።

እነዚህ ሁሉ ስጦታዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት መሆኑን ተመልክተሃል። እስካሁን በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቅህ ከሆነ ዛሬ ልትጠመቅ ትችላለህ። ልብህን ከፍተህ በእምነት እርሱን ማምለክ ጀምር፣ ለእርሱም ፈቃድ ራስህን አሳልፈህ ስጥ። ውስጣዊ በሆነ ሕይወትህ ሲነካህ ይሰማሃል። ሙሉ በሙሉ ሊቆጣጠርህ ሲጀምር በአዲስ ቋንቋ መናገር ትቀጥላለህ። የዚያን ጊዜም በሙላት ወደ አንተ እንደመጣ ታውቃለህ። ያም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወትህ ጅማሬ ይሆናል። በመንፈስ ቅዱስ በተሞላው ሕይወትህ ጸንተህ በምትኖርበት ጊዜ እርሱ እንደፈቀደ ስጦታዎቹን በአንተ ውስጥ ይገልጻል።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- መናፍስትን የመለየት ስጦታ
- በልዩ ልሳን የመናገር ስጦታ
- ልዩ ልሳንን የመተርጎም ስጦታ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

- በዚህ ክፍለ ትምህርት የቀረቡትን ሦስት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መዘርዘር፣ የእያንዳንዱን ስጦታ ተግባርና ዓላማ መግለጽ
- ከእነዚህ ስጦታዎች አንዱ ወይም ከዚያም በላይ የሆኑት በአንተ ሕይወት ውስጥ እንዴት ሊገለጹ እንደሚችሉ መረዳት
- ከእነዚህ ስጦታዎች ሁለቱ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንዴት እንደተገለጹ ማብራራት

የትምህርቱ መመሪያዎች

1. 1ቆሮ 14:1-28 አንብብ

2. 1ቆሮ 14:2-3 መሠረት በማድረግ ሦስቱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና ምንነታቸውን የሚያሳይ ሰንጠረዥ በማስታወሻ ደብተርህ አዘጋጅ።

3. በመጨረሻ የሙከራ ፈተናዎች አጠናቃቸው።

4. 1ቆሮ 13 በታልህ ማጥናትህን አጠናቅ።

የትምህርቱ ዝርዝር

መለኮታዊ ስጦታዎች

ዓላማ 1 መናፍስትን የመለየት ስጦታ ዓላማና ተግባር መግለጽ።

የስጦታው ትርጓሜ

"ለአንዱም መናፍስትን መለየት ይሰጠዋል" (1ቆሮ 12:10)። መለየት ማለት "በውጪ ከሚታየው አልፎ በውስጥ ያለውን ማየት ነው።" *መለየት* የሚለው ቃል በታወቀው ነገር ላይ በመመሥረት መዳኘት ወይም መፈረጅ የሚለውን ሃሳብም ያዘለ ነው። *መንፈስ* የሚለው ቃል "እስትንፋስ ማለት ነው" ይሁን እንጂ ለአማኞች መንፈስ ከእስትንፋስም የላቀ ነው። ትክክለኛው ትርጉሙ "መንፈሳዊ አካል ነው።" እዚህ ላይ ከተጠቀምንበት አንጻር ከሦስት መናፍስት አንደኛውን የሚገልጽ ነው። የሰው መንፈስ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ወይም ዕርኩሳን መናፍስት። የሰው መንፈስ እጅግ አስፈላጊ የሆነው የሰው ክፍል ነው። ሰው በመንፈሱ መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን ያውቃል። የእግዚአብሔር መንፈስ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው። ዕርኩሳን መናፍስት ደግሞ በክፋት ዓለም ውስጥ የሚገኙ የሰይጣን አገልጋዮች ናቸው።

መናፍስትን የመለየት ስጦታ፣ እንግዲህ አንድ መንፈስ ራሱን በገለጸ ጊዜ ማናቸውም ሰው ከሚመለከተው ባሻገር ለመመልከት በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ የተለየ ችሎታ ነው። አንድ ሰው በየትኛው መንፈስ አማካይነት እንደሚናገር ወይም እንደሚያገለግል የማወቅ ችሎታ ነው።

(1). በሰዎች ውስጥ ራሳቸውን ሊገልጹ የሚችሉ ሦስት ዓይነት መንፈሶች _____፣ _____ና _____ናቸው።

(2). መናፍስት በመለየት ስጦታ አማካይነት አማኝ _____ይችላል።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

ሰይጣን ታላቅ አስመሳይ ነው። ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገውን አሰመስሎ ለማድረግ ይሞክራል ማለት ነው። ሰይጣን ራሱን በሚገልጥበት ጊዜ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ እንደተገለጸ እንዲያምኑ ለማድረግ ይጥራል። ይህ ችግር ሊያመጣ ይችላል፣ ምክንያቱም አማኞች ሊታለሉ ይችላሉ። ከዚህም በስተቀር ሰዎች ከራሳቸውም መንፈስ አውጥተው ሊናገሩ ይችላሉ። ሲናገሩም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሚናገሩ ሊያስመስሉ ይችላሉ። ይህም ደግሞ በክርስቶስ አካል ላይ ችግር ሊያስከትል ይችላል።

የአካሉ ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ለአካሉ የሚያስፈልገውን ሁሉ ያቀርባል። ጌታ ለአካሉ ከሚያደርጋቸው መካከል አካሉን ከዕርኩሳት መናፍስት ጥቃት መከላከልና መናፍስትን በመለየት ስጦታ አማካይነት መንፈስ ቅዱስ በአርግጥ የሚጠቀምባቸውን አማኞች ከክፉው መጠበቅ ይገኙበታል። አንዳንድ ጊዜ በአማኙ አማካይነት መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ተግሣፅ ሊያመጣ ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሌሎች አማኞች ይህ የተነገረው ከዕርኩስ መንፈስ ነው፣ ወይም የተናገረው ሰው ከራሱ አውጥቶ ነው የተናገረው ለማለት ይፈተኑ ይሆናል። ይሁን እንጂ መናፍስትን የመለየት ስጦታ የተገለጸው መንፈስ ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆነ የክርስቶስ አካል እንዲያውቅ ያስችለዋል።

የአንዳንድ ዕርኩስ መናፍስት አሠራር መናፍስትን የመለየት ስጦታም ባይኖር ሊታወቅ ይችላል። ይህንን በሚመለከት ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች መመሪያ ሰጥቶ ነበር። "ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር ኢየሱስ የተረገመ ነው የሚል እንደሌለ፣ በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ" (1ቆሮ 12:3)። ጳውሎስ ምን ማለቱ ነበር? የተናገረው በመንፈስ ስለሚናገሩ ሰዎች ነበር። አንድ ሰው በመንፈስ ምሪት ተናገርሁ ብሎ "ኢየሱስን የተረገመ ነው" ካለ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አልተናገርም ማለቱ ነው። በተጨማሪ በዕርኩስ መንፈስ ግፊት የሚናገር ማንም ሰው፡- "ኢየሱስ ጌታ ነው" ለማለት አይችልም ማለቱ ነው።

አሁን ደግሞ መናፍስትን የመለየት ስጦታ በጌታ ኢየሱስ ሕይወትና በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይሠራ እንደነበረ መመልከት ጠቃሚ ነው። መናፍስትን የመለየት ስጦታ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ችሎታ እንደሆነ ልናስተውል ይገባናል።

መናፍስትን መለየት በኢየሱስ አገልግሎት

ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ወይም የተሞላ ነበር። "እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና። አባት ልጁን ይወዳል፣ ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል" (ዮሐ 3:34-35)። ስለሆነም ጌታ ኢየሱስ መልካሙንና ክፉውንም መንፈስ መለየት ይችል ነበር።

1. በናትናኤል ውስጥ የነበረውን *መልካም መንፈስ* ለይቶ አወቀ። ከናትናኤል ጋር ገና ከመነጋገሩ በፊት በውስጡ ምን ዓይነት መንፈስ እንደነበረ አወቀ። ፊልጶስ ናትናኤልን ወደ ኢየሱስ ባመጣው ጊዜ፣ ጌታ ኢየሱስ "ተንኮል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው አነሆ" በማለት ተናገረ (ዮሐ 1: 47)።

2. በያዕቆብና በዮሐንስ የነበረውን *ትክክለኛ ያልሆነ መንፈስ* አወቀ። እነዚህ ወንድማማቾች ኢየሱስን ሊቀበሉት ያልፈለጉትን አሳት ከሰማይ ወርዶ እንዲያጠፋቸው ፈልገው ነበር። ኢየሱስ ግን "ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆነላችሁ አታውቁም" አላቸው (ሉቃ 9:55)።

3. ብዙውን ጊዜ *ዕርኩሳን መናፍስትን* ለይቶ ያውቃቸው ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ለአሥራ ስምንት ዓመታት ሽባ ሆና የኖረች ሴት ተመለከተ። የሰዲቱ ችግር የተፈጠረው በዕርኩሳን መናፍስት እንደሆነ አወቀ። ይህ መንፈስ አይናገርም፣ ያሁን እንጂ ምስኪኗን ሴት አስሯት ነበር። "አንቺ ሴት ከድካምሽ ተፈትተሻል" አላት (ሉቃ 13:12)። በዚያን ወቅት ደህና ነበረች፣ ፈውስም አያስፈልጋትም ነበር። የሚያስፈልጋት ከዕርኩስ መንፈስ ነፃ መሆን ብቻ ነበር። መናፍስትን የመለየት ስጦታ ለሕመምተኞችና ለአካለ ስንኩላን ከመጸለይ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ላላቸው እጅግ ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል እንማራለን።

ስጦታው በቀደሞዋ ቤተ ክርስቲያን

1. በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ጴጥሮስ በሐናንያና በሰጲራ ውስጥ የነበረውን የሐሰት መንፈስ አወቀ። በመንፈስ ቅዱስ ላይም እንደዋሹ አወቀ (የሐዋ 5:3)። ሰዎች በዕርኩስ መንፈስ እንዲያዙ ለማድረግ ሰይጣን ካልቻለ በተሳሳተ ወይም በሚያሳስት መንፈስ እንዲያዙ ለማድረግ ይሞክራል።

2. በድጋሚ ጴጥሮስ በስምዖን (ጠንቋዩ) ውስጥ የነበረውን የሐሰት መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት አወቀ (የሐዋ 8:23)። ሆኖም ይህን ያደረገው መናፍስትን በመለየት ስጦታ አማካይነት ነበር ወይስ በእውቀት ቃል አማካይነት? ዳሩ ማን በእርግጠኛነት መናገር ይችላል? ምናልባት ሁለቱም ስጦታ ሊሆን ይችላል። ቂይም ብለን እንደተመለከትነው እነዚህ ስጦታዎች ሁሉ የሚፈልቁት ከመንፈስ ቅዱስ ነው። ብዙውን ጊዜም ይደጋገፋሉ። የተሰጠበትን ዓላማ ያዘል ስጦታዎቹ ራሳቸው በዚያ መጠን አስፈላጊ አያደሉም። አስፈላጊነታቸው የክርስቶስን አካል እስካነጹ ድረስ ነው።

3. መናፍስትን በመለየት ስጦታ አማካይነት ሐዋርያው ጳውሎስ በአንዲት ገረድ ውስጥ የነበረውን ዕርኩስ መንፈስ ለይቶ አወቀ። አንድ ማንኛውም አማኝ ተፈጥሮአዊውን የማወቅ ችሎታውን ተጠቅሞ ገረዲቱ የእግዚአብሔር ባሪያ ናት ብሎ ሊያስብ ይችል ነበር። የተናገረችው ቃል «የመዳንን መንገድ የሚነግሩአችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው» የሚል ነበር (የሐዋ 16:17)። ሲለሙት፣ ያ መልካም ይመስላል፣ ሆኖም

ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእርሷ ውስጥ የተናገረው ዕርኩስ መንፈስ እንደሆነ አወቀ። መንፈስ ቅዱስ ለጳውሎስ ተናግሮት ስለነበረ ጳውሎስ ሊያውቅ ቻለ። ስለሆነም ጳውሎስ ዕርኩስ መንፈሱን እንዲህ ሲል ገሰጸው፣ "ከእርሷ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዛለሁ" አለው (የሐዋ 16:18)። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው በዚያኑ ሰዓት ወጣ።

ጳውሎስ ዕርኩሱን መንፈስ ለይቶ ማወቅ ብቻ ሳይሆን እንዳስወጣውም ልንገነዘብ ይገባል። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለአማኝ የሚሰጠው ልዕለ - ተፈጥሮአዊ ኃይል ለእርሱ ዕርኩሱን መንፈስ ያስወጣ ዘንድ ችሎታን ሰጠው። የማያምኑ ሰዎች ይህ ኃይል የላቸውም (የሐዋ 19:11-17)።

ዕርኩሳን መናፍስት ሊያደርጉ ከሚሞክሩት ነገር አንዱ አማኞች የስህተት ትምህርት እንዲቀበሉ ማድረግ ነው። መናፍስትን የመለየት ስጦታ አማኙ ከመንፈስ ቅዱስ የሆነውን ትምህርትና ከዕርኩሳን መናፍስት የሆነውን ትምህርት መለየት እንዲችል ይረዳዋል። "ስለሚያስቱአችሁ ለዎች ይህን ጽፌላችኋለሁ፣ እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፣ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም" (1ዮሐ 2:26-27)። መንፈስ ቅዱስን በጥንቃቄ ማዳመጥን መማር ይገባናል። እርሱን ካዳመጥን የትኞቹ አስተማሪዎች የስህተት ትምህርት ሊያስተላልፉልን እንደሚሞክሩ ያስታውቀናል።

(3). የሚከተሉትን መግለጫዎች አጠናቅቅ።

ሀ. አስመሳይ ማለት_____ ነው።
ለ. ሶስት ዓይነት መንፈሶች ራሳቸውን በ_____ ይገልጻሉ።
ሐ. መናፍስትን በመለየት ስጦታ አማካይነት የክርስቶስ አካል___ይችላል።

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

መናፍስትን የመለየት ስጦታ ዋና ዓላማ የክርስቶስን አካል ከጥቃት ለመከላከል ነው። ይህ ስጦታ ወንጌል እንዲታገድ ከሚሞክሩ ዕርኩሳን መናፍስት የክርስቶስን አካል ይጠብቃል። ብዙውን ጊዜ አካሉን ከሚጎዱና ከሚከፋፍሉ የስህተት መናፍስትም አካሉን ይጠብቃል። ከዚህ በተጨማሪ መናፍስትን የመለየት ስጦታ የክርስቶስን አካል ከስህተት ትምህርት ይጠብቃታል። ይህ ሁሉ ጥበቃ የክርስቶስ አካል እንዲታነጽ ይረዳዋል።

(4). በሐዋ 16:16-18 በሐዋርያው ጳውሎስ ውስጥ የተገለጸው መናፍስትን የመለየት ስጦታ የክርስቶስን አካል ከምን ነበር የጠበቀው? _____

በልዩ ልሳን የመናገር ስጦታ

ዓላማ 2 የልዩ ልሳን ስጦታን ተግባርና ዓላማ መግለጽ።

የስጦታው ትርጓሜ

"ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር ይሰጠዋል" (1ቆሮ 12፡10)። *ልሳን* ማለት ቋንቋ ማለት ነው። የተለየ ልሳኖች የሚባሉት ያልተማርናቸው ቋንቋዎች ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 13፡1 ላይ "በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ...." ያለውን በማስታወስ ይህ ስጦታ ፍጹም ልዕለ - ተፈጥሮአዊ እንደሆነ ልንረዳ ይገባናል። የልዩ ልሳን ስጦታ በፍጹም ያልተማርነውን ቋንቋ መናገር እንዲቻል በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ችሎታ ነው። የሚሰጠው ቋንቋ አንድ ምድራዊ ቋንቋ ሊሆን ይችላል። የልዩ ልሳን ስጦታ በፍጹም በትምህርት የተገኘ ቋንቋ አይደለም። በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ቋንቋ ነው።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

የልዩ ልሳን ስጦታ በጣም ከሚታወቁት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ነው። ለክርስቶስ አካል እጅግ አስፈላጊ ነው። በዚህም ምክንያት ሰይጣን ሰዎች በልዩ ልሳን እንዳይናገሩ ለማድረግ ይሞክራል። ስለሆነም ስለ ስጦታው ልንረዳው የሚገባንን ያህል መረዳት ያስፈልገናል።

በልዩ ልሳን የመናገር አስፈላጊነት

ቀደም ሲል የትንቢት ስጦታ ከስጦታዎች ሁሉ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው ብለናል። ይሁን እንጂ በአንዳንድ መንገድ በልዩ ልሳን መናገርም ያንኑ ያህል አስፈላጊ ነው። ይህ ሊሆን ከሚችልባቸው ምክንያቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. የልዩ ልሳን ስጦታ ማንኛውም አማኝ ሊኖረው የሚችል ስጦታ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ፦ "ሁላችሁ በልሳኖች ልትናገሩ እወድ ነበር" ብሏል (1ቆሮ 14:5)።

2. የልዩ ልሳን ስጦታ በማንኛውም ጊዜ፣ በየትኛውም ስፍራና በማንኛውም የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ልንገልጸው የምንችለው ስጦታ ነው። አንድ ሰው ልዩ ልሳንን ዝግ ብሎ ወይም ከፍ ብሎ መናገር ይችላል (1ቆሮ. 14:28)።

3. የልዩ ልሳን ስጦታ ከዘጠኙ ስጦታዎች ሁሉ አማኙ ራሱን ሊያንጽ የሚችልበት መሠረታዊ የሆነ ስጦታ ነው (1ቆሮ 14:4)።

4. የልዩ ልሳን ስጦታ እንደ ጅማሬ ሊያገለግል ይችላል። ይህንን በምሳሌ መግለጽ ይቻላል። በእስራኤል አገር ሁሰት ዓይነት መቅረዞች ነበሩ። አንዳንዶቹ ሰባት ዘንጎች ሲኖሩዋቸው፣ ሌሎቹ ደግሞ ዘጠኝ ዘንጎች አሉዋቸው። ዘጠኝ ዘንጎች ካሏቸው መቅረዞች አንደኛውን ዘንግ ከሌሎቹ ስምንት ዘንጎች ሰይቶ ማንሣት ይቻላል። ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ይለኮሳል፥ ከዚያም በተለኮሰው በዚህ ዘንግ ሌሎቹ ስምንት ዘንጎች ይለኮሳሉ። ስለሆነም ይኸ አንዱ ዘንግ ለሌሎች ስምንት ዘንጎች መሰኮሻ ወይም ጅማሪ ነው።

የልዩ ልሳን ስጦታም እንደዚያ ነው። ልዕለ - ተፈጥሮአዊ ወደ ሆነው ክልል እንድንገባ ይረዳናል። ልዕለ - ተፈጥሮአዊ የሆነውን ልምምድ ያስጀምረናል ማለት እንችላለን። ሌሎቹን ስምንት ስጦታዎች እንድንገልጽ ያዘጋጀናል።

5. ልዩ ልሳን የመንፈስ ቅዱስ ቋንቋ ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ነው። ልዩ ልሳን በሰብአዊ ችሎታችን ልናደርግ ከምንችለው በላይ ከእግዚአብሔር ጋር በተሻለ መንገድ እንድንነጋገር ያስችሰናል።

(5). ከሚከተሉት መግለጫዎች እውነት ከሆኑት አንጻር "እ" ሐሰት ከሆኑት አንጻር ድግሞ "ሐ" ብሰህ ጻፍ።

___ሀ. ልዩ ልሳን ማለት በትምህርት ቤት የምንማረው ነው።
___ለ. በልዩ ልሳን የሚናገሩ አንዳንድ ሰዎች በመላእክት ልሳን ይናገራሉ።
___ሐ. በልዩ ልሳን መናገር ከዘጠኙ ስጦታዎች ሁሉ አስፈላጊነቱ እጅግ አነስተኛ ነው።
___መ. የልዩ ልሳን ስጦታ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ብቻ የሚገኝ ስጦታ ነው።

በልዩ ልሳን የመናገር ተግባር

በልዩ ልሳን መናገር በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ምልክት ነው። ማንኛውም ሰው በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቀ ጊዜ በልዩ ልሳን ይናገራል ብለን በመተማመን መናገር እንችላለን። እርሱ በማያውቃቸው አያሌ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ሊናገር ይችላል። በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ሰው በልዩ ልሳን ያናገራል ብሰን የምናምንበት ብዙ ምክንያቶች ይኖራሉ።

በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲወርድ በዚያ የተገኙት ሁሉ በልሳን ተናገሩ። በዚያም ስፍራ የነበሩት አስራ ሁለቱ ሐዋርያትና ከእንደ መቶ በላይ የሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች ነበሩ። መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ምን እንደሚሆኑ በዚያ ከነበሩት አንዳቸውም አያውቁም ነበር። በዚያ አንጻር ምንም ትምህርት አልተማሩም፣ ስሰሆነም ምንም የተሳሳተ ሃሳብ ወይም የተንደፈ ነገር አልነበራቸው። ይሁን

እንጂ በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቁ ጊዜ ሁሉም ተመሳሳይ ልምምድ ነበራቸው። ይኸውም ሁሉም በልሳን ተናግረዋል።

ስለሆነም በመንፈስ ቅዱስ በምንጠመቅበት ጊዜ ምን መጠበቅ እንደሚገባን ማወቅ ከፈለግን ልንመለከተው የሚያስፈልገን ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁ ስለሆነላቸው የቀረበውን መግለጫ ነው። በዚያን ጊዜ የተወሰነ ሁኔታ ይታይ ነበር። በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቁ ጊዜ ሁሉ በልሳን ይናገሩ ነበር። ይህንኑ በሚመለከት ከቀረቡት የመጀመሪያዎቹ መግለጫዎች አንዳንዶቹን ከዚህ በታች እንመልከት።

1. *አንድ መቶ ሃያዎቹ* በአንድነት የተሰበሰቡት "በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፣ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር" (የሐዋ 2:4)።

2. *የሰማርያ ሰዎች* የሐዋ 8: 14-17 ተመልከት። መጽሐፍ ቅዱስ በልሳን ተናግረዋል አይልም። ከዚህም በስተቀር በልዩ ልሳኖች አልተናገሩምም አይልም። በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንደተሰጣቸው፣ ስምዖን በተመለከተ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነገር ለማድረግ ኃይል ለመግዛት እንደ ፈለገ ግን ይናገራል። ስምዖን ምን አይቶ ነበር? የሰማርያ ሰዎች በልዩ ልሳን ሲናገሩ እንዳየና እንደሰማ እናምናለን።

3. *የጳውሎስ ልምምድ* የሐዋ 9:17 እንብብ። እዚህም ላይ በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቀ ጊዜ ጳውሎስ በልሳን ተናግሮ እንደነበረ ወይም እንዳልነበረ አልተነገረንም። ይሁን እንጂ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ "ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁና እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ" በማለት ተናግሯል (1ቆሮ 14:18)። መቼ መናገር እንደጀመረ ትገምታላችሁ? በመንፈስ ቅዱስ ከተጠመቀ በኋላ በልሳኖች እንደተናገረ እናምናለን።

4. *ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ* የሐዋ 10:44-47 ተመልከት። "በልሳኖች ሲናገሩ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና"።

5. *የኤፌሶን ሰዎች* የሐዋ 19:1-6 እንብብ። በዚህም ስፍራ በልዩ ልሳን ተናግረው እንደነበረ ግልጽ ነው።

ከዚህ በላይ የተሰጡትን አምስት መግለጫዎች ስንመረምር፣ ከእንደኛው በስተቀር፣ በተጠቀሱት መግለጫዎች የተገኙት ሰዎች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀዋል፣ በልሳንም ተናግረዋል። በመንፈስ ቅዱስ ሳይጠመቅ የቀረው ብቸኛው ሰው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 የተጠቀሰው ስምዖን ነበር። ልቡ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል ስላልነበረ ይህ ልምምድ ሊኖረው አልቻለም። ስለሆነም በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ሁሉ በልሳን ይናገራል ብለን እናምናለን።

(6). እንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ጊዜ ምልክቱ በልሳን መናገር ነው የምንለው፦

ሀ. በልሳን መናገር ልዕለ - ተፈጥሮአዊ የሆነ አሠራር ስለሆነ ነው።
ለ. በልሳን መናገር ለመማር ከባድ ስለሆነ ነው።
ሐ. በመንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያ የተጠመቁት በልሳን የመናገር ልምምድ ነበራቸው።
መ. በሐዋርያት ሥራ እንደተዘገበው በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁት ሁሉ በልሳን ተናግረዋል።

መንፈሳዊ መነቃቃትን ያስገኛል

በልሳን መናገር የአማኙን መንፈሳዊ ሕይወት ያንፃል። "በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል" (1ቆሮ 14:4)። ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው ተናጋሪውን ማነፅ በልሳን የመናገር እጅግ አስፈላጊው ተግባር ነው። አማኞች ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው መታነፅ ይስፈልጋቸዋል። "ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነፅ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ. . ." (ይሁዳ 20)። በመንፈስ ቅዱስ ለተሞላ አማኝ ሁሉ ይህ ታላቅ ረድኤት ነው።

በልሳን መናገር በራሱ ተናጋሪውን ያንፀዋል፣ ሆኖም የሚተረጎም ልዩ ልሳን የክርስቶስን አካል ያንፃል (1ቆሮ 14:4-5)። በጉባዔ ውስጥ ልዩ ልሳን በሚተረጎምበት ጊዜ መላው የክርስቶስ አካል የመታነፅ ልምምድ ይኖረዋል።

የሚተረጎም ልዩ ልሳን መላውን የክርስቶስን አካል የሚያንፀው እንዴት ነው? ብዙ ሰዎች የሚተረጎም ልዩ ልሳን ከትንቢት ስጦታ እኩል ነው ይላሉ። ይህ አባባል በተለይ ሐዋርያው ጳውሎስ "ማኅበሩ ይታነፅ ዘንድ ንግግሩን ባይተረጉም በልሳኖች ከሚናገር ትንቢትን የሚናገር ይበልጣል" በማለት በተናገረው ላይ የተመሠረተ ነው (1ቆሮ 14:5)። የሚተረጎም ልዩ ልሳን ከትንቢት ስጦታ ጋር እኩል እንዳልሆነ ብዙዎች ያምናሉ። ይልቁንም ሁለቱ ስጦታዎች ተደጋግፈው፥ የትንቢት ስጦታ ብቻውን አካሉን እንደሚያንፅ ሁሉ፥ መላውን አካል ያንፃሉ።

በዚህ በኩል ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ቁልፍ ጥቅስ የሆነው 1ቆሮ 14:2-3 ነው። "በልሳን የሚናገር ስለ እግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፣ የሚያስተውለው የለምና፥ በመንፈስ ግን ምስጢርን ይናገራል።"

የሚተረጎም ልሳን ከትንቢት እኩል ነው ብለው የሚያስተምሩ ሰዎች ሐዋርያው ጳውሎስ ያልተተረጎመውን ልሳን ሊረዳ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው ለማለት ፈልጎ ነው ብለው ያምናሉ። በእነዚህ ሰዎች አባባል ጳውሎስ ልሳን ምንጊዜም የሚነገረው ለእግዚአብሔር ነው ማለቱ አይደለም ይላሉ። አሁን እዚህ ላይ በሚተረጎመው ልዩ ልሳንና በትንቢት

መካከል ልዩነት ያለ ይመስላል። በልዩ ልሳን የሚናገር ሰው ለእግዚአብሔር ይናገራል፣ ትንቢትን የሚናገር ለሰዎች ይናገራል።

ከሐዋርያት ሥራና ከ1ኛ ቆሮንቶስ የተወጣጡትን የሚቀጥሉትን ጥቅሶችም ስንመረምር በልዩ ልሳን የሚነገረው ምንጊዜም ለእግዚአብሔር እንደሆነ እንገነዘባለን።

1. *የሐዋ 2:11* "የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን" አንዳንዶቹ በዚህ ጥቅስ መሠረት ስምቹ ስለ እግዚአብሔር ሥራ ለአድማጮቻቸው እንደ ተናገሩ ይመስላቸዋል። ሆኖም እንደዚህ የተባለላቸው እግዚአብሔርን ሲያመልኩና ሲያመሰግኑ ነበር። የሚናገሩት ለእግዚአብሔር ነበር።

2. *የሐዋ 10:46* "በልሳኖች ሲናገሩ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸ ዋልና" እነዚህም ቢሆኑ የተናገሩት ለእግዚአብሔር ነበር።

3. *1ቆሮ 14:14-15* እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ "በመንፈስ ማለትም በልሳን እጸልያለሁ" ብሏል። በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገር ነበር።

4. *1ቆሮ 14:16* "እንዲያማ ካነልሆነ፣ አንተ በመንፈስ ብትባረክ. . ." ጳውሎስ እዚህ ላይ ያለው "በልሳን እየጸለይክ እግዚአብሔርን ስትባርክ ... ነው።" እዚህ ላይ በድጋሚ ንግግሩ ወደ እግዚአብሔር ነው።

5. *1ቆሮ 14:17* "አንተማ መልካም ታመሰግናለህ" ይህም ማለት በልሳን እየተናገርህ ምስጋና የምታቀርበው ለእግዚአብሔር ነው።

ቀደም ሲል እንደተገነዘብነው በስጦታዎች መካከል አንዳንድ ጊዜ መደጋገፍ አለ። ምንም እንኳ የትንቢት አገልግሎት ለሰዎች ቢሆንም በብሉይ ኪዳን የነበረው ትንቢት ምስጋናንም ይጨምር እንደነበረ አንዳንዶች ያስተውላሉ። አንዳንዶች ይህንን ባይቀበሉትም፣ ምናልባት አንተ ይህንን መሠረት በማድረግ በግልህ የሚተረጎም ልዩ ልሳን የሚነገረው ለሰዎች ነው ብለህ ታስብ ይሆናል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አምስት ሁኔታዎች በልሳን የተናገሩት ሁሉ የተናገሩት ለእግዚአብሔር ነበር። ይሁን እንጂ በጉባዔ ለእግዚአብሔር መናገር ለምን አስፈለገ? ይህ አስፈላጊ ጥያቄ ነው። ለዚህ ጥያቄ ምላሹ በመንፈስ ማምለክ፣ በመንፈስ መጸለይ፣ በመንፈስ መባረክና በመንፈስ ማመስገን እጅግ በጣም አስፈላጊ ናቸው። ይህንን ስንተረጉመው እነዚህ የአምልኮ መግለጫዎች የእግዚአብሔርን በረከት ያስከትላሉ፣ መላው የክርስቶስ አካልም ይታነፃል።

ልዕለ - ተፈጥሮአዊ በሆነውና ለምዕመናኑ በሚነገረው የትንቢት ስጦታ አማካይነት የክርስቶስ አካል በምክርና በማፅናናት ቃል ይታነፃል። ልዕለ -

ተፈጥሮአዊ በሆነው፣ ዘሚተርንም ልዩ ልሳን አማካኝነት የክርስቶስ አካል በአምልኮ በመሳተፍ፣ በጸሎት፣ እግዚአብሔርን በመባረክና በማመስገን ይታነፃል።

የሚከተሉትን መግለጫዎች አጠናቃቸው።

(7). ያልተተረጎመ ልሳን_____ ያንፃል። የሚተረጎመው ልዩ ልሳን ግን የሚያንፀው _____ ነው።

(8). በልሳን መናገር አቅጣጫው ምንጊዜም ወደ _____ነው።

የተለየ እርዳታ

በልሳን በምንጸልይበት ጊዜ በተለመደ ሁኔታ እንዳንጸልይ፣ መጸለይ እንደሚገባን እንድንጸልይ ያስችለናል። "እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፣ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፣ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል" (ሮሜ 8፣26)።

በልሳን መናገር አማኝ ላልሆኑ ምልክት ሊሆን ይችላል። "በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም" (1ቆሮ 14:22)። አንድ አማኝ ያልሆነ ሰው ተናጋሪው ራሱ የማያውቀውን ቋንቋ ሲናገር በሚሰማበት ጊዜ አማኝ ያልሆነው ያ ሰው ወዲያውኑ እግዚአብሔር እንደሚናገረው ይገነዘባል። እግዚአብሔር በተነገረው ቃል ልዕለ - ተፈጥ ሮአዊነት፣ የሚያስተላልፈው መልእክት ሰውዬውን ላይናገረው ይችላል። ሆኖም በማንኛውም መንገድ የተነገረው ቃል ለአዳማጩ ጥቅም ነው።

በበዓለ ሃምሳ ቀን የሆነውም ይኸው ነበር። ከዓለም ዙሪያ ለዎች ሁሉ በኢየሩሳሌም ተገኝተው ነበር። በአንድነት ተሰብስበው በመጡ ጊዜ ከገሊላ የመጡት ሰዎች "የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻቸው ሲናገሩ እንሰማቸዋለን" አሉ (የሐዋ 2:11)። ይህም አማኝ ያልሆኑት የወንጌሉን ቃል እንዲሰሙ ዝግጁ ያደርጋቸዋል። በልሳን መናገር ወደ ኢየሩሳሌም ለመጡት ምልክት ሆኖላቸው ነበር።

(9). የሚከተሉትን መግለጫዎች አጠናቃቸው።

ሀ. መንፈስ ቅዱስ እንደ_____ፈቃድ እንድንጸልይ ይረዳናል።
ለ. በልሳን መናገር አማኙን ይረዳዋል ምክንያቱም_____ያውቃል።
ሐ. አማኝ ያልሆነ ሰው ክርስቲያኖች በልሳን ሲናገሩ ሲሰማ_ __ያውቃል።

በልዩ ልሳን መናገርን ስንለማመድ ልንከተላቸው የሚገቡ መመሪያዎች

በልሳን መናገር በጣም የተለመደ በመሆኑ፥ ስጦታውን በትክክለኛ አጠቃቀም መረዳት ይኖር ዘንድ አስፈላጊ ነው። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የልሳን ስጦታ ነበራቸው፣ ሆኖም ትክክለኛውን አጠቃቀም አላወቁበትም ነበር። በዚያም አቅጣጫ ተጨማሪ እውቀት ያስፈልጋቸው ነበርና ሐዋርያው ጳውሎስ አንዳንድ መመሪያዎችን ሰጣቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ የሰጣቸውን መመሪያዎች እስኪ እንመልከት።

1. በልሳን መናገር እጅግ ታላቅ ትኩረት ሊሰጠው አይገባም። 1ቆሮ 14:6 እና 14:26 አንብብ። በአምልኮ ስብሰባ ውስጥ በልሳን ከመናገር ይልቅ ለራዕዮች፣ ለእውቀት ቃል፣ ለትንቢት፣ ለመሠረታዊ ክርስትና ትምህርት፣ ለመዝሙሮችና ለልሳኖች ትርጉም ጊዜና ስፍራ ሊሰጣቸው ይገባል።

2. በአንድ የአምልኮ ስብሰባ በልዩ ልሳን የሚናገሩት ከሁለት ወይም ከሦስት ሰዎች መብለጥ የለባቸውም (1ቆሮ 14:27)።

3. በትዛዜ የሚነገር ልዩ ልሳን መተርጎም ይገባዋል (1ቆሮ 14:27)።

4. በአምልኮ ስብሰባ ላይ በልዩ ልሳን የሚናገሩ ካሉ የሚተረጉም ከሌለ ዐጥ ሊሉ ይገባቸዋል (1ቆሮ 14:28)።

5. በአምልኮ ስብሰባ ላይ በልዩ ልሳን የሚናገሩ መተርጎም እንዲችሉም መጸለይ ይገባቸዋል (1ቆሮ 14:13)።

6. በልዩ ልሳን መናገር ሊከለከል አይገባውም (1ቆሮ 14:39)።

7. በልዩ ልሳን መናገር ዙከትን ሊፈጥር አይገባውም (1ቆሮ 14:40)።

(10). የልዩ ልሳን ስጦታ በጠቃሚ መልኩ እንዲገለጽ ጠንካራ መሠረት የሚሆንለት _____ነው።

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

በልዩ ልሳን የመናገር ስጦታ ሁለት ዓላማ አለው።

1. የሚናገረውን አማኝ ማነፅ

2. በተተረጎመ ጊዜ የክርስቶስን አካል ማነፅ

ጉባዔው የሚታነፀው በመንፈስ ቅዱስ አንቃቂነት በሚካሄደው አምልኮ፣ ጸሎት፣ እግዚአብሔርን መባረክና ለእርሱም ምስጋና በመስጠት አማካይነት ነው።

አንዳንዶች በልዩ ልሳን መናገርንና ትንቢትን የግል መመሪያ ለማግኘት ሊጠቀሙባቸው ይሞክራሉ። ከዚህም የተነሣ በጣም ከባድ ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ልዩ ልሳን ምንጊዜም የሚነገረው ለእግዚአብሔር እንደሆነ ከተረዳን እርሱ ለሰዎች መልዕክት የሚሰጠው በዚህ መንገድ እንዳልሆነ መገንዘብ ይኖርብናል። ይህንን ስንል እግዚአብሔር በልዩ ልሳን ለሰዎች ሊናገር አይችልም ማለታችን አይደለም። ሆኖም ከተፈጸመ ተዓምራት ነው እንጂ የልዩ ልሳን ስጦታ አጠቃላይ ተግባር አይደለም።

የትንቢት ስጦታን ለግል መመሪያ መጠቀምን በተመለከተ ዶናልድ ጂ የተባሉት ሰው እንዲህ ብለዋል። "የትንቢት ስጦታ በአዲስ ኪዳን ምሪትን ለመስጠት ዓላማ እንደዋለ የሚገልጽ አንድም መረጃ እንደሌለ በእውነት ማረጋገጥ ይቻላል።" እዚህ ላይ አንድ ተጨማሪ ነገርም ሊታወስ ይገባል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ትንቢት ስጦታ ዓላማ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈበት ጊዜ ስጦታው የተሰጠው ለማነፅ፣ ለመምከርና ለማጽናናት ነው ብሎ ነበር። ዓላማው የተገለጸባቸው እነዚህ ቃላት፥ አንደኛውም ስጦታው የግል መመሪያ ለማግኘት እንደሚውል አያመለክትም። ሐዋርያው ጳውሎስ በሰጠው መመሪያ መሠረት ስጦታዎችን በምንገለገልበት ጊዜ፥ ከአደጋ እንጠበቃለን፣ የስጦታዎቹንም ዓላማ እናሟላለን።

(11). በልዩ ልሳን መናገርን ጨምሮ ለዘጠኙም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ታላቁና አጠቃላይ ዓላማው _____ነው።

ልዩ ልሳን የመተርጎም ስጦታ

ዓላማ 3 በልዩ ልሳን የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ ተግባርና ዓላማ መግለጽ።

ዓላማ 4 ይህንን ስጦታ በመግለጽ መንፈስ ቅዱስ እንዴት ሊጠቀምብህ እንደሚችል መግለጽ።

የስጦታው ትርጓሜ

"ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል" (1ቆሮ 12:10)። *መተርጎም* ማለት "መግለጫ መስጠት ማለት ነው።" ቃል በቃል ማስተርጎም እንዳልሆነ መረዳት አለብን። *ማስተርጎም* ማለት "በአንድ ቋንቋ የተነገረውን ያንኑ ነገር በሌላ ቋንቋ መናገር ነው።" ስለሆነም በልዩ ልሳን የተነገረውን መተርጎም "በሌላ ቋንቋ ለተነገረው ፍቺ መስጠት" ማለት እንደሆነ እንረዳለን። የልዩ ልሳንን ፍቺ የመስጠት ችሎታ ከመንፈስ ቅዱስ ብቻ እንደሚመጣ ልንረዳም ያስፈልገናል።

ስጦታው በምሳሌ ሲብራራ

ልዩ ልሳን በጉባዔ *መናገር* ተገቢ የሚሆነው በሚተረጎምበት ጊዜ ብቻ ነው። "በልሳን የሚናገር ቢኖር .... አንዱም ይተርጉም" (1ቆሮ 14:27)። ያልተተረጎመ ልዩ ልሳን በጉባዔ ውስጥ ከሐዋርያው ጳውሎስ *መመሪያ* ጋር ይቃረናል። "መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለማነፅ እንዲበዛላችሁ ፈልጉ" (1ቆሮ 14:12)።

በጉባዔ *መካከል* በልዩ ልሳን ለ*መናገር* በ*መንፈስህ* ውስጥ ግፊት ቢሰማህና የተናገርከውን የሚተርጉም ሰው ባይኖርስ? ይህ *ታዲያ* በ*መጀመሪያም መናገር* አልነበረብህም ማለት ነው? አይደለም። ***በመተርጎም በኩል መንፈስ ቅዱስ የሚጠቀምበት ሰው ለመተርጎም እምነት አልነበረውም አልታዘዘም ሊሆን ይችላል።*** ***ትንቢትንም በሚመለከት አሠራሩ ይህንኑ የመሰለ ነው።*** "እንደ *መንፈስ* ፈቃድ የሚኖሩ ግን የ*መንፈስን* ነገር ያስባሉ" (ሮሜ 8:5)።

በተጨማሪ የተናገርከውን የሚተረጉም ከሌለ "የሚተረጉም ባይኖር ግን በማኅበር *መካከል* ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር" የሚለውን የ*መጽሐፍ* ቅዱስ ቃል ስላልጠበቅህ ሊሆን ይችላል (1ቆሮ 14:28)። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የተናገርከው ነገር ባይተረጎም ቢቀር ቅር ሊልህ አይገባም። ይሁን እንጂ የሚተረጉም ሰው *መኖሩን* ባታውቅ እንደገና እንዳትናገር ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብሃል። ከዚህም በስተቀር በልዩ ልሳን የተናገርከውን ማንም ያልተረጎመው ከሆነ፥ ምናልባት እንተ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 14:13 ላይ "በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ" በማለት ለሰጠው ምክር የበለጠ ትኩረት *መስጠት* አለብህ ማለት ነው።

በልዩ ልሳን የተነገረውን *መተርጎም* በተ*መለከተ* ሌላም ጥያቄ አለ። *መንፈስ* ቅዱስ በልዩ ልሳን የ*መተርጎምን* ስጦታ በእኔ ውስጥ ሊገልጽ እንደሚፈልግ እንዴት ማወቅ እችላለሁ? *መልሱ* ለሌሎች ስጦታዎች ካቀረብነው ጋር ተመሳሳይ ነው። አንድ ሰው በልዩ ልሳን ከተናገረ በኋላ በ*መንፈስህ* ውስጥ ለአምልኮ፣ ለጸሎት፣ ለመባረክ ወይም ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ ታላቅ ግፊት ወይም የ*መናለቅለቅ* ሁኔታ ይሰማሃል። ከዚያ በኋላ *መንፈስ* ቅዱስ እንድትናገር የሰጠኽን በግልጽነት *መናገር* ይገባሃል። በ*መጀመሪያ* ጥቂት ቃላትን ብቻ ተቀብለህ ይሆናል። በእምነት *መናገር* ስትቀጥል ብዙ ቃላት እየተጨመሩ ይመጣሉ። ብዙም ሳይቆይ የ*መልእክቱን* ሙሉ ትርጉም *መስጠት* ይቻልሃል።

(12). ሐሰት ከሆነው *መግለጫ* አንጻር ያለውን ፊደል ክበብ።

ሀ. በአንድ ጉባዔ ሊነገሩ የሚችሉት የልዩ ልሳን *መልእክቶችና* ለትርጉም ቻቸው የተወሰነ ቁጥር የለውም።

ለ. የልዩ ልሳንን ዓላማ ሰዎች እንዲረዱ ማለትም፥ የክርስቶስ አካል እንዲ ታነፅ ከተፈለገ፥ በጉባዔ የሚነገር የልዩ ልሳን *መልእክት* ምንጊዜም *መተርጎም* አለበት።

ሐ. በልዩ ልሳን የ*መናገር* ዋና ዓላማ ለማያምኑ ሰዎች ነው።

መ. በጉባዔ ውስጥ በልዩ ልሳን የተነገረውን የሚተረጉም ከሌለ ተናጋሪው *መልእክቱን* የበለጠ ግልጽ አድርጎ በድጋሚ *መናገር* አለበት።

(13). በልዩ ልሳን የተነገረውን እንድትተረጉም *መንፈስ* ቅዱስ በውስጥህ እንደሚንቀሳቀስ የምታውቀው

ሀ. ልዩ ልሳን የተነገረበትን ቋንቋ የተማርህ ከሆነ።

ለ. የሚያዕናና ወይም ሕዝብን የሚመክር አንድ ነገር እንድትናገር ጥልቅ የሆነ የ*መንፈስ* ቅዱስ ኃይል በውስጥህ ሲንቀሳቀስ የሚሰማህ ከሆነ።

ሐ. በድንገት ወደ አእምሮህ የሚመጣ ለአምልኮ፣ ለጸሎት፣ ለበረከትና ለም ስጋና የሚያነሳሳ ቃል ለ*መናገር* በውስጥህ ጠንካራ ግፊት የሚሰማህ ከሆነ።

ስጦታው የተሰጠበት ዓላማ

በልዩ ልሳን የተነገረውን የ*መተርጎም* ስጦታ ዓላማ፥ በጉባዔ በልዩ ልሳን ለተነገረው፥ ትርጓሜ በ*መስጠት* የክርስቶስን አካል ማነፅ ነው። አባላቱ በልዩ ልሳን የተነገረውን በሚረዱበት ጊዜ *መታነፅ* ወደ አካሉ ይመጣል። በዚህ ዓይነት *መንገድ* ጉባዔው በአምልኮ፣ በጸሎት፣ በበረከትና ለእግዚአብሔር ምስጋና በ*መስጠት* ከፍ ወዳለ ደረጃ ይደርሳል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ አማኞች ሸክማቸው ይቃለልላቸዋል፣ ችግሮቻቸው ይፈቱላቸዋል፣ ደስታቸው ይጨምራል፣ *መንፈሳዊ* ሕይወታቸው ይጠነክራል። በ*መንፈስ* ቅዱስ ኃይልና በተነቃቃ ሁኔታ አባላቱ ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ *መሳው* ቤተ ክርስቲያን ይጠናከራል።

የሙከራ ፈተናዎች

የሐዋ 2:1-4፣ 10:44-47፣ 19:1-6 አንብብና የሚከተሉትን መግለጫዎች ሊያጠናቅቅ ከሚችለው ሐረግ አንጻር ያለውን ፊደል ክበበው።

1. በእነዚህ ወቅቶች በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁት አማኞች ሁሉ፡-

ሀ. ስብከት ሲያዳምጡ ነበር።
ለ. በልዩ ልሳን ይናገሩ ነበር።
ሐ. ለጸሎት ተንበርክከው ነበር።

2. ከቀረበው መግለጫ ጋር ተስማሚ የሆነውን ስጦታዎች የሚወክለውን ቁጥር በፊደሉ አንጻር ባለው ክፍት ቦታ ጻፍ።

1. በልዩ ልሳን መናገር
2. ልዩ ልሳንን መተርጎም
3. መናፍስትን መለየት

___ሀ. በሐዋ 16፡ 17-18 ላይ ሐዋርያው ከእግዚአብሔር ያልሆነ መንፈስ በአንዲት ገረድ እንደነበረ አወቀ።
___ለ. በሐዋ 2:1-4 ላይ በኅብረት ሲጸልዩ የነበሩ አማኞች ተምረው በማያውቁት ቋንቋ መናገር ጀመሩ።
___ሐ. ከአማኞች አንደኛው በልዩ ልሳን የተነገረውን መልእክት በሚተረጉምበት ጊዜ የአማኞችን ኅብረት ያንጻል።
___መ. ሌሎችን ስምንት ስጦታዎች መግለጽ እንድንችል የሚያዘጋጀን አንድ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አለ።

3. እውነተኛ ከሆኑት መግለጫዎች አንጻር ያለውን ፊደል ክበበው።

ሀ. መንፈስ ቅዱስ በአንድ አማኝ አማካይነት በልዩ ቋንቋ ሲናገር ያ ቋንቋ በምድር ላይ የማይታወቅ ቋንቋ ሊሆን ይችላል።
ለ. ዕርኩሳን መናፍስት መናፍስትን በመለየት ስጦታ አማካይነት ብቻ ሊታወቁ ይችላሉ።
ሐ. መናፍስትን የመለየት ስጦታ አንዳንድ ጊዜ ለሕመምተኞችና ለአካለ ስንኩላን በመጸለይ አገልግሎት ወቅት ጠቃሚ ስጦታ ነው።
መ. አንድ ሰው ከራሱ መንፈስ አውጥቶ ወይም ከሐሰት መንፈስ አለዚያም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ይናገራል።
ሠ. በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ሁሉ በልሳን አይናገሩም።

4. በልዩ ልሳን መናገርን የሚገልጸው ሌላ ቃል _____ ነው።

5. መናፍስትን የመለየት ዋናው ዓላማ_____ነው።

6. የልዩ ልሳን ስጦታ አካሉን እንዲያንጽ የሚያስፈልገው ሌላው ነገር_____ነው።

7. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የልዩ ልሳን ስጦታን አጠቃቀም በሚመለከት የትኛው ነው እንደ መመሪያ የሚያገለግለው? እውነተኛ ከሆኑት መግለጫዎች አንጻር ያሉትን ፊደሎች ክበባቸው።

ሀ. በልሳን መናገር ሁከትን ሊፈጥር አይገባም።
ለ. የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ብቻ በልዩ ልሳን የተነገረውን መተርጎም አለበት።
ሐ. በጉባዔ በልዩ ልሳን የተነገረውን የሚተረጉም ከሌለ በልዩ ልሳን የሚናገረው ስው ገዘም ማለት አለበት።
መ. በልዩ ልሳን የሚናገረው ስው መተርጎምንም እንዲስጠው እግዚአብሔርን ይጠይቅ የሚል ምንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለም።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. የሰው መንፈስ፣ መንፈስ ቅዱስና ዕርኩሳን መናፍስት

8. እግዚአብሔር

2. የትኛው መንፈስ ራሱን እንደገለጠ ማወቅ

9. ሀ. እግዚአብሔር
ለ. እግዚአብሔር በእርሱ አማካይነት እንደሚናገር
ሐ. እግዚአብሔር እንደሚናገር

3. ሀ. መቅዳት (መኮረጅ)
ለ. ስዎች
ሐ. ከጥቃት ሊጠበቅ
10. እውቀት

4. የወንጌሉን ቃል ሊያግድ ከነበረው ዕርኩስ መንፈስ አካሉን ጠብቋል።

11. የአካሉ መታነፅ

5. ሀ. ሐ
ለ. እ
ሐ. ሐ
መ. ሐ

12. ሀ. ሐሰት
ለ. እውነት
ሐ. ሐስት
መ. ሐስት

6. ሐ፣ መ
13. ሐ
7. ተናጋሪውን፣ አካሉን

የመከራ ፈተና መልሶች

ክፍለ ትምህርት 1

1. ሐ
2. እ
3. ሐ
4. እ
5. ሐ
6. እ
7. እ
8. ሐ
9. እ
10. እ
11. እ

ክፍለ ትምህርት 2

1. ሀ. እውቀት
   ለ. እምነት
   ሐ. ልምምድ

2. ሀ. እምነትን ያስገኛል
   ለ. እምነትን ይቆጣጠራል
   ሐ. ልምምድን ይመስናል

3. ሀ. ሐዋርያት
   ለ. ነብያት
   ሐ. መንፈላውያን
   መ. መጋብያን
   ሠ. አስተማሪዎች
   ማጣናዘቢያ፦ ኤፌሶን 4፡11

4. ሀ. ምክር
   ለ. ልግስና
   ሐ. መግዛት ወይም ማስተዳደር
   መ. ምሕረትን ማድረግ

   ማስታወሻ፦ ዕርዳታ ማድረግ፣ ማገልገልና
   ማስተማርም ተዘርዝረዋል።

5. ሀ. የጥበብ ቃል
   ለ. የእውቀት ቃል
   ሐ. እምነት
   መ. የፈውስ ስጦታዎች
   ሠ. ተዓምራት ማድረግ ስጦታ
   ረ. ትንቢት
   ሰ. ልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖች
   ሸ. ልዩ ልሳንን መተርጎም

ማስታወሻ፦ ቅደም ተከተላቸው ይህን ያህል
አስፈላጊ አይደለም።

6. 1ቆሮ 13፡1-2 ከመጽሐፍ ቅዱስህ ተመልከት

7. ለ

8. ለ

9. ሐ

ክፍለ ትምህርት 3

1. ሀ. 5
   ለ. 3
   ሐ. 1
   መ. 4
   ሠ. 2

2. እግዚአብሔር

3. ሀ. ሐሰት
   ለ. እውነት
   ሐ. ሐሰት
   መ. ሐሰት
   ሠ. እውነት

4. ወንጌል ወደ አዳዲስ ቦታዎች ያደርሳሉ፥ ሆኖም የክርስቶስን አካል ያንፃሉ፥ በበላይነትም ይቆጣጠራሉ።

5. መተንበይ ወይም አንድ ሁኔታ ወደፊት እንደሚሆን መናገርና ማወጅ፥ የእግዚአብሔርንም መልእክት መተርጎም።

ክፍለ ትምህርት 4

1. ሀ. መጋብያንና አስተማሪዎች
   ሠ. ሐዋርያት
   መ. ወንጌላውያን
   ሰ. ነብያት

2. ለ እና ሐ

3. ሐ

4. መልሶች ሁሉ ትክክል ናቸው

5. ፍቅር. . .የማይገባውን አያደርግም፣የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም፣ በደልን አይቆጥርም፣ ከእውነት ጋር ደስ ይሰኛል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም።

ክፍለ ትምህርት 5

1. ሐ
2. እ
3. እ
4. ሐ
5. እ
6. ሐ
7. ሐ
8. እ
9. ሐ
10. እ
11. እ
12. ሐ
13. እ
14. እ

ክፍለ ትምህርት 6

1. ያለውን ቁሳቁስ፣ ጊዜውን፣ ጉልበቱንና ችሎታውን መስጠት

2. ጳጳስ፣ መጋቢ፣ ሰብሳቢ፣ ሽማግሌ፣ ረዳት

3. ሀ. ማስተዳደር
   ሰ. መርዳት
   ሐ. መለገስ
   መ. ምሕረት ማድረግ

4. መግዛት ወይም ማስተዳደር
5. ልግስና
6. ሀ. ምሕረት ማድረግ
   ለ. መርዳት
   ሐ. መለገስ
   መ. መግዛት ወይም ማስተዳደር
   ሠ. ምሕረት ማድረግ

7. ግብረገብ፣ ማስተማር፣ መምከር

ክፍለ ትምህርት 7

1. ሐ
2. እ
3. ሐ
4. እ
5. ሐ
6. ሐ
7. እ
8. እ
9. እ

ክፍለ ትምህርት 8

1. ለ

2. ሐ

3. ሀ እና ሰ

4. ሰ

5. ሐ

6. ለ

7. ፈውስ፣ ተዓምራት ማድረግና ትንቢት

8. የክርስቶስን አካል ለማነፅ

9. ሁሉን ቻይ

10. እንቅፋቶችን

11. ማፍረስ

12. በምክር፣ በማፅናናት

ክፍለ ትምህርት 9

1. ለ

2. ሀ. 3
   ለ. 1
   ሐ. 2
   መ. 1

3. ሀ. እውነት
   ለ. ሐሰት
   ሐ. እውነት
   መ. እውነት
   ሠ. ሐሰት

4. ቁንቁዎች

5. አማኞችን ከጥቂት መጠበቅ ወይም አካሉን ከክፉ መጠበቅ።

6. በልዩ ልሳን የተነገረውን መተርጎም

7. ሀ. እውነት
   ለ. ሐሰት
   ሐ. እውነት
   መ. ሐሰት